


t.me/OLDBOOKSPDF

## ክፍል - አንድ

# የግንፍሌ ማለዶች

t.me/OLDBOOKSPDF

የተተፈተፈ ቅንድቡን እያዩ ትግሬዩ የሚሉትም አሉ:: ያልተፈነከትነው እኔና አሰፋ ጢሬሪ ብቻ ነበርን:: አሰፋ ጢሬሪ ካልደረሱበት የማይደርስ ስለሆነ ነው:: ከደረሱበት ደግሞ ሦስት ቀንም ቢሆን እየተከታተለ ይነሜነሜል እንጂ ልማታ አይልም:: እኔ ደግሞ ዛሬ ቀመስኩ::

ጓደኞቼ የመፈንከት ቆሊያቸው ስላልተገፈፈ ወይም የሞትኩ ያህል ስለ ቆጠሩኝ እንደ አስከሬን ተሸከሙኝ:: ከሚጢጢ እጆቻቸው የተበጀ ርብራብ ቃሬዛ ላይ አንጋለሉኝ:: ሰውነቴ ዘና ብሎ የመንሳፈፍ መንፈስ ተሰማኝ:: አሁንም ፊንከቼ እየተግለበለበ ወደ ሰማዩ-ሰማያት የሚሮጥ መሰለኝ:: የጉም ችፍርጉን እየጣሰ ወደ ላይ.....

...ከተንጋለልኩበት እንደምንም እንገቴን አቅንቼ በአንድ አይኔ ወደ ፊት አየሁ:: ጋሙዳው እጆቼን ሰቅሰቆ ወገቤ ስር ከትቶ ብቻውን የተሸከመ የሚያስመስለው ድርሻ ወሰደ:: ቀጮ የያዘችው ቁርጭምጭሚቴን ነው:: ሙቂ ትንሽ ከፍ ብሎ ባቴ ላይ እጁን አጋድሟል:: የተረፉት በእንፋሽ እከንፋሽነት ፊት ፊት ይላሉ::

"መንገድ! መንገድ!"

እንደ ጓደኞቼ እጅ የሚያንፈላስስ የሸለብታ እቅፍ ውስጥ ሆኜ የሚያስተጋቡ ድምፆች ይሰሙኛል::

- ምን ሆኖ ነው?

- ጋንጩር ፈንከቶት::

- እሱ ልጅ ምን ይሻላል ይኼን ድንጋይ መወርወር? አበስኩ ገበርኩ! ደሙ ማለቁ አይደለም እንዴ?

በድምፃቸው የጋሙዳ እናት እንደሆኑ አውቄያለሁ:: ቃችኛው ሠፈር ደርሰናል ማለት ነው:: ሚዳውን ካቋረጥን አቤት:: በዚህ መካከል የይጋርዱ ቁጦ ድምፅ እያስገመገመ ከበበኝ::

- እንዴ? እንዴ? መቼም ያ ጋንጩር ነው:: ቆም አድርጋችሁ ደቃቅ አፈር ካስንሱበት እንጂ ደሙን እንዲያቆምለት::



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሦስት

የፕላስተሩ ድሪቶ እንደ አልቅት ግንባሬ ላይ ተለጥፎብኛል፡፡ አዚያ ካሊም የተነጠፈበት የልብስ ሳጥን ላይ እንደተንጋለልኩ አባቴ መጣ፡፡ እኔ ሳመሽ እንደማደርገው ኤልቪስ ፕሪስሊውን ብቻ ብቅ አድርጎ ወደ ውስጥ አየ፡፡ እናቴ ጓዳ ናት፡፡ ገባ፣ አየኝ፡፡

"ምንድን ነው?" አለ፡፡

ለመጠጣቱና ለማምሸቱ መሸፋፈኛ ሲያደርገኝ እንዳሰበ ገባኝ፡፡ በአጥንታም እጁ አገጬን አከርሮ ይዞ ግንባሬ ላይ አተኮረ፡፡ እናቴ ከጓዳ ወጣች፡፡

"አጅሬ" በሚል አሱን አየችው፡፡

"ማነው? ምንድን ነው?....." እንደኔ ተርበተበተ፡፡ ሳጠፋ እናቴ ጥላዬን እንዳትወጋብኝ እንደምሆነው፡፡

"ልጅ ነው፤ ተፈነከተ" አለችው አቅልላ....

"ለምን አልላከሽብኝም?"

"ምን ሆነና? ልጅ እንደተፈናከተ ነው፡፡"

"ሲሞትስ ልጅ እንደተጋደለ ነው ልትይ ነው?"

"አያድርገው እንጂ ቢሞትስ ምን ልትፈይድ ነው የምትጠራው?" አለች፡፡

ዛሬ እናቴ ምን ነክቷታል? ጠልታኛለች ወይስ ምንድን ነው?

አባቴ ኤልቪስ ፕሪሲሊውን ደፋ፡፡ ይሄኔ ከእናቴ ፈቃድ ቢያገኝ ኖሮ...

እናቴ አባቴን ከጫካ አጥምዳ፣ አስራ፣ የሚበላው እየሰጠች የገራችው የማዷ አውሬ ይመስለኛል፡፡ እናቴ ብትፈቅድለት አባቴ ከቅርብ ጎረቤት እስከ ሩቅ ዘመድ



t.me/OLDBOOKSPDF

ድረስ መደዳውን በር እየገነጠለ በቴስታ የሚረመርም ይመስለኛል:: እንኳን ሌላው ቀርቶ እኔም ልጁ የቴስታው ተቋዳሽ ከመሆን አይቀርልኝም::

አንድ ጊዜ እናቴ በእኔ ተናዳ አባቴ ሲመጣ አልጎመጎመችበት:: "ተቆጪ አባት የለው..."

አባቴ ከአፏ ተቀብሎ እንደ ጭልፊት አንጠልጥሎኝ ወደ ላይ የበረረ ይመስለኛል:: ምን እንዳደረገኝ ከትውስታዬ ውጭ ነው:: ብቻ ወደ ዳመናው ይዞኝ ወጣ:: ጉዟችን ወደ ሰማየ-ሰማያት ነው:: ለፀሐይ ቀረብን መሰለኝ ብርሃን ዋጠኝ፣ ከፀሐይ አልፈን ሄድን መሰለኝ ጨለመ:: ከዚህ የለቀቀኝ እንደሆን መሬት ለመውደቅ ሰባት ቀን ሳይወስድብኝ አይቀርም::

"የአባት እጅ አሳየው" ብትለው አስር አጥፍ የእንጀራ አባት እጅ አሳየኝ:: አባቴ ለእናቴ ይኸው ነው::



t.me/OLDBOOKSPDF

# አራት

የሚቧጥጥ ኡኡታ ተሰማ፡፡ የግብግብ ድምፅ ተከተለ፡፡

"እገድለዋለሁ፤ እገድለዋለሁ" ጋሽ ድንቁ ነበሩ የሚፎከሩት፡፡ አባቱ ላይ መስሎኝ ቀና ብዬ አየሁት፡፡ ድንጋጤ ሆነ ደስታ አዘውትሮ አይሰማውም፡፡ እናቱ ስትደነግጥ ወይም ስትደሰት እጁቢ ነው፡፡ አሁንም ፓሪሲሊውን ከደፋበት አላነሳም፡፡

"አለቀውም! አሁን እኔ የላኩት አይመስልም፣ ወዳጆቼ? ዛሬ በሥጋው ነው የምቆርጠው" ጋንጩርን እንደሆነ ገባኝ፡፡ የጋንጩር እናት በጩኸታቸው መጧጠጣቸውን ቀጥለዋል፡፡ በጥርሳቸው ነው እንዴ የሚጮሁት? ጋሽ ድንቁ ይዘውታል ማለት ነው፡፡ ከአባቱ ሲያመልጥ ራቅ ብሎ ይፈነከታቸው ይሆን? ጆሮዬን አቆምኩ፡፡

ጋንጩር ፀቡ እራቅ ብሎ ነው፡፡ ድንጋይ ወርውሮ ስለማይስት ከያዙት የማይለቁት ብዙ ናቸው፡፡ ጋንጩርም እስኪለቁት የፈረዱበትን በፀጥታ ይቀበላል፡፡ ቡክስ፣ ጥፊ፣ ንክሻ፣ እርግጫ፣ ጠረባ....ዝም፡፡ ሲለቁት ደግሞ የጥቃቱን ያህል የድንጋዩን መጠንና ቁጥር ይወስናል፡፡ ተለቅ ተለቅ ያለ ሦስት? ሁለት? አንድ? ... የወሰነውን ያህል ሳይዛነፍ ይፈነክታል፡፡ ስለዚህ ከጋንጩር ጋር ተጣልተው ከደበደቡት በኋላ መልቀቅ የሚያስከትለውን በማሰብ ይዘውት የሚጮሁ ብዙ ልጆች ናቸው፡፡

ጋሽ ድንቁን "እንዳትለቁት ይፈነክቶታል" ማለት ከጀለኝ፡፡ ይኼኔ የጋንጩር እናት የሚጮሁት ባላቸው ወደፊት መፈንከታቸው አሳስቧቸው ሊሆን ይችላል፡፡

እናቴ "ምንድን ነው?" እያለች ከጓዳ ወጣች፡፡ አባቴ በእጁቢነት "ምንድን ነው?" አለ፡፡

ተከተልኩ፡፡ እናቴ በራችንን ሳትለቅ ወደነጋንጩር ቤት አትጣጫ አጨነቆረች፡፡ እኔ ተሚቧን ፈልፍዬ ወሬውን ለመቋደስ ሞከርኩ፡፡ ምንም የሚታይ



t.me/OLDBOOKSPDF

"ከሰው መካከል ውጣ!" ይላል። እኔ ልጆቹ ሲሮጡ አብሬ እሮጣለሁ። ዛሬ ግን አበዛሁትና ዝም ብዬ ቆምኩ። እሱም የመጣ ይምጣ ብሎ ፊነከተኝ።

"ተፋናከትሽ አይደል?" አልኩት።

"እራስህ ነሃ ፤ ማን ተማታ አለህ?" አለኝ።

"አለቅህ መሰለሃል፤ እገድልሃለሁ"

"ብትገድለኝ እንኳን ለትንሣኤ ሙታን ጠብቄ በሞቶ ድንጋይ እፈነክትሃለሁ" አለኝ የተተመጠበት እየተቁነጠነጠ። እንደ ድሮዬ መፈንከት የምፈራ መሰሎታል።

እናቴ ድንገት ዘው ብላ "እናንተ እፍ ለእፍ ገጥማችኋል እኛ አዋቂዎቹ እንታመሳለን" አለች።

ጋንጩር ዛቻዬን ሲናገር ሲያቆበቁብ በአይኔም በእጄም ለመንኩት። እናቴ ታቅፌ የቀረሁትን ዝርግ ሰሃን እያየች "አትበላም እንዴ?" አለችኝ።

"በቃኝ" አልኳት። ጥላዬን ለመውጋት ሰበብ እየፈለገች መሰለኝ።

"በኋላ እንደለመድከው በእኩለ ለሊት ራበኝ ብትል ታገኝ መስሎሃል።" የመነጠቅ ያህል ሰሃኑን ተቀበለችኝ። ወደ ጋንጩር ዞራ "ዛሬ የአንተ አባት ተነስቶባቸዋል እዚህ ታድርና ነገ ሲጣናቸው ሲበርድ..."

ጋንጩር እዚህ ሲያድር? ደነገጥኩ!! የአንዳንድ ጊዜ የእኛ ቤት አዳር እንኳን ለባዕዱ ጋንጩር ለእኔም ትዝብት አለው። እና ያ አንዳንድ ጊዜ የእናቴና የአባቴ ሁኔታ ዛሬ ማታ ቢደገምስ? የጭንቀት መአት ወረደብኝ።

"እሰቲ እርፈህ እውራ" እናቴ

"እናልሽ..." አባቴ

"እ...ሆ..ሆ..ይ... እጅህ ነው የሚያወራው?" እናቴ ድምፅ ውስጥ ግን የአባቴን እጅ መጥላት የለበትም። ብትጠላውማ...

"እናልሽ...እንዳየሁሽ ደነገጥኩ። ከባልኮኒው ጀርባ ብርጭቆ እያጠበሽ ነው። ቀዮቹ ሲቶች በማይታዩበት ጭለማ ዳንስ ቤት እንቺ በግ ብለሽ አይኔን


t.me/OLDBOOKSPDF

አጥበረበርሽው፡፡ እየደነስኩ የማናት ጠይም ጨረቃ? እልኩ ለራሴ፤ ለካ እንቺም አይተሽኝ ደንግጠሻል፡፡"

"ጉረኛ ሥራ አጥቼ፤ እኔ ለራሴ..."

የእናቴንና የአባቴን የጭላማ ወሬ አንድ በአንድ ለቅሜ አውቀዋለሁ፡፡ ለምን እንደጠላ እንደሚደጋግሙት እንጃ!! ቀጥሎ 'አንድ ቀን እኮ ልብ ሳትይው ነግረሽኛል' ይላል አባቴ 'እንዳይከፋህ ነዋ የዋሸሁህ' ትለዋለች እናቴ 'ይልቅ እጅህን አሳርፍና አውራኝ ትለዋለች፡፡ "እናልሽ..." ይላል አባቴ፡፡

"እናልሽ..." አለ አሁንም "እናልሽ የዚያች ማታ ቤቴ ገብቼ 'ጠይሟ ጨረቃ' የሚለውን ግጥምና ዜማ ደረስኩት፡፡

"በእኔ የተነሳ?" እናቴ ደሞ! ይሄን ስንቴ ሰምታ፤ ይሄን ስንቴ ጠይቃለች? ከመወለዴ በፊት ስንቴ? ከተወለድኩ በኋላ ስንቴ?... ኡፍ! ላለማዳመጥ ጆሮዎቼን በሁለት እጆቼ እደፍናለሁ፡፡ ቀደም ሲል ጭንቅላቴ ውስጥ ተቀርፆ የተቀመጠው በተራው ያጠነጥናል፡፡

"ግጥምና ዜማውን ለኮሎኔል ወሰጄ ስጠኋቸው፡፡ 'እንዲህ ነው እንጂ' አሉ 'ቅመም ነሽ እኮ' አሉኝ፡፡ ትንሽ ስለነበርኩ እንቺ ነው የሚሉኝ፡፡"

"እሱን ተወው፤ ዕድሜዬህንማ ጨልጠህ የጠጣህ ነህ፡፡ እስቲ እጅህ ይረፍና አውራኝ፡"

"እናልሽ...."

ታዲያ ወሬያቸው የተደጋገመና የማውቀው ከሆነ እኔን ለምን ያናድደኛል? "እንቺ ለምለም..." እላለሁ፡፡

"ልጅህ ተነሳበት፤ ምቀኛ ነው መቼም ሰው ደስ ብሎት ሲጫወት አይወድ፤ ምንድን ነው? አርፈህ አትተኛም?"

"እራብኝ"

"እራትህን በልተህ ተርፎህ ተነስቶ?" መብራት ይበራል፡፡ ደስ ይለኛል፡፡ አንግዲህ አንቅልፍ እስኪወስደኝ ስለሚጠብቁ ፀጥ ይሏታል፡፡ የእናቴን ከምር መናደድ ላለማየት እከናነባለሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

መንፈስነት ሰው ቤት ውስጥ የሚገኝ ስውር ባሕሪ አይንፀባረቅበትም፡፡ ከብደት የሚያነሳ፣ ጉሽ አፕ የሚሰራ፣ ሲትአፕ የማይጠቀመው፣ ከስፖርት ቤት የማይጠፋ አይነት ነው፡፡

"ይሄ ልጅ ምን ሆኖ ቀረ? አባረርከው እንዴ?" አለች እናቴ

"አባረርከው እንዴ?" አለ አባቴ ከእሷ ቀበል አድርጎ፡፡ ፕሪስሊውን ቀና አደረገና እንደ ጭልፊት አፈፍ አድርጎኝ ወደ ሰማይ-ሰማያት ሊበር አቆበቆበ፡፡ እናቴ፦ ገልመጥ አድርጋ ፀጥ አሰኘችልኝ፡፡

"ኧረ እኔ..." እያልኩ ወደ በሩ አፈገፈግኩ፡፡ ሳላውቀው በሩን ጠርቅሜው ኖሯል፡፡ እንገቴን አስግጌ ስመለከት "ማሰሮውን" ከተጣደበት አጣሁት፡፡ ደነገጥኩ፡፡ በእናቴ ጥላዬን ሊያስወጋብኝ፡፡

"ሴጣንን እፈነክታለሁ ሲል ነበር" አልኳት፡፡

"ምን? ምነው እሱ ልጅ ተጨማለቀ..." ገፍተር አድርጋኝ ወደ ውጭ አለፈች፡፡ ትከሻዋ ላይ ያጣፋችው ነጠላ የሳንቡሳ ሊጥ መስሎ በጨለማው ውስጥ ይታያል፡፡ የእነ ጋንጩርን ኮሸሽላ አጥር አልፋ ወደ ጓሮ ዞራለች፡፡ የጋንጩር ድፍረት ብቻ ሳይሆን የእኔ ፍርሃት አስገረመኝ፡፡ ይሄኔ እናቴ ስትደርስ ሴጣን ሳያስበው በጋንጩር እንዴ ተመቶ "ድገመኝ" እያለ እግሩ ስር ይንከባለላል፡፡ በጭራውም ጭምር ይለማመጣል፡፡ ጋንጩር ችግኝ መስሎ እንደተተከለ ሴጣኑን ይመለከተዋል፡፡

"ምነው ልጄ ልብ ብትገዛ" የእናቴ ድምፅ ነበር ጋንጩርን አስቀድማ መጣች፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"እናልሽ" ይላል አባቴ "አንድ ጊዜ ትዝ ይልሻል?"

"ምኑ?" ትላለች፡፡

"አከስትሽ ተጣልተውሽ ይሆን ልከውሽ እንጃ ለአንድ ሳምንት ጠፍተሽ ነበር፡፡"

"እሷ ምን ትጣላኛለች፡፡ እንደውም እንደ ልጅ የማፈጥባት እኔ ነኝ፡፡"

"እናልሽ፤ ብጠይቅ ባስጠይቅ አየኋት የሚል ጠፉ፡፡ ግራ ገባኝ አጠፉፍሽ ድንገት እንደ ጤዛ ዱካ ሳታሰሚ፡፡ ቢጨንቀኝ በፊትም አልነበረች ይሆን አልኩ?"

"አቤት! ማባበሉን ስታውቅበት"

"ፍቅራችንን!"

"እ...ሽ"

"እናልሽ መዕናኛ ጊታሬን አንስቼ ደንቀፍ ሳያደርገኝ አንድ ግጥምና ዜማ ደረስኩ፤ ዝም ብዬ እንደ እንባ ወረደኝ ብልሽ ይቀላል፡፡ ከዚህ ቀደም የማውቀውን ዘፈን እያንጎራጎርኩ ነበር የመሰለኝ፡፡ በኋላ ኮሎኔል ሰምተው 'ቅመም ነሽ እኮ' አሉኝ፡፡

"የትኛው ነው ዘፈኑ?"

"ልዘፍንልሽ አይደል....

....እሆሆ ገዳማ ገደምዳማዬ
እሆሆይ ገዳማ ገደምዳማዬ
የኔን ጠይም ወጣት አያችሁ ወይ፤"

መቼም የአባቴ ድምፅ ሌላ ነው፡፡ ነሸጥ ሲያደርገው ተነስቶ ጊታር እንደሚመታ ሁሉ በቀኝ እጁ ጣቶች እየደነቋቆሉ በግራ እጁ ጣቶች እየጠቋቆመ ተመስጦ ይዘፍናል፡፡

"ገዳማይ
አከሰቷን ባስጠይቅ
ገዳማይ



t.me/OLDBOOKSPDF

እንጃልህ ይሉኛል
ገዳማይ
ጎረቤት ባስጠይቅ
ገዳማይ
ወጣ አለች ይሉኛል
ገዳማይ
እንደምን አድርጌ
ገዳማይ
ልቤን ላሳያቸው
ገዳማይ
አይጨክኑም ነበር
ገዳማይ
እንደኔ ቢያማቸው።"

በዚህ ዘፈን የእናቴ ፊት በንዴት ሲዳፈርስ ካንዴም ሦስቴ አይቻለሁ። አባቴ ሲጀምረው ባይረዳውም እዚች ጋ ሲደርስ ደንግጦ ያቆማል። "ቀጥል እንጂ... ምን አስቆመህ?" ትለዋለች። ቅስሙ ተሰብሮ ህሞቱ ፈስሶ ይቀጥለዋል።

ገዳማይ
ሲቸግረኝ ጊዜ
ገዳማይ
ግራ ቢገባኝ
ገዳማይ
ትገኝ እንደሁ ብዬ
ገዳማይ
እዛ ቤት ሄድኩኝ
ገዳማይ
ብሄድም አልከፈቱኝ
ገዳማይ
አጅግ ቁናኝ እንጂ
ገዳማይ



t.me/OLDBOOKSPDF

የተሰጣቸውን ሽልጦ፣ የድፎ ቁራሽ፣ ፍርኖ ወይም አሹቅ ይዘው ፀሐይ ለመሞቅ ብቅ ሲሉ ካደፈጠበት ወጥቶ "ወጋሁ!" ይላል፡፡ ይሰጡታል፤ ወይም "ባትወጋ ብዩሃለሁ" ብለው ያፍሩበታል፡፡ አይለቅም፡፡ ይጨቃጨቃል፡፡

ለጋሙዳ መድሃኒቱ መሰፍን ሲንጢ ናት፡፡ ገና ከቤቷ ሳትወጣ ድምጿን ዘለግ አድርጋ "ጋሙዳ ባትወጋ" ትላለች፡፡ "ባትወጋ ባትወጋ ባትወጋ" ጋሙዳ እየተነጫነጨ ይወጣል፡፡ "ገና ሳታየኝ ነው እንዴ?" ይላል፡፡

ይኼን እያሰብኩ ጋሙዳ ከነጋንጩር አጥር ስር ብቅ ብሎ "ወጋሁ" አለኝ፡፡ ጣቱን የጠቆመው እልጣበቅ ያለኝ ፕላስተር ላይ ነበር፡፡ በመደንገጥ እየተናደድኩ "እንካ ብላ" አልኩት፡፡ ሊቀበል ካለ በኋላ እጁን እየሰበሰበ፤

"ፍርኖ መሰለኝ፣ እታች ሆኜ ሳየው፣ ይመስላል" አለ እየተቆጨ፡፡ በየት በኩል አቆራርጦ አጠገቤ ብቅ እንዳለ እያሰብኩ ተደንቅኩ፡፡ ደግሞ በዚህ ጭጋግ ውስጥ እጄ ላይ የሆነ ነገር መያዜን ማረጋገጡ፡፡

"ጋንጩርን አትለቀውም አይደል?" አለኝ፡፡

'እለቀዋለሁ? አለቀውም?' ለራሴም ግራ ገባኝ፡፡ ግንባሬ ላይ ያረፈች ጢንዚዛ በእጄ ደፍኜ እንደያዝኩ ሁሉ ቁስሌን ከድኜ ዝም አልኩት፡፡

በሽሙጥ እያየኝ "ከእንግዲህ በቴስታ መማታት አትችልም፡፡ ስለዚህ ሁሉም ይምጣልኝ እያሉ ነው፡፡" ዝም አልኩት፡፡ ቴስታ በግንባር መሰኗቸዋል፡፡ ግን ከጆሮ ከፍ ባለው የጭንቅላት ማዕዘን መሆኑን እኔና አባቴ ብቻ እናውቀዋለን፡፡

---

[1] "ወጋሁ" ከሆኑት የሚበላ ነገር የሚከፈል ግዴታ ያለበት የልጆች ጨዋታ ነው



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሰድስት

አባቴ ለምሳ አልመጣም፡፡ ምስኪን አባቴ! በአባቴ ፋንታ ጋንጩር በራችን ላይ አንዣበበ፡፡ እናቴ ጠርታ ምሳ ሰጠችው፡፡ ከሊም የተነጠፈችበት ሳጥን ላይ ሆኖ ሲበላ ሳየው አንጀቴ አረረ፡፡ ዝርግ ሰሃኑ ላይ የተነጠፈው እንጀራ መረቅ ያለው ምስር ወጥ ፈሰበት በጋንጩር ያልታጠበ እጅ ይተገተጋል፡፡ እናቴ ወደ ጓዳ ስትገባ ጠብቄ "ቀላዋጭ!" አልኩት፡፡

በማብሸቅ ፈገግ አለ፡፡ ይባስ ብሎ እንደኔ "አንቺ ለምለም" ብሎ ተጣራ፡፡ የእናቴን ምላሽ ለማወቅ ጓዳ ጓዳውን አየሁ፡፡ እናቴ ከሚገርም ፈገግታ ጋር ብቅ ብላ አየችው፡፡

"ወጥ ጨምሪልኝ" አላት፡፡

"እያነካካህ ብላ እንጂ" አለችው፡፡

የእናቴ ምላሽ የጋንጩርን ድፍረት ለማበረታታት እንጂ ወጥ ለመሰሰት እንዳልሆነ በሚያስታውቅ አኳኋን፡፡ በገንኩ፤ ነፈርኩ፡፡

"ለምለም ይላል እንዴ?" የልጅነት መንበሬ በጋንጩር የኩዴታ ድርጊት እየተናጋች የመጣች መሰለኝ፡፡

እናቴ ፈገግ እንዳለች ያመጣችውን ወጥ ከጋንጩር ሰሃን ላይ አውጥታ ጭልፋውን እንዲጠራርገው ሰሃኑ ላይ ተወችለት፡፡ "የምግባር ትምህርትህ ይቆይ" አለችኝ፡፡

"እንዴ ታዲያ እኔ የእሱን እናት..."

"ምን ሆኗል ልጄ?..."

እውነትም ምን ሆኛለሁ? ያላወቅኩት ጥቃት ሆዴ ገብቶ እንባዬን አረገፈብኝ፡፡

"እገልልሻለሁ" አልኳት፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

አይኔን በጠባቡ ከፍቼ አያለሁ:: ይኸ የእልህ ጨዋታ ከእናቴ ሁኔታ የመነጠል ፍላጎቴን አላሳካልኝም::

"እናቴ ጠሊታኛለች ወይስ ምንድን ነው?"

እንደ አባቴ ለልምምተ የሚሆን የዘፈን ጀብዱ የለኝ፤ አንዳንድ ጊዜ ዝም ብሎ በመዝፈን ብቻ ይታረቃት እንደነበር አስታውሳለሁ:: ምስር ስትለቅም የበሩን ብርሃን ጋርዷት....

"ገላ - ኮርተሽ ተቀመጪ
"ገላ - እንቺ ምን ቸገረሽ
"ገላ - በውበት ማራኪ
"ገላ - አድርጎ ከፈጠረሽ"
"ይልቅ ብርሃን አትከልለኝ..." እናቴ
"ገላ - መድፍ አዳፍኔም ቢሆን
"ገላ - ሞት ቢመጣ አልፈራም
"ገላ - እያልኩ ስጠራሽ

"ገላ - የኔ አካል ለምለም፤" አባቴ

"ጽድቁ ቀርቶ በቅጡ በኮነነኝ አለ አሉ::" እናቴ

"ለምለም ሙች! ፍቅራችንን!..."

"እንዴ ኧረ ምን ነካው ሰውየው" እናቴ

"እ...አውቃ!" .... እኔ

አንዳንድ ጊዜ የሚያስቁ የዘፈን ገድሎቹን ይተርከላታል::

"እናልሽ እኛ ራሳችንን የምናየው እንደ ንጉስ ባንድ ነው:: በእርግጥም ደግሞ ንጉሱ ለእኛ ያደላሉ:: ጭንቅ ጥበብ ሆነ:: ኮሎኔል 'ይቺን፤ የዛሬን ልጆች ከጉድ አውጡኝ፤ ንጉስ ውድድሩ ላይ ይገኛሉ እሉ ልዕልቷም ይመጣሉ ይሉናል::

ሌት ተቀን ልምምዳችን ቀጠለ:: አይደርስ የለም ቀኑ ደረሰ:: ሁላችንም በልምምድ አካላችንን ጨርሰን ከስተናል:: ኮሎኔል አስሬ ነው ስማችንን የሚጠሩት::



t.me/OLDBOOKSPDF

እናልሽ የእኛ ተራ ደርሶ መድረክ ላይ ልንወጣ ስንዘጋጅ አስር አሊቃ ባዶላ ሰማይ ይውጣ መሬት ይግባ ይጠፋብናል:: ዋናው የትሮምቦን ተጫዋች! ከሁላችንም የኮሎኔልማ ምን ይነገራል:: ብንወጣ ብንወርድ የት ይገኝ? በኋላ ቢቸግረኝ አንድ ሃሳብ አቀረብኩ:: ኮሎኔሉ መጀመሪያ ተቃወሙ፣ በኋላ ግን ያለ ትሮምቦን እንደማይሆን ሲገባቸው ይሁን አሉ:: ቶሎ አልጋና አትክልተኛችን ቤት ሾፌር ላክን:: አፍታም ሳይቆይ እያከታለፈ አመጣቸው::"

"ምን ልታደርጉ?" እናቴ ከዚህ በፊት የሰማችው ቢሆንም.....

"ልነግርሽ አይደል፣ እኚህ አትክልተኛ ጥንት የጣሊያን አሽከር የነበሩ በየሚጓዳው ሲፈሱ የማያፍሩ ነበሩ:: ዘፈኑን አስጠንቻቸው ትሮምቦኑን ተከተው እንዲፈሱ:: ከመድረክ ጀርባ ድምፅ ማጉያውን ብሽሽታቸው ስር ደቅኜ 'አሁን' ስላቸው 'ጠረር' ያደርጋሉ:: ይገርምሻል ግሩም ሆኖ የትሮምቦኑ ክፍተት በፈስ ተተካ"

"አቤት አንተ" ...እናቴ እየሳቀች::

"ፍቅራችንን! እንደውም ቢስ ተባለ::

"አትክልተኛው ቢስ ሲባል ተስፋ ቆርጠው ነበር፡፡ ይኼ የእናት ክፍላችን ሞት ሽረት መሆኑን ነግሬ አበረታታኋቸው:: ተወጡት! አቤት ያኔ የነበረ የኮሎኔል ደስታ:: እዚያ መድረክ ላይ የተቀረፀው በፈስ የታጀበ ዘፈን አሁንም በሬድዮ ይተላለፋል!"

"ካ-ካ-ካ-ካ-ካ...." - እናቴ

"ያን የመሰለ ጊዜ አለፈ..." - አባቴ

"አንቺ ለምለም" - እኔ

"ተነሳበት ልጅሁ! ሰው ደስ ሲለው አይወድ" - እናቴ

"ጹፍ!" ይላል ጆንያው በእልህ እደግመዋለሁ:: አንዳንዴም ጋጠወጥ ተጣጥፎ የቀረበልኝ ያህል በማሰብ ጨከን እያልኩ በበቀል ስኬት እረካለሁ:: የት አባቱ!!

እናቴ ድንገት ከቤት ስትወጣ ጀርባዬ ይነግረኛል::



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴ? እንዴ? እንዴ?" ስትል በአይኗ ስትል ይሰማኛል፡፡ ስሆር አልተሳሳትኩም፡፡ አቧራ መቃሚ ያናደዳትም ያስገረማትም ትመስላለች፡፡ ገዳፋው ጋንጩር እጠገቧ ቆሞ ፈገግ እንዳለ ያየኛል፡፡

"በቆምህ አቧራ ትጠጣለህ?" እናቴ

"እቤት እንዳይገባ ነው፡፡" ለጊዜው የመጣልኝን ሰበብ፡፡ አይኖቼ ጋንጩር ላይ እንደተሰኩ፤ መንቀል ተሳነኝ፡፡ ሽንፈት ተሰማኝ፡፡

እናቴ አይኔን ተከትላ ጋንጩርን አየችው፡፡ ሁኔታው ደስ ያሰኛት አትመስልም፡፡ በሀዘን ልትከሰኝ እየሞከረች "ተወው አሁን ግባና ታጠብ" አለችኝ፡፡

ሀዘኔታዋን ሳገኝ ሆድ ብሶኝ አለቀስኩ፡፡ እናቴ ምንም አስተያየት ሳትሰጥ አየችኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

የመጣበት እግሩ ውሃ የማይዘልቀው የተቀቀለ እንጨት ይመስላል:: ከቁምጣ እፍ ውስጥ ብቅ ያለ እግሩን ባየሁ ቁጥር የባላገር ልጅነት ይሰማኛል::

መልስ ሳልሰጠው ወደ ውስጥ ገባሁ:: ድምጹን ከፍ አድርጎ ተናገረ::

"እኔም ከነካኸኝ አለቅህም!"

ስወጣ ግን የለም:: የታች ሠፈር ልጆች አንዳች የነገር ፍለጋ ትርምስ ውስጥ እንዳሉ እየተሰማኝ ነው:: ከዚህ በፊት ከሁሉም ጋር በየተራ ተደባድቢ የአባቴን የድብድብ ምክር ተግብሬባቸዋለሁ:: በፊት ድብድብ እንደ ጋሽ ድንቁ ታማሎ መጣል ይመስለኝ ነበር:: ለመጣል ስታገል በሚያርፍብኝ ቡጢ ቀድሜ መውደቁንና መሸነፉን ልምድ አደረኩ:: አባቴ ይኼን አይነት ተከታታይ ምክሩን ይለግሰኝ ጀመር::

"ተደባዳቢህ እራሱ ይውደቅ እንጂ ለመጣል ብለህ አትግጠመው:: በዱላ ያልደከመ ብትጥለው እንኳን ይገለብጥሃል::"

"እሺ"

"ድብድብ የፍጥነት እንጂ የጉልበት ጉዳይ አይደለም:: በከስና ቴስታህ ፍጥነት ካላቸው ማንም አይቋቋምህም::"

"እሺ"

"ለፀብ የመጣን ሰው በመታገስ ለማለዘብና ፀብን ለማስቀረት አትሞክር:: ፀቡን ዛሬ ብታስቀር እንኳን ቆይቶ መምጣቱ አይቀርም::"

"እሺ"

"ምትህን በፍፁም አታቋርጥ፣ ማጣደፍ::" እጁን ለቦክስ ምት አየር ላይ ሰነዘረ፤ በማንባሩ ጨመረበት።

"እሺ"

አባቴ ያለው ሁሉ ትክክል ነበር:: ከእኩዮቼ የሚችለኝ ጠፋ:: የማያውቁትንና የማይማሩትን የድብድብ ስልት ተገበርኩባቸው:: የሚገርመው አሁንም የሚያውቁት በቴስታ የምመታቸው በግንባሬ እንደሆነ ነው:: የሚመታው


t.me/OLDBOOKSPDF

"ስንጥር የለም::"

"ከእነ ድንቁ አጥር ላይ ቅጠል አምጣ"

"ቢያዩኝስ?"

"ይይሃ!"

"እኔ እንደሆነ ፓስቲ ብበላ ይሻለኛል" እለዋለሁ::

"አሁንም?"

"አዎ"

"ምን ቸገረኝ" ፓስቲ::

አዋዝቼ ወደ ውጭ ልወጣ ስል "ወዴት ነው ?" አለኝ::

"እዚሁ ነኝ::"

"ቁርስ በላህ እንዴ?"

"አይ"

"ቆይ ፓስቲ እገዛልሃለሁ:: ከዛ በፊት ግን እዚህ አልጋ ስር ገብተህ የምታወጣልኝ እቃ አለ::"

"ምን? ጫማ ነው?"

"አይደለም:: በከረጢት ከታ እናትህ እዚያ የወረወረችው ጊታር እንዴት እንደሆነ ማየት እፈልጋለሁ:: ደሞ እንዳትነግራት:: ቆይና ቀስ ብለህ መቼም ይሄ አልጋ ሥር ያልተከተተበት የለም..."

እውነትም የሳሎናችንን እዳ የተሸከመው አልጋ ሥራችን ነው:: በሳፋ የእኔ የእናቴና የአባቴ ጫማዎች ተሞልተው ተቀምጠዋል:: የሚደረጉ፣ የጠበቡ፣ የተቀደዱ፣ ዘመን ያለፈባቸው ... ብዙ ጫማዎች:: ልብሶችም በተመሳሳይ እንዲሁ በማዳበሪያ እየተሞሉ ተጥለዋል::

"አቀማመጡን ልብ እያልክ፤ በኋላ ለመመለስ" አለኝ::

አባቴ ሥጋቱ እናቴ ጊታር ማውጣታችንን እንዳታውቅ ማድረግ ነው:: አቤት ሥጋት! እንገቱ የሚሸመቀቅ ቀረጢት አገኘቼ ከብዙ ኮተቶች ስር ጎተትኩት::


t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን አይነት ይሻልሃል፡፡ አሃሃሃሃ... ቢንጎ ብርቱካን ይሁንልህ? ካናዳ ድራይ ይሻልሃል? አሃሃሃሃሃ....የኔ ዘበናይ አረንቻታ አማረህ? አንተ አረንቻት ጠጥተህ ጠላውን በአንኮላ ማን ሊልፈው ነው? አሃሃሃሃ....."

ቦላሌ ሱሪ ጠየቁ ተብለን እናስገርማለን፡፡

"አሃሃሃሃ...እ? ቦላሌ? ቢራቢሮ ሸሚዝስ፤ አትፈልግም? ሀራምቤ ሸሚዝ ይሻልሃል? አሃሃሃሃሃ.....አየሽልኝ የዚህን ልጅ ጉድ? ቦላሌ ግዛ እኮ ነው የሚለው..."

እዚህ መካከል የከተሜ ንቃት ያለው አባቴ ብቻ ነው፡፡ ሳንባ፣ ቴዊስት፣ ቡጊቡጊ....ይደንሳል፡፡ ያፏጫል፣ ፀጉሩን ኤልቪስ ፕሪስሊ ይቆረጣል፣ ጊታር ይጫወታል፡፡ ከሁሉም በላይ እኔን ለስላሳ ያጠጣል፡፡

"ለስላሳ ልጋብዝህ?" ይለኛል፡፡ እናቴ ሞጃ ስትሄድ "የትኛውን አይነት መጠጣት ትፈልጋለህ? አይ ቢንጎ ብርቱካን የሴቶች ነው፡፡ ካናዳ ድራይ ይሻልሃል፡፡ አየሩ ልብህ ላይ ሲቆም ወንድነት ይሰማሃል "ቧ" ስታደርገው እንደ አንበሳ ያገሳህ ይመስልሃል፡፡"



t.me/OLDBOOKSPDF

# ሰምንት

ጭልጥ አድርጎ ከወሰደኝ ሃሳብ ያናጠበኝ የጎጋንጪር አጥር በር ነበር:: የቆርቆሮው በር እናቱ ላይ አሞራ ከንፍ ትንሽ ጣሪያ እንደባርኔጣ ደፍቷል:: አንዳንድ ጊዜ ዝናብ ሲጥል እኔና ጋንጪር ካልተጣላን እዚህ የአጥሩ ባርኔጣ ስር ተጠልለን ማዶ ማዶውን እያየን እናወራለን፤ አዳላጦት በወደቀ እንስቃለን::

የአጥሩን በር ሰበው የወጡት የጋንጪር እናትና እህቱ ነበሩ:: እናትየው ጥርሳቸውን የአርበኛ ፀጉር አስመስለው አንጨፍርረዋል:: ማናሉ ደግሞ ችፍርግ ፀጉሯን 'አምፖሎ' ለመስራት ተፍጨርጭራለች:: አባቴ የያዘውን አይነት ዘንቢል አንጠልጥላ ከእናቷ ኋላ ትከተላለች:: የጋንጪር እናት ሲያዩኝ የተነፈሰ ከንፈር መጠጣ አስቀደሙ::

"ሹሹ አፈር ይብላኝ፤ ተሻለህና ወጣህ? ሹሹ አይዞህ፤ መልሼም ሳላይህ ሹሹ፤ ታዲያ እዚህ ብቻህን ምን ታደርጋለህ? እ? ነው? ሹሹ አፈር ይብላኝ" የተከናነቡትን ነጠላ ሰርሰረው አበባ ቀሚሳቸው አንገትጌ ውስጥ እጃቸውን ሰደዱ:: የተሰደደው እጅ መሃረብ ይዞ ወጣ:: መሃረቡ መአዘን ላይ በወፍራሙ ተቋጥሯል:: ፈትተው ድፍን አስር ሳንቲም ሰጡኝ::

"ሹሹ አፈር ይብላኝ፤ ልጆች ፈልግና ከእነሱ ጋር ተጫወት ወይም ወደ ቤትህ ግባ ሹሹ" መንገዳቸውን ቀጠሉ::

ማናሉን በፍርሃት አየኋት:: ፊቷ ላይ ሀዘን ሳይሆን ቀልድ ወይም ፌዝ ያነበብኩ መሰለኝ:: እንደ እናቷ 'ሹሹ' የሚል ችፍርግ ፀጉሯን ብነጫት በወደድኩ ነበር:: የእናቷ አይነት ደቃቅ አበባ የተበተነበት ቀሚስ ለብሳለች:: በቆዳ ጫማ ሞድ የተሰራ አጭበርባሪ ኮንጎ አድርጋለች:: እግሯ በሚያጥወለውል ሁኔታ ቅባት ተለቅልቋል::

"አይዞህ" አለችኝ አፏን በፌዝ አሞጥሙጣ

t.me/OLDBOOKSPDF

ነገሩ የሁለት ቀን ጥንስስ ብቻ እንዳልሆነ ገባኝ:: በተናጠል ስላልቻሉኝ ተደራጅተው...... የማደርገው ጠፍቶኝ ግራ እንደተጋባሁ ጋንጩር ከአጠገቢ ቱር ብሎ ተፈተለከ:: የቀበናን ዳገት ከሙቼው እንደወጣ እንጃ!! መጀመሪያ ጋንጩር ለራሱ ፈርቶ መስሎኝ ነበር:: ግን እንዳልሆነ በነ ጋሙዳ መረበሽ አወቅኩ:: ገም ብሎ ቆመ::

"ጋንጩሬ" አለ ጋሙዳው "እኛ እኮ ላንቺ ብለን ነው። እያሳሳቀ ቀበና ወንዝ ሊጨምርሽ ነበር::"

"ይጨምረኝ!" አለ ጋንጩር

የሲንጢ ተዋጊ አይን ዶለዶመ:: ቀጮ ማቅብቆቧ ከሸፎ ግራ መጋባት ተረከባት:: ሙቴ የተማመነበት ድል ከእነ ጋሙዳ እጅ ስለወጣ የመሃል ሠፋሪ ለሚት ከወዲያ ወዲህ አላጋት::

"ጋንጩሬ፣ አይደብርሽም እንዴ?" ጋሙዳ ነበር::

"ከፈለጋችሁ አንድ ለአንድ" አለ ጋንጩር

"እሺ አንተ እዚህ ና፣ አንድ በአንድ በፊትም ያሰብነው ነው" አለ ቀጮ

"አልመጣም:: በአድማ ልደብድብ ብትሉ ሁለት ሁለቴ እፈነክታችኋለሁ::" ጋንጩር እኔ ላይ አተኩሮ "ትችላቸዋለህ?" አለኝ::

"ይምጡ" አልኩ:: ወዲያውኑ ጋሙዳው ፊት ላይ ሹፈት አየሁ:: "መጀመሪያ ጋሙዳው ይምጣልኝ፣ ከዚያ ቀጮ" ሙቴና ሲንጢ ገና ሳልደዛቸው እንደሚያለቅሱ አውቃለሁ::

"ቀጥሉ" አለ ጋንጩር

ጋሙዳ እንደ ጋሽ ድንቁ ለድብድብ ይዘጋጃል ብዬ ሳስብ የያዘውን እንጨት ጥሎ በጭብጡ ጆሮ ግንዴ ላይ ብሎ ጣለኝ:: ሁሉም ሳቁ:: ጋሙዳ የእሱ ግዳይ እንደሆንኩ ቆጥሮ ድብድቡን ከመቀጠል ይልቅ ጋንጩርን አናገረ::

"ስላሸንፍን አትፈነክቺንም አይደል?"

"አልነካችሁም" አለ ጋንጩር ድምፁ ላይ ስለኔ ፍርሃት ያደረበት እንደሆነ ያስታውቃል:: "በቃኝ ካለ ግን በቃ!"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ይምጣ" አለ ሙቄ አንባውን እየጠረገ::

"ቀሙስ?"

"ከነካኝ አለቀውም::"

"በሉ ይዋጣላችሁ::"

ዞር ብዬ ጋሙዳን አየሁት:: ያፈነደደበት ቦታ በጎኑ ፍንግል ብሏል:: እጆቹ ፊቱ ላይ ናቸው በየጣቶቹ መካከል ደሙ ይንጨፈጨፋል:: አላዘንኩለትም:: እግሬንና መንገጭላዬን እያሻሸሁ ህመሜን ባስተናግድ እወድ ነበር:: እነ ቀጮ ፊት ግን ይኼን ማድረግ አልፈለኩምና ተውኩት::

ሙቄና ቀጮ ከእኔ ጋር ከመደባደብ ለመሸሽ ሲሉ እርስ በእርስ ተናረቱ:: ዳር ሆኜ ሳያቸው የድብድባቸው ፍጥነት እኔ የምቋቋመው ሆኖ አልታየኝም:: የእኔን ድብድብ ዳር ሆኜ የማየት ዕድል አልገጠመኝማ:: ሴንጢን እየኋት አይኗ ይሸሸኛል:: ሙቄና ቀጮ እኩል ፍጥነትና ጉልበት ስላላቸው ከፉኛ ተቀጣቀጡ:: ሁለቱም ደምተዋል:: በመጨረሻ እቧራ ላይ መንደባለል ብቻ ቻሉ::

"በቃ" አለ አዋጊያችን ጋንጩር "አሁን ደግሞ ሴንጢ"

"እኔ አልደባደብም!"

"ካልተደባደብሽ ትደበደቢያለሽ" ጋንጩር ፍርድ ሰጠ::

"በእናታችሁ፣ በእናታችሁ"

"ምን ትቀጣ?" ጋንጩር ጠየቀኝ::

"እግሬን ይሳም፣ ከዛ አዝሎኝ ሠፈር ያድርሰኝ" አልኩ::

"እሺ" አለ ሴንጢ

ሴንጢ ደስ እያላት እግሬን ሳመች:: የድል መልስ በቅሎዬም ሆነች:: ጋንጩር የሰርጡን አፋፍ ሳይለቅ፣ እኛ የወንዙን ዳር ይዘን እንደተዛዘልን ስንሄድ እያየን ወደ ሠፈር ተመለስን:: ህመምተኛ እግሬን በእንዲህ ያለ ሁኔታ አሳረፍኩት::

t.me/OLDBOOKSPDF

# ዘጠኝ

"ሰላም! ኧረ ሰላም! ቤቶች! ሰው የለም?"

በድምፃቸው የጋሙዳ እናት እንደሆኑ አውቄያለሁ። ብርድ ልብሱን ተከናንቤ ዝም አልኩ። አባቴ የእናቴን ስም ሲሰማ እንደመባተት ብሎ ተነሳ፤ በደመነፍስ ጊታሩን አስገድፎ ካቆመበት ግድግዳ ላይ አነሳ። ትንሽ ተርበትብቶ እናቴን ሰው እንደፈለጋት አረጋገጠ መሰለኝ አልጋው ላይ ቁጭ ብሎ ፐሪስሊውን ደፋ።

"ሰላም! ቤቶች!"

የጋሙዳ እናት ገግመዋል። አባቴ የሌሊት ቱታውን እንዳደረገ ወጥቶ አናገራቸው። ጋንጩር እኔ አልጋ ላይ እንደተኛ ከጭንቅላቱ ቀና ብሎ አየኝ። እንደማየው ሲያረጋግጥ "ጋሙዳ ሞተ!" አለኝ።

ልቤ ትርትር አለች። ንፁህን ድንገት ሳገኛት እንኳን እንዲህ አልሆንኩም። ጋንጩር ድንጋጤዬን አይቶ ከት ብሎ ሳቀ።

"አንተ ልጅ፤ ተው ግን ከእኔ ጋር?" አልኩ ከልቤ ተናድጄ።

ድምፁ እንዳይሰማ አፉን አፍኖ ሳቁን ጨረሰ።

የጋሙዳ እናት ለአባቴ አቤቱታቸውን አሰሙ።

"እዚህ ተወልዶ ያደገ ነው። እነሱ አብረው የሚደበድቡት ከየት የመጣ ባይተዋር ማድረጋቸው ነው? የእሱ አባት ከማንም በላይ ጥጋበኛ ነበር፤ ትናንት ሞቶ ዛሬ የእሱን ልጅ በአባታቸው የሚመኩ ይምቱት? ኧረ እግዚአብሔርን ቀና ብሎ ማየት ደግ ነው። ጉልበት የእሱ የፈጣሪ መሆኑን ማስታወስ ይገባል። የጋንጩር መፍትሔው ቀላል ነው። ብቻ አንተ ልጅህን ያዝልኝ። ፊት ፊቱን ብለው ሲጥሉት ቢሞትስ? ወንድ ከሆኑ ለየብቻ አይገጥሙትም? ምድረ ላንቃሳ ሁሉ፤ በልተው የሚያድሩ አይመስሉ..."



t.me/OLDBOOKSPDF

የጋሙዳ እናት ድምፅ እየራቀ ሄደ:: አባቴ ምንም ሳይመልስ አዳምጦ መጣ:: ድንጋጤው የለቀቀው አይመስልም::

"ምን ታደፍጣላችሁ? ለምንድን ነው አንድ ልጅ ለሁለት የምትደበድቡት?" በራሱ ድንጋጤ የተናደደውን በእኛ ሊያሳብብ እንደሆነ ገባኝ::

"ኧረ እኔ ብቻ ነኝ የመታሁት" አልኩ::

"እሱ ብቻ ነው፣ እኔ እራቅ ብዬ ነበር:: እንደውም አለቀረብኩም" አለ ጋንጩር

"አንድ ሰው ለሁለት ይደበደባል? ብቻ ለብቻ ገጥሞ ከቻሉ መምታት፣ ካልቻሉ መመታት'ጂ ለሁለት አንድ ሰው መምታት የውርደት ውርደት ነው::" አባቴ እኛን መስማት የፈለገ አይመስልም:: እኔ ዝም ስል ጋንጩር ያብራራለት ጀመር::

"አይደለም፣ እንደውም እነሱ ናቸው ለአምስት ሊደበድቡን የመጡት በኋላ..."

"እኮ እናንተ ደግሞ እሱን ጠብቃችሁ ለሁለት..." ጭራሽ ንዴቱ ብሶ ቀበቶውን አውልቆ ካስቀመጠው ሱሪው ላይ መፍታት ጀመረ::

"ኧረ አይደለም! አይደለም!" ጋንጩር ተግለበለበ:: እኔ ግን አባቴ እንደማይመታን አውቃለሁ:: ዝም ብዬ እየው ጀመር:: እንደውም ሳቁ መጣ::

"አንድ ሰው ተባብሮ መውረር የጉንዳን እንጂ የሰው ልጅ ተግባር አይደለም:: ጉንዳኖች!" ቀበቶውን ከፈታ በኋላ እጁ ላይ ቸብ ቸብ አድርጎ መልሶ ወረወረው::

ጋንጩር ግድግዳው ላይ ተለጥፎ ቁና ቁና ይተነፍሳል::

"የታባታችሁ፣ ሂዱና አሁን ቁርሳችሁን ፓስቴ ግዙ:: ደሞ ተባብራችሁ ሰው ደብድቡና አፈር አገባችኋለሁ::" አንድ ብር አውጥቶ ወደ ጋንጩር አቅጣጫ ወረወረ::

"ላንተም እንግዛልህ?" አልኩት::

"ለራሳችሁ ብቻ፣ ሻይ እዛው ብትጠጡ ይሻላል ወይስ እዚህ ታፈሉ?"

"ሻይ እንፈልግም?" አልኩ::

t.me/OLDBOOKSPDF

"ደግ" ሱሪውን አንስቶ ያለ አንድ ሙያ የፈታውን ቀበቶውን ሱሪው ውስጥ መወሰወስ ጀመረ:: ጋንጩርን አከታልፈ, ይገፍው ወጣሁ:: የትናንቱ እግሬ የተናጋ አጥንት ሳይኖረው አይቀርም:: ያስነከሰኝ ጀመር::

ገና ወገግ ማለቱ ነው:: ሚዳውን አቋርጠን እንዳንሄድ የጋሙዳን እናት ስለፈራን በእነ ጋንጩር ጓሮ አድርገን ዳር ዳሩን ወደ ሚስማር ፋብሪካ ተሻገርን:: ወዲያውም እግሬን ለማሳረፍ ሻይ ቤት ውስጥ ጥቂት አረፍ አልን:: የሻይ ቤቱ ባለቤት ጫት በአፉ እየጨቀጨቀ በማይታወቅ ቋንቋ ቅልቅል ይጮሃል::

"ዋሂድ ሻይ!!"

"አርቢን ፓስቲ!"

"ፋሪቅ-እማት!"

ፉል ያወለድ!"

"እማት ስልስ!"

ቀስ ተብሎ የታዘዘውን ያስተጋባል:: አራሱ የሚያቀርበውን ብስኩትና ዳቦ ጭምር ጮሆ ይናገራል::

በእስር፣ በእስር ሳንቲም ጭንቅላታችንን የሚያካክል ብስኩት ገዝተን እንዳመጣጣችን ወደ ሠፈር አመራን:: በእነ ጋንጩር ጓሮ ብቅ ስንል ጭርታው በስጋት የሚያምስ አይነት ሆነብን:: የጉድጓድ ውሃውን ደፍ ተደግፈን በጋዜጣ የተጠቀለለ ብስኩታችንን ልንገምጥ ስንል ከየት እንደመጣ ልብ ያላልነው ድምፅ ባረቀብን::

"ወጋሁ!"

ከው ብለን ቀረን:: ጋሙዳው ነበር፤ ከበስተጀርባችን ብቅ አለ:: ፊቱ ከማኮፍኮፉ በተጨማሪ ወፍራም የጥቁር ጤፍ ሙቅ የተደፋበት መስሏል:: አንዳንድ አራራ መሳይ መጠጥ ያሉ ቁስል ደሴቶች ፈንጠቅጠቅ ብለው ይታያሉ:: ከምኒው እንዲህ ተፈጣጥሞ እንደጠበቀን እንጃ::

"ወጋሁ!" በተድፎነፎኑ አይኖቹ ብስኩታችን ላይ አጨንቁሮ "አንተንም ወጋሁ!!" ጋንጩርን ነበር::


t.me/OLDBOOKSPDF

ትምህርት ቤት ስንገባ፣ ከክፍል ስንለቀቅ...የተደበቀ ጓደኞችንን አይተን "ሳንጌታ" እንለዋለን ቀድመን፤ ካልሆነ መደለታችን ነው።

ከእነዚህ የስምምነት ጨዋታዎች ውጪ የተንኮል ጨዋታዎችም ነበሩ። ለምሳሌ ቀይ ሸክላ አኩል ገምሰን ከድንጋይ ጋር በመፈተግ እናድቦለቡለዋለን። ከዚያ በካልሲ ውስጥ ከተን የጨርቅ ኳስ በማስመሰል ተደብቀን እናንከባለውና "ኳስ፣ ኳስ" እንላለን። አንዳንድ ልጆች ኳስ ያገኙ መስሏቸው ባለ በሌለ ኃይላቸው ያንን ሸክላ ይጠልዛሉ። ቁጭ...የእግራቸው ጣቶች በመደዳ ይታጨዳሉ።

ሹሌ (እርግጫ) ተቧድኖ የጎል ጦርነት (አመድ በላስቲክ ሞልተን እንደ ቦንብ እየወረወርን አካባቢው ሲታፈን በጓል የምንወረውረው የአንዳንድ ተንኮለኞች ልጆች ድንጋይ በጭቃ አድቦልቡለው ይማታሉ።

አባሮሽ፣ ቃጤ፣ ዲሞ...ይኸ ሁሉ ጨዋታ የልጅነት ዘመናችንን ድብልቅልቁን ያወጣዋል።

* * *

ከትንሽ ጨዋታ በኋላ ጋሙዳ ፍፁም ነፃ ሆኖ በሙሉ ልብ ይጫወት ጀመር።

"....አንድ ቀን ደም ቀጮ እናቱ ዳቦ ሲጋግሩ ማድቤት ቁጭ ብሎ እስኪበስል ይጠብቃል። የመጀመሪያው ጢቢኛ በስሎ ሲገለበጥ ሁሉ እዛው ነበርኩ። ልክ ከእናቱ ተቀብሎ ከማድ ቤቱ "እፍ እፍ" እያለ እያበረደው ሲወጣ 'ወጋሁ!' አልኩታ እሃሃሃ...."

የጋሙዳ ገድል "በወጋሁ" የተሞላ ነው። ቀስ በቀስ ፀፀቱም ፍርሃቱም እየለቀቀኝ ሄደ። ከኋላችን ቀረት ሲል እጠነቀቀዋለሁ። ወደ ግንፍሌ ወንዝ ወርደን ጋንጩር ግራ እጁን መወርወር ሲያለማምድ እየነው። ሁሉም ነገር እንደቀድሞው ሰሜት አለሰጥ አለኝ። ቤቴ ሄጄ በጋንጩር የተነጠቅሁት ድንክ አልጋ ላይ ብተኛ ወደድኩ።

"ዋንዛው አፍርቷል ሄደን እንልቀም" አለኝ ጋሙዳ



t.me/OLDBOOKSPDF

ብዙም ሳይቆይ በዜማው ንብርብር ላይ አንዳንድ ቃላት በስሱ ፈሰሱ:: ቃላቶቹ ከዜማው ጋር ሳይኳረፉ ሰርገው የሚያደርሱት መሰለኝ:: አባቴ ከምሳጢው ተናጥቦ ወደ እነ ጋንጩር ግቢ ውስጥ አሾልቆ መልከት አደረገ:: ጊታሩ ከቀድሞ በበለጠ ወኔ ዜማ ያዘንብ ጀመር:: የሰማየ ሰማያቱ ድምፅ ከላይ ሳይሆን ከማናሉ እንደሚፈልቅ ገባኝ::

"ከተራራው ወዲያ፣
- ናፍቆቴ
ከደመናው ውስጥ፣
- ናፍቆቴ
አንተን ያየሁ መስሎኝ፣
- ናፍቆቴ
ልቤ ሲል ድንግጥ!"

አይኖቼን ጨፍኜ ግድግዳውን በጀርባዬ ተደግፌ ቆምኩ:: ከዚያም ሳላስበው እየተንሸራተትኩ ተቀመጥኩ:: ማናሉ የዐጉርሽን ሸካራነት በዚህ አለስልሰሽው ተብላ ድምጿ ተሰጥቷታል:: ያንኑ አዝማች እየደጋገመች ቢሆንም አይሰለችም:: ጥቂት እንዲሁ እንደቆየች አባቴ "ናፍቆቴ" የሚለውን እያስገባ ያግዛት ጀመር:: ሌላ ጣዕም ተወለደ:: ወፍራሙ የአባቴ ድምፅ ጆሮ ላይ በልድልዱ ይንቆረቆራል:: ቆየት ብሎ አዝማቹን በኃይል ሳይሆን አለስልሶ ተቀበላት:: "ናፍቆቴ" የሚለውን ማጀቢያ ማናሉ ተረከበች::

"በመንገድ ላይ ስሄድ" (አባቴ)
"ናፍቆቴ" (ማናሉ)
"ብዙ ሰው ሲመጣ" (አባቴ)
"ናፍቆቴ" (ማናሉ)
"አንቺን ያየሁ መስሎኝ" (አባቴ)
ናፍቆቴ" (ማናሉ)
"አይ ያየሁት ጣጣ" (አባቴ)
"አልጋ ላይ ተኝቼ - ናፍቆቴ"
"እንቅልፍ አልወስድ ቢለኝ - ናፍቆቴ"
"ጨለማውን ጥሰሽ - ናፍቆቴ"


t.me/OLDBOOKSPDF

ይለማተዋል:: "ዛሬ የበላሁት እንዴት ይጣፍጣል፣ ሽታውን እንኳን አያችሁትን" ይላል:: ጋሙዳው እንዲህ ሲያደርግ ሊያስመልሰኝ ይቃጣኛል:: እጠላዋለሁ:: ዛሬ ግን ይሄን ዘዴ ቢያውሰኝ ወደድኩ...

ከጥጋብ በኋላ ጋንጩርን ፍለጋ ስሄድ እህቱ በር ላይ ቆማ አየኋት:: ለንፁህ የማሳየው መሽቆጥቆጥ መጣብኝ:: አሸዋ ውስጥ እንደተሻጠ አካፋ ሲበጠር ሽቅ-ሽቅ-ሽቅ የሚለው ፀጉሯን በእናቷ ሻሽ ሸብ አድርጋዋለች:: ስታየኝ ዐይኗ ላይ ጥላቻ አነበብኩ::

"የእናቱ ቢጤ ማሽንክ" አለችኝ::

ማሽንክ ምን ማለት እንደሆን አላወቅኩም:: ይሁንና መጥፎ እንደሆነ ከገለፃዋ ተረድቻለሁ:: ትክ ብዬ አየኋት::

"ምስጦች!!" አለች እኔና እናቴን ደርባ መሆን አለበት:: ለምን እንደሆነ በማይገባኝ አኳኋን ምን ያህል የምወዳቸውና የማከብራቸው ቢሆንም ሲነኩብኝ መታገስ አይሆንልኝም::

"ሹ-ሹ..." አልኳት እንደ እናቷ ጥርሴን አግጥጬ:: ድንጋይ ልታነሳ ስትል ሸሽሁና የውሃው ጉድጓድ ጋ ቆምኩ:: እንዳትመታኝ ለመጠንቀቅ የምከረች በሚያስመስላት አኳኋን ወረወረችብኝ:: ድምጼ ባይሰማም ጥርሴን አግጥጬ "ሹ-ሹ.." አልኳት::

"ማሽንኮች" አለች::

ይኼ ማሽንክ ምንድን ነው? የማይታገሱት ስድብ ቢሆንስ? የእውነት ተናደድኩ:: ሴቶች እንደሆን ከትንሽ እስከ ትልቅ የሚመቱ አይደሉም:: አንዳንድ ባሎች ሲማቱ ካየ አባቴ ቱግ ብሎ ያለእናቴ ፈቃድ ሊደባደብ ይቃጣዋል:: ስለዚህ ሴቶችን መሸሽና ማብሸቅ እንጂ አንዴ ከተያዝኩ በኋላ እንደ ጋንጩር ዝም ብሎ መደብደብ እንደሆነ ይሰማኛል::

ማናሉን ለዚህ ስድቧ ምላሽ የሚሆን ነገር ሳፈላልግ ሽሮዋ ትዝ አለኝ:: እያየችኝ ጣቴን ወደ አፌ ከትቼ ለማስመለስ ስታገል ማናሉ ላለማየት ዐይኗን በእጇ ከልላ ወደ ግቢው ውስጥ ሸሸች::



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጎሽ! ጎሽ! ሰደበኝ::" አፈሩንም ቅጠሉንም ከመሬት ቧጠጡ

እየሸሸሁ "እኔም አይቼዎታለሁ ተደብቀው የባኛን ቂጥ ሲመለከቱ" አልኩ:: ከመብሸቅ ይልቅ ሳቁ:: የበለጠ በገንኩ:: የሚመስል ነገር እንዳልተናገርኩ ገባኝ:: እጅግም ሳላስብበት የተናገርኩት ግን የጋሙዳን እናት እንደ ኮረንቲ ያዛቸው

"ሰው ሁሉ አንዛ ገበያ ሲሄድ፣ እማማ ይጋርዱም ሲሄዱ እርስዎ ባኝ ቤት ተደብቀው ሲገቡ አይቼዎታለሁ"

"እ?"

"እ-ዎ ሚካኤልን!!"

"አንተ ማሽንክ" ይቺ ስድብ ተደገመች:: ዞር ዞር እያሉ አካባቢያቸውን አዩ:: ያፈሱትን አመድና ቅጠል እየበተኑ "መቼም አታድግ" አሉኝ::

የጋሙዳን እናት እንዲህ ተገላገልኳቸው:: የባሰብኝ ግን የገዛ ጓደኞቼ ተደብቀው "ይጋሩዱ ቂጦ" የሚሉኝ ማብሸቂያቸው ነው:: "ይጋርዱ ቂጦ" ማንን ከማን እንደምለይ ግራ ገባኝ:: ለወትሮው የጓደኞቼን ሁሉ ድምፅ እለይ ነበር:: አሁን ግን የሚያበሽቁኝ ድምፃቸውን እየለዋወጡ ነው:: እንደ ፍየል እያንቀጠቀጡ እንደ በግ እያወፈሩ እንደ ዶሮ እያኮኮሉ...

ወሬው እማማ ይጋርዱ ጆሮ ደረሰ:: አልተቆጡም:: እንደውም እየሳቁ "የቢላዋና የወንድ ትንሽ የለውም:: ሁለቱም የሰባ የሰባውን ይወዳሉ" አሉ:: መንገድ ላይ ሲያገኙኝ ባኝ አጠገባቸው ከሌሉ "ባሌ ሲታየኝ መጣህ? ና!" ይሉኛል እየሳቁ::

በማልከላከለው ደረጃ የግንፍሌዎች መሳቂያ ሆንኩ:: ሁኔታዬን የሚረዳ፣ ንግግሬን የሚቀበል ጠፋ::

"እኔ እኮ ያየሁት ማናሉን ነው::"

"ቀጣፊ ማናሉ መች 'ላት' አላትና ነው የምታያት?"

ስመናጨር

"መጎርመስህን እኮ በይጋርዱ ቂጦ አወቅን" ይሉኛል::



t.me/OLDBOOKSPDF

አባቴ ቁና ቁና እየተነፈሰ መጥቶ አጠገቤ ተቀመጠ:: መቆናጠሩ ሳይሆን ንዴቱ ላይ ላይ እንደሚያስተነፍሰው ገብቶኛል:: ፐሪስሊውን እንደደፋ ጥቂት ቆይቶ ከድብድብ ስልት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ትልቅ ሰው አናገረኝ::

"ወሬ ተሸሽቶ የትም አይደረስ፤ አየሩ ሁሉ ወሬ አይደለም እንዴ? አየር ተሸሽቶ ወዴት? ስለዚህ አየር እንዳይኖር ከመሞከር በውስጡ መኖርን መርሳት ነው የሚበጀው:: ወሬ ታግሎ የሚጥልህ መኖሩን በሙሉ ትኩረት ስታረጋግጥለት ብቻ ነው:: ልብ በል ወደፊት እድሜ ልክህን የምትኖረው ዛሬ "ሀ" ብለህ በጀመርካት የወሬ አየር ውስጥ ነው::"

አባቴ ሌላ ሳይሆን ከተናጠል ድብድብ ወደ የጋራ ድብድብ ያደገ ስልቱን እንዳስጠናኝ የገባኝ ቆይቶ ነው:: ያኔ "አየር፤ አየር፤ አየር" ሲል የመጣልኝ የአካባቢ ሳይንስ ትምህርታችን ነበር::

"ለሰው ልጅ መኖር የሚያስፈልጉት ሦስት መሠረታዊ ነገሮች

ሀ/ ምግብ
ለ/መጠጥና
ሐ/ወሬ ቅልቅል አየር ናቸው::"


t.me/OLDBOOKSPDF

# አስራ አንድ

አባቴ በነገሬ ጣልቃ ቢገባም የማንፍሌን ሰማይና ምድር አልተማመንኩባቸውም:: ስለዚህ ሳልወጣ ቤት ውስጥ ዋልኩ:: ቤት ውስጥ እየቀረበች እና እየራቀች ስታጫውተኝ የዋለችው የጣሪያ ቀዳዳ የፈጠራት የጨረር ሳንቲም የምስራቅ አቅጣጫ ግድግዳችን ላይ ተሟላ እንደወጣች ጋሙዳ ቧሬ አፉን ከፈተ::

"መኩብብ" ሲል ተጣራ

የሴለ የመሰለኝ አባቴ "ምንድን ነው?" ሲለው ሰማሁ::

"ንፁህ ትፈልገዋለች" አለ::

ደንግጬ ቆምኩ:: እግሬ መሬቱን ወግቶ መያዝ አቃተው:: አንዳንድ ሰዎች ጉልበቴን ብርክ መታው የሚሉት ይሄን ሳይሆን አይቀርም:: እግሬ አልወጋ አለኝ አይሉም?

"የማን ናት ንፁህ?" አለ አባቴ

"እ - እ - እዛ - ቀበና - እዛ....." ጋሙዳ ተንተባተበ:: እንደ ጋሙዳ አፍ የእኔ መንፈስ ተሳሰረብኝ:: ይቺ ልጅ ተፈጥሮዬን ምን አደረገችብኝ? ስል አሰብኩ::

አባቴ የንፁህን ማንነት መጠየቁ ተገቢ እንዳልሆነ ተሰምቶት የጋሙዳን መንተባተብ አቋርጦ ወደ ቤት ገባ:: "ሰምተሃል?" አለኝ::

በጭንቅላቴ አዎ አልኩትና ተቀመጥኩ:: አባቴ በትዝብት እንደሚመለከተኝ ገብቶኛል::

"ታዲያ.....?" አለኝ በሩን እየለቀቀልኝ:: አባቴ ባጠበበው በር ወጥቼ ጋሙዳን አየሁት:: የቦካ ፊቱ መጠጥ ብሎለታል:: ድምፁን ዝቅ አድርጎ "ዋንዛ ለቅመን ስንመጣ ንፁህን በረንዳ ላይ አየናት:: ጋንጩሬ ጠራት፣ ከዛ፣ ከዛ......"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ጨለንክኩበት......እንዴት ያለሁት......ደመን......ረሃቡንስ......ውኃ እንኳን አልጠጣ......እንዴት ያለሁት ጨካኝ ነኝ!......"

ቤቱን ጠላሁት እንጂ ለእናቴ አላዘንኩም:: እሷም እንደ አባቴ መወዘቻ ውኃ ይገፍ በተቀመጥኩበት አንድ ምሽት ወጥታ ትጠፋ ይሆናል::

ግን ለምን ያኔ አባቴ ሲሄድ አልተከተልኩትም? ሲያነቅፈው እየደገፍኩ፣ ሲጠማው እያጠጣሁ ለምን እስከ ዓለም ዳርቻ አልተጓዝኩም? መቼም አንድ ቦታ አይቆምም:: ቀሪ ዘመኑ የመሄድ፣ የመጓዝ፣ ያለበትን ቦታ የመሸሽ ነው:: ዘወትር እንደ ጀንበር በምስራቅ ወጥቶ በምዕራብ የመጥለቅ ተደጋጋሚ ሂደት ውስጥ ነው:: "አባቴ!" ብዬ መሮጥህ አለኝኝ::

"የት ነው ያለኸው?"

እናቴ ከሦስት ቀን ፆምና ዝምታ በኋላ የአባቴን ሞት የተረዳች ያህል አለቀሰች:: በተጠራሞተ አኳኋን ድምጿ ፈፅሞ እስኪዘጋ ድረስ የንስሃ ሙሾ አወረደች::

"የት ወደክ? እምን ገባህ? እኔን፣ እኔን የእኔ ጌታ፣ እኔን፣ ጨካኙዋን፣ እኔን ከፉዋን፣ እኔን ከሃዲዋን" ደረቷን ደጋግማ ደሰቀች:: በጉልበቷ እየዳኸች መሬት ለመሬት አሰሰች:: ስብር፣ እምሽክ፣ ድቅቅ ከማለቷም በላይ እራሷን በማዋረድ ለራሷ የነበራትን ግምትና ክብር ተፃረረች:: አንድ ሌሊት ሙሉ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ካሳለፈች በኋላ ጠዋት የሞት ያህል የከበደ እንቅልፍ ጣላት:: ትዝ ይለኛል እኩለ ቀን ላይ ነበር የነቃችው:: እየተንገዳገደች ተነስታ እሳት አቀጣጠለች፣ በትንሽ ማሰሮ ውኃ ጥዳ ሳሎን ውስጥ ገላዋን ታጠበች:: የንስሃዋ ፍፃሜ እንደሆነ ገባኝ::



t.me/OLDBOOKSPDF

# አስራ ሁለት

ጠዋት የእናቴ የመጀመሪያ ሥራ ሰባራውን ጊታር ለመጀመሪያ ጊዜ እንስታ አልጋ ስር መከተት ነበር:: የጊታሩን እጀታ ከአልጋ ስር ለናወጣው በነበረበት አኳኋን፣ በጨርቅ ቀረጢት ውስጥ በጥንቃቄ ከትታ ከቋጠረች በኋላ አልጋ ስር አኖረችው:: ከጊታሩ ጋር ሽሮ የተሰራበትን ብረት ድስት ሳይታጠብ አልጋ ስር ከተተችው:: ሥራዎቹን ስታከናውን እርጋታና ጥንቃቄ ነበራት::

ረፋድ ላይ ጋንጩር ለመጀመሪያ ጊዜ ብቅ አለ:: እናቴ ሙት ፈገግታ እያሳየችው "ምን ታርጮልቃለህ፣ አትገባም?" አለችው በተዘጋ ድምጿ::

ገብቶ ፍርድ እንደሚቀበል ሰው ከፊቷ ቆመ:: ጉንጭና ጉንጩን በአንድ እጇ ስትይዘው አገጩ መዳፏ ላይ አረፈ:: ጠጋ አድርጋ ሳመችው::

"ና አንተም ልሳምህ" አለችና እኔንም እንደ ጋንጩር ጉንጩን ጋ! ሳመችኝ::

ገና ከሞጆ የመጣች ያህል አዲስ ነገር አይባት ነበር:: ካመጣችው ጥራጥሬ በአይነት በአይነት አውጥታ በየተራ ለቀመች:: ቅይጥ ንፍሮ ልትቀቅል ነው ማለት ነው:: ስንዴ፣ ባቄላ፣ ምስር፣ ሽንብራ:: እንደ አበሳሰሉ ፍጥነት ማሰሮ ውስጥ ከትታ ቀቀለች:: ከንፍሮ አቀቃቀሏ ውጭ ምናም የድሮዋን እናቴን አትመስልም:: ሙትት ያለው ፈገግታዋ በጥቁር ብርሃን የተከፈነ ነው:: ንግግሯ፣ አስተያየቷ፣ አሳሳቋ፣ አካሄዷ ሁሉ እንጀት የራቀው ሰው አይነት ነው:: ግን ደግሞ እንዳች በግልፅ የማይታይ ጉልበት አለው::

የቤታችን ፀብ፣ ንጹሕና ንስሃ ያለ ማንም ባዕድ ተሳትፎ ስለተከናወነ ወሬው የትም ያልደረሰ ይመስለኝ ነበር:: አንዳንድ ጎረቤቶች በሰበብ አስባብ እየመጡ

"ባለቤትሽን ሰሞኑን አላየሁትም" ሲሏት

"አለ፣ መንገድ ሄዶ ነው" ትላለች ሳትናወጥ ወዲያው በሚገፋተር ድምፀት "ምን ፈለክ ነበር ያሉኝ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"ባቄላ፣ አተር፣ አንድ ስፍር ስንዴ..." ሲሉ

"በግገር ነው፣ ወይስ...?"

"ትሸጫለሽ? ከብድሩማ አንድኛውን ግዢው ይሻለኛል።"

በዚህ መንገድ እናቴ ወደ እህል ንግድ ገባች። እኔ የማግባት ቅጡ ጠፍቶኝ ዝም ብዬ አያታለሁ። እራሷን ከሃሳብ ለመገላገል የምትጠቀምበት ዘዴ መስሎ ይታየኛል። ከሰው ጋር ያላትን ግንኙነት ቆጥባ ሁለመናዋን ሥራዋ ላይ ጣደች። አንዳንዴ በሳምንት ሁለቴ ሞጆ እየተመላለሰች እህል ትጭናለች። እንደተቀናት የማንፍሴ ሴቶች ወገቧን አስራ ተመሳስላ "ና! ኑ!" ትለናለች እኔና ጋንጩርን

"ና! ኑ! ለተሸከሚው ቤቱን አሳዩ" ወይም "አንተ እዚሁ እህሉን ጠብቅ አንተኛው ደግሞ ቤቱን አሳየው።"

የሥራ ድልድላችን ይሄው ነው። እናቴ እንደቀድሞው ሞጆ ሄዳ መከረሙን ትታቀለች። ውሎ ገብ እህሉን ጭና ከተፍ።

ጋሽ ድንቁ አንዳንዴ ሲሰክሩ "እኔ የምለው" ይላሉ ድምፃቸውን ዘለግ አድርገው "ሞጆ ደጋ ነው፣ ቆላ ነው? ወይስ ወይና ደጋ? እንዴት ባቄላና ማሽላ አንድ ጋ ይመረትበታል? ገብስና በቆሎ? ጨረቂትና ጤፍ? ተሰምቶም አያውቅ።"

እናቴ አይናን ሰብራ ጆሮዋን ታነቃለች።

"ይሄ ሁሉ አንድ ጋ የሚገኘው እህል በረንዳ ብቻ ነው።"

"ጋሽ ድንቁ እንደ ቀድሞው ጊዜ ቤታችንን ለመድፈር አይሞክሩ እንጂ ፍርሃታቸው ጠፍቶ መዛናት መጀመራቸው እርግጥ ነው። ከእሳቸው በላይ ለማዋረድ የሚያጀበጅቡት የታች ሠፈር ሰዎች ናቸው። ከእኔ አልፈው ጋንጩር ባጠፋውም የሚወቀሱት እናቴን ነው።

"ለምለም፣ ይኼ ወዶ ገባ ልጅሽን አንድ በይኝ" ይላሉ የጋሙዳ እናት

እናቴ "እያገባኝም" አትልም። "ምን አደረገ?" ትጠይቃለች።

"ልጄን ፈነከተው፣ ደሙን አፈሰሰው፣ ደሙን ያፍስሰውና"

"ልጅ ነው፣ ከመራገም መቆጣት ይሻላል።"


t.me/OLDBOOKSPDF

"እንደው ምን ምን ተጨዋወቃችሁ? አፍታተህ እኮ አልነገርከኝም። እኔን ወቀሰልህ?"

"አ-ይ"

"ኢ-ቪ ጤናዬን ጠየቀ?"

"አ-ዎ"

"እኔ ምን እሆናለሁ? ደህና ቤቴ ተቀምጬ የእመቤት ኑሮዬ አልተጓደለ፣ ይኼን ነገርከው?"

"አዎ፣ አሁን ተኝ ነገ እናወራለን።"

"አፈር ተኛ እቴ፣ እኔ ተጨንቂያለሁ ልተኛ ይበለኝ? አረንዛ ሆድ! ይኼኔ አባትህንም እንዲሁ ዝም ብለኸዋል።" ወሬዋ ቅርንጫፍ አበጅቶ መነሻውን እስኪስት ድረስ ትራገማለች፣ ትወቅሳለች።



t.me/OLDBOOKSPDF

ሆናለች ይቺ? ቀምዬ አሳድጌ...." ስሜት ማለዘቢያ የጭንቅላት ውስጥ ወጌ ለዛሬ አልያዘልኝም:: መንፈሴ እንደተሰበረ በግቢው ለመውጣት መለስ ስል

"ቆይ" አለች ማናሉ

ቆምኩ::

"አባትህ የደረሰበት ታውቃ?"

ዝም አልኳት::

"ከፉዎች!" አለችኝ እኔና እናቴን ደርባ፤

የሚወቅሰኝ አፈልግ ነበር ማለት ነው? ስሰደብ ለማድመጥ ጓጓሁ::

"ለምን ጨከናችሁበት? ከፉዎች!! እንዴት አስቻላችሁ? ሁለት ቀንና ሌሊት እዛች ሳጥን ላይ ተቀምጦ ምን ልባችሁን አደነደነው?......" ድምጿ የእናቴ ነው:: ሙሾ የበዛበት፣ ፀፀት ፈጥርቆ የያዘው፣ መለስ ብዬ አየኋት:: ያገጠጠ ሀዘን ፊቷን እንጨፍሮታል:: ከፀነሰች የሰነበተውን የሀዘን ቅሪት እንባ ለመገላገል በደከመ መንፈስ እንደምታምጥ ያስታውቃል::

"ለምን?" እኔም ድምፅ አልባ ጥያቄ አቀረብኩላት:: የአባቴ መጥፋት ሀዘኑ ከእኛ ጎጆ አልፎ ታዛችን ስር እንኳን ይገኛል ብዬ አላሰብኩም ነበር::

"ግን ለምን?"

"ጠላቱ እኔ ነኝ" አለች:: "በዚህም ዘላለም ራሴን ስወቅስ እኖራለሁ::"

"እንዴት?" በአፌ ይሁን በአይኔ ጠየቅኳት::

"ደከም ባለበት የመጨረሻ ሌሊት ተሰርቄ ገብቼ አጥሚት አቀመስኩት:: በግድ አንድ ሁለት ማንኪያዎች፤ የመኮብለያ ጉልበት ሆነት:: እዚሁ ቢሞት...."

አቅፌ ማባበል አሰኘኝ:: በእሷ አሳብቢ ማልቀስ፣ ግን እግሬ ታስሮ አልንቀሳቀስ አለኝ::

"መጥፋቱን እንኳን ያወቅኩት ከሁለት ቀን በኋላ አጥሚት ይዤ ሌሊት ስሄድ ነው:: እናትህ በቦታው ተተክታ አገኘኋት::"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እናን?" በአፌ ወይም በዐይኔ

"አቅፈያት አለቀስኩ።" የከበደ ነገር የምትነግረኝ ሳትመስል ቀጠለች፡፡ "እስከዛሬ አለቀስኩ፣ እስከዛሬ አሰብኩ.... ምነው አግኝቼው ከተንጋለለበት ቀና ባደረኩት፣ እስከ ዓለም ዳርቻ በተከተልኩት፣ መሄዱን ባገዘኩት፣ መራቡን በረዳሁት....." የእኔ ፀፀት ሲፈታተነኝ በማናሉ በኩል የመጣ መሰለኝ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

# አስራ አራት

እናቴ እህል ወደ አፏ ሳትል መንደርተኛውን በየመንገዱ እና በየቤቱ ታስለምለች::

"ዛሬ ማናሉ አገኘችው ከመንገድ፣ እንዴት አምሮበታል አለችኝ፣ ይገርማል፣ እኛ እዚህ ጠብ እርግፍ እንላለን እሱ እዚያ...." ፊቷን መገረም ይረታዋል::

ማናሉ ባክና ስትመጣ ትጠየቃለች:: አቧራ የቃመ ኮንጎ ጫማዋን እያየች ዝም ትላለች::

"ዛሬ ጋሽ ድንቁ መጠጥ ቤት ሰተት ብሎ ሲገባ ተከትለው አፈፍ አደረጉት:: ወንዱ! ብሎ ሲዞር ጋሽ ድንቁ:: ምነው? ምነው? ብለው ሊወቃቅሱት ሲሞከሩ አፉን እየተመተመ ዝም ይበሉ እራሴ ሹልክ ብዬ እመጣለሁ:: ለለምለም አይንገሩብኝ አላቸው:: አይ እሱ ለእሱ ተጨንቆን እንጂ.... "

ጋሽ ድንቁ ይኸን ሲሰሙ ቱግ አሉ "አብርሬ ገደል ከታው ሲታቢቃ ደሞ እኔን የነብሰ ገዳይ ማለባበሻ ማድረጓ ነው? ቀጣፊ!!"

የጋሽ ድንቁ ንግግር ለእኔም ሆነ ለእናቴ እንደ መርዶ የከበደ ነገር ነበር:: እኔ አባቴ ይሞታል ብዬ ማሰብ አልፈልግም:: እንደ ጀንበር ተዳክሞ በምዕራብ ቢጠልቅ እንኳን ነገ አዲስ ሆኖ በምስራቅ ብቅ እንደሚል ተስፋ ማድረጉን ሙጥኝ ብዬ እኖራለሁ:: ጊዜው ምን ቢረዝም ይደርሳል:: አባቴና እናቴ ጨለማን ተገን አድርገው ያወራሉ::

"እናልሽ...." ይላታል::

"እጅህ ይረፍና አውራ እስቲ" ትለዋለች

"እናልሽ ያ ዘመን መለወጫ የጭንቀት ሌሊት ደረሰ። ግርማዊነታቸው ልጃቸውን ልዕልቷን ይዘው ተገኝተዋል:: የእኛ ተራ ደርሶ የመከፈቻውን እኔ


t.me/OLDBOOKSPDF

እንድሚጫወት ኮሎኔሉ ወስነዋል:: ገባሁ:: ሰው ሁሉ በሀገር ልብስ ተንቆጥቁጦ የበረዶ ክምር መስሏል::"

"ኢ-ቤ-ት ማርቀቅ ስትወድ" እናቴ

"ማርቀቅ አይደለም - ፍቅራችንን ስልሽ" አባቴ

"ኢ-ቪ እጅህ ይረፍና አጫውተኝ" እናቴ

"እናልሽ አዲስ የደረስኩትን ዜማና ግጥም ማቅረብ ጀመርኩ::

"ፍቀጂለትና በደንብ ይቀመጥ
ለመኖር ፈልጓል ልቤ ልብሽ ውስጥ

ሕዝቡ ቢስ፣ ቢስ፣ ቢስ ልደግም ስል ኮሎኔል በቃ በቃ ውረድ አይሉም? ምነው? ብላቸው ጃንሆይ ተቆጡ አሉ:: ለምን? ስል እየዘፈንክ ወደ ልዕልቲቱ ስለጠቆምክ አይሉም::"

"ኢ-ቤ-ት አንተ! ልዕልቲቷም ጋ ሄድክ?"

"እኔ ስራሴ ያ - ሁሉ መብራት ላዬ ላይ ተለቆ ምን ይታየኛል? እኔ እንደውም አስብ የነበረው አንቺን ነው::"

"አሁን ድለላውን ተውና ፍሬ ነገሩን ንገረኝ"

"በኋላማ ከሙዚቃ ክፍሉ ተባረርኩ:: የተጠቀሰብኝ አንቀፅ እዛው ኮሎኔሉ የገፉት ነበር:: በመንግስት ባንድ እና ዝግጅት፣ አቅሙን ያላገናዘበ የግል ፍላጎቱን አለአግባብ ለማሳካት በመሞከሩ የሚል::"

"አንቺ ለምለም!"

"ልጅህ ተነሳበት፣ ሰው ደስ ብሎት ሲጫወት አይወድ"

ይኸን ተስፋ አድርጌ ስኖር ድንገት አንድ ቀን እናቴ እንዲህ አለችኝ::

"ከፉኛ ደከምኛል:: አገሬ ገብቼ ከዘመዶቼ ላስተዋውቅህና የሚመጣውን እዚያው ሆኜ ልቀበል"

ኮተት ሳናበዛ ወደ ሞጆ ተሰደድን።

t.me/OLDBOOKSPDF

# ክፍል ሁለት

# የሞጆ ቀትሮች



t.me/OLDBOOKSPDF

# 1

# የእግዚአብሔር ዘንግ

የተፈጥሮ ንዳድ ከአፋር ተነሥቶ፣ ዱከምን አጣቅሶ፣ ደብረ ዘይትን አጣጥፎ፣ ሞጆ እንደሚደርስ የጂኦግራፊ መምህራችን ሲነግሩን እጅግ ተደንቅሁ፤ የስምጥ ሸለቆ በደቡብ ኢትዮጵያ አድርጎ ድንበር በማሳበር ከኬንያ እስከ ታንዛኒያ ያሉትን ሕዝቦች የስልቱ ነዋሪ አድርጓቸዋል፡፡ ይሄን የሰማሁ ሰሞን አንዳች መፍትሔ ማግኘት ያደራጀው ተረታዊ አሳቤ መጣልኝ፡፡ የእግዚአብሔር ፀሐያማ ዘንግ ከእጁ አምልጦ ወደ ምድር በመውረድ ይሄን አካባቢ በቁመቱ ልክ አሰመጠው፡፡ ከምድር ወለል እጅግ አርቆ ባለመዝለቁ ውኃውን መቅ፣ አፈሩን ጥብስ እያደረገ ይኖራል፡፡ የሞጆ ሙቀት ሲጨምር፡-

"ተነሣበት የእግዚአብሔር ዘንግ" እላለሁ፡፡ የሞጆ አፈር ያልበሰለ የበቆሎ እንኩሮ ይመስላል ያልጠፋ ብረት ምጣድ ላይ እንደተጣደ ሁሉ ዝም ብሎ የሚግለበለብ ብርሃናማ ጢስ አለው፡፡ ይሄ ምድር እንደ ግንፍሌ ቀይ ሆነ ጥቁር አፈር የለውም፡፡ ወንዞቹ ውኃ አልባ ናቸው፡፡ ዝናቡ የጋለው ምድር ላይ እንዳረፈ ይጠፋል፡፡ ሾላ፣ ዋንዛ፣ አቃቅማ፣ አውጥ፣ ቀጋ፣ አጋም.... የሉም፡፡ በእነሱ ፋንታ የካዛሚር፣ የግራር እና የቱሪማንቱሪ ዛፎች ወርረውታል፡፡

ወደ ሞጆ የመጣሁ ሰሞን ዐይኔም ነፍሴም ተጨንቀውብኝ ነበር፡፡ ከመልመዴ በፊት ሞቴ እንደሚቀድም ይሰማኝ ነበር፡፡ እየሩን እንደ አሸዋ በሰፌድ መሳይ ነገር የገፋብኝ ይመስል ከሁሉም አቅጣጫ የማያንቀሳቅስ ኃይል ቀስፎ ይይዘኛል፡፡ ደረቴን አንቀሳቅሼ መተንፈስ ይሳነኛል፡፡ እታፈናለሁ፡፡ ላብ፣ ላብ፣ ብቻ፡፡

ለሞጆ አናናር የቀረበ መፍትሔ ባይኖርም ተረታዊ እሳቤዬ ውስጥ ግን አንዳች ተስፋ ትታየኝ ነበር፡፡ አንድ ቀን እግዚአብሔር ዘንጉን ሲፈልጋት ሜቷ

t.me/OLDBOOKSPDF

ጋሽ ጥበቡ ከአንገታቸው ቀድሞ ዐይናቸው ቀና እያለ በፀብ መጎምጀት ያይዋቸዋል፡፡ ግን ምንም ማድረግ ባለመቻል እየተትከነከኑ መንገዳቸውን ይቀጥላሉ፡፡

ጋሽ ጥበቡን ማበሳጨት ለጋሽ በረደድ አደጋ የሌለበት ጨዋታ ነው፡፡ መጠጥ ቤትም ሲያገኙዋቸው ለአዝማሪ ግጥም በመስጠት ያስቁባቸዋል አሉ፡፡

"ለመደብህ መስል ያይጥ ጀግንነት፣
አምና ሦስት ገደልክ ዘንድሮ አምስት፤
ያሰልህ እንደሆን ለከርም ድመት"


t.me/OLDBOOKSPDF

# 2

## የሞጆ ወርቅ

ጋሽ በረደድ እኔን ሲያዩ የአዋቂነት መቆርቆር ያሳያሉ::

"አንተ ልጅ፣ በዚህ ቀትር ብቻህን ምን ታደርጋለህ? ቤትህ ቁጭ አትልም? የሞጆ ወርቅስ? ወይ እሷጋ እዚያው እህል በረንዳ ሂድ እንጂ እዚህ..."

የጋሽ በረደድ መቆርቆር ጨርሶ አይጥመኝም:: እንደውም ያናድደኛል:: ምክንያቱንም አውቀዋለሁ:: በአከስቴ ነው:: ተስፋ የማይቆረጥ የረጅም ጊዜ ምኞት አከስቴ ላይ እንዳላቸው ይገባኛል::

"የሞጆ ወርቅ" ይላሉ::

የቪ.ወርቅ ነው ስሟ" እላለሁ ጣልቃ ገብቼ

"አይ የልጅ ነገር ከቪ ሞጆ አይበልጥም?"

ዐይናቸውን፣ መቁነጥነጣቸውን፣ አከስቴን ለማስደሰት ያላቸውን ጥረት እያየሁ እጠላቸዋለሁ:: እኔን ብቻዬን አግኝተው ከገሠፁኝ ሰበብ አድርገው አከስቴጋ እንዳይሄዱ ተስፋ ለማስቆረጥ ቀድሚያቸው እሄዳለሁ::

አከስቴ ሠርከ እንቁጣጣሽ መስላ ነው ወደ እህል በረንዳው የምትሄደው:: ብዙ የተለፋባቸው ጥበብ ልብሶች ታዘወትራለች:: ጥልፏ እየተንቆጠቆጠ ከጆሮና ከአንገት ወርቆቿ ጋር ይፎካከራል:: ሻሿን ከኋላ አምጥታ አናቷ ላይ ታስረውና ሆን ብላ የፀጉሯን ዘለላ ከሻሹ እንዲያፈተልክ ትፈቅድለታለች:: ከቤት ወጥታ ወደ እህል በረንዳው ስትሄድ ቢያንስ ሁለት አሽከሮች ይከተሏታል:: የእኔን ትከሻ አቀፍ አድርጋ እንደዘበት የአሽከሮቿን ስሞታ ታደምጣለች:: እህል በረንዳ ስንደርስ ንፁህ ሸርጥ ይቀርላታል:: እሱን ጥበቧ ላይ ደርባ የእህል በረንዳው ድምቀት ሆና


t.me/OLDBOOKSPDF

ጋሽ በረደድ ለአክስቴ ምኞት ሲሉ ያዳንቁኛል:: "በእኛ ጊዜ ቢሆን ከቡር ዘበኛ ይመለመል ነበር::"

"አይ የእርስዎ ነገር፣ የእኔ ልጅ ዶክተር ነው የሚሆነው:: ያያሉ፣ ምናለች በሉኝ ቱ ከምላሴ ፀጉር ይነቀል"

አክስቴ በእኔ የምትተማመነው ለይስሙላ አይደለም:: ደግሞም እንደው ከባዶ ሜዳ ተነሥታ ዶክተርነትን ከእኔ አትጠብቅም:: ትምህርቴን አሳብባ ምንም ነገር እንዳይጎድልብኝ ትጥራለች:: ልብሴና ጫማዬ አይነት በአይነት ነው:: ለእኔ የሚሆን ልብስ ባየች ቁጥር መግዛት ነው:: ይሄንን አስታከው የሠፈር ጓደኞቼና የትምህርት ቤት ልጆች "ቱሪስት" የሚል ቅፅል ሥም ሰጥተውኛል::

"ቱሪስት" የተባልኩት በልብሴ ብቻ ሳይሆን በምይዘው ገንዘብም ጭምር እንደሆነ አውቃለሁ:: አክስቴ ብር ቆጥራ ሰጥታኝ አታውቅም::

"በርሳዬ ያውልህ ውሰድ" ትለኛለች::

ኀላፊነቱን ለእኔ ትተውዋለች:: አዘውትራ እንዲህ ስትል ታሳስበኛለች::

"ብቻ ገንዘቡን ለከፉ ነገር አትጠቀምበት እንጂ ከፈለከማ...." ትከታዋ እውነት ፈታሽ ነው:: "ይሄንን የእኔ ልጅ አታደርገውም!"

እራሴን የእራሴ ጠባቂ አደረገችው ልበል? ጎርምሼ እንኳን ጓደኞቼ ጫት ሲቅሙ፣ ሲያጨሱና ሲጠጡ ልሞክረው ብዬ አላውቅም:: የእራሴ ጠባቂ እራሴ ዘወትር ከጎኔ አለአ:: ጠባቂ የሌላቸው ጓደኞቼ......


t.me/OLDBOOKSPDF

# 3

## ሙና

አክስቴ የዱክትርና መንገዴን ስትጠርግልኝ የግል አስጠኚ ቀጠረችልኝ። ያማከራት የትምህርት ቤታችን ዳይሬክተር ሳይሆን አይቀርም። የተቀጠረችልኝ መምህርት ሳያት ንዴት፣ ንዴት የሚለኝ አስተማሪዬ ነበረች። ሙና ትባላለች።

ሙና ጠላቂ ወናተኛ የሚያስመስላት ትልቅ መነጽር አላት። ሽበት ጣል ጣል ያለበት ከርዳዳ ፀጉሯን በቅባት ወደ ኋላ ለማስተኛት ትሞክራለች። አዘውትራ ጀርባዋ ላይ ጣል የምታደርጋቸው የተለያዩ ሳይነን ሻሾች አሏት። አረጅም ቀሚስ ትለብሳለች። አፊ ዱልዱም አይጥ የመሰለ አይጥማ ጫማ ታደርጋለች። ስትሄድ እግሮቿ ሁለት አይጦች ቀደም ቀረት እያሉ በስለላ የሚጓዙ ይመስላሉ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ልታስተምረን የመጣችው ስምንተኛ ክፍል ሆነን ነበር። ከዚያ በፊት የአምስተኛ ክፍል መምህርት ሆና እውቃታለሁና በተለይ እኔ ተናደድኩ። የጉርምስና ትዕቢቴ አንዳች ድምዳሜ ላይ አድርሶኝ ነበርና ነው። የአምስተኛ ክፍል መምህሮች 5ኛ ክፍልን ሥራቸው ያደረጉ የአምስተኛ ክፍልን ሊያልፉ የሚችሉ ነገር ግን ስድስተኛ ክፍልን የማያውቁ ተማሪዎች ይመስሉኝ ነበር። ስለዚህ መምህርት ሙናን በሦስት ክፍል አልፌያት በየት በኩል እንደቀደመችኝ መገንዘብ ተሣነኝ። በትዕቢት ወደ ቢሮ ሄጄ ለዲያሬክተሩ አቤት አልኩ።

"ቲቸር ሙና የአምስተኛ መምህርት እንጂ እንዴት የእኛ ይሆናሉ?"

"የየሺወርቅ ጎረምሣ፣ በእናንም ሥራ ገባህ? ጥሩ፣ መምህርት ሙናን የምናውቃት እኛ እንጂ አንተ አይደለህም። አሁን ውጣ!"

"አይደለም እኮ..."

"ውጣ አልኩህ ውጣ! ባጠጥክ"



t.me/OLDBOOKSPDF

በቀጣዩ ቀን ሙና መነፅሯን ሁለት የኢሊ ሜጨቶች አስመስላ ዓይኗ ላይ እንደደነቀረች መጣች፡፡ እሮጌ ቁስ የሚያስመስላትን ጎታታ ቀሚስ በአንድ እጇ ይዛ በሌላኛው የቾክ ካርቶን የተቀመጠበት መጽሐፍ

ምንም ሳትናገር "ሎጋሪዝም" የሚል ቃል ጻፈች

ፊቷ ሙሉ በሙሉ በሁለቱ ኢሊዎች ተሸፍኗል

ከመነጽሩ የተረፉት ከንፈሮቿ እንደፍሬሙ ሰስና ረጅም ሆነው ታዩኝ፡፡ ከትምህርቷ ይልቅ ሁኔታዋ ላይ አተኮርኩ፡፡ እነዚህ ስስ ከንፈሮች እንደ እናቴ አይኖች ቃል ሳይወጣቸው ብዙ የሚናገሩ ሆነው አገኘኋቸው፡፡ ረብሻ ቢጤ ሲያጋጥማት በኢሊዋ ታፈጥና በስስ ከንፈሮቿ ታንቋሽሻለች፡፡ መማታቷን በሚያስመርጥ አኳኋን ትጸየፋለች፡፡ ይሄን ሁኔታዋን ብዙ ጊዜ ስናረፍድ፣ የቤት ሥራ ሳንሠራ፣ መጽሐፍ ስንረሳ ደጋግሜ አይቼዋለሁ፡፡ ተማሪዎቹ ከሁሉም መምህራን በላይ የሚፈሯት እንደነበረች አስታውሳለሁ፡፡

በዚያ በመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ ያለችውን አንዱን ሳልሰማ ጨረሰች፡፡

"ጥያቄ ካላችሁ......"

ዝም አለ ክፍሉ፡፡

ፊቷን ወደግራ ወይም ወደቀኝ አድርጋ በዐይኖቿ ግን እኔን የምታየኝ ሆኖ ተሰማኝ፡፡

"ጥያቄ የላችሁም?"

ድፍን መነፅሯን ከለላ አድርጋ እኔን እንደምታየኝ ገብቶኛል፡፡

"እዛጋ፣ ጥግ" አለች ወደኔ እየጠቆመች፡፡ አሁንም ፊቷ የዞረው በእኔ ተቃራኒ ነበር፡፡

"ጥያቄ የለህም?"

አለማድመጤ ቁጩኝ እንጂ አልደነገጥኩም፡፡

"የለኝም" አልኩ፡፡

"ከመማርህ በፊት ግን ጥያቄ ነበረህ" አለችኝ፣ እንደ አንሶላ ጠርዝ መስመር ብቻ የሆነው ከንፈሯን በንቀት ለጥጣ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"ነበረኝ" አልኩ ከማፈግፈግ ይልቅ እየተጋፈጥኩ

"ምንድነው?" ተማሪዎቹ ሁሉ ወደኔ ዞሩና በዓይናቸው እንደዝንብ ወረሩኝ:: ከዚህ በፊት ደጋግሜ ሳውጠነጥን የነበረ አንድ ነገር ትዝ አለኝ:: መምህርቷን ለማናደጃ ሳይጠቅም አይቀርም በሚል ሰነዘርኩት

"ሒሳብን ለማወቅ ያን ያህል መጣር አልነበረብኝም:: ውጤቱ ልፋት ነው:: ቁጥር መካብ፣ ማፍረስ፣ መልሶ መካብ ለሕይወት ምን ጥቅም ይሰጣል? ምንም!"

ከፍሉን ጤናማ ያልሆነ ጸጥታ መታው:: የተማሪዎቹ ዐይን አሁን የመምህርቷን ፊት ወርሮታል:: የብረት ምጣድ ጠርዝ የመሰለ ከንፈሯ በንቀት አልተሰጠጠም:: ብቻ በኖክ ብናኝ እከክ የወረሰው የመሰለ እጇን ወደ ኋላ አጣምራ ተንጎራደደች:: ልፋቷ ሁሉ ገደል እንደገባ ሳይሰማት አልቀረም:: በመነፅር ግርዶሽ የተሸሸገ ስሜቷን ሳልረዳ ጠየቀችኝ::

"ሥምህ ማነው?"

"መኪብብ" በረባሽነት ሥሜን ወደ ቢሮ ልታስተላልፍ እንደሆን አልተጠራጠርኩም::

"መኪብብ...... መኪብብ... መኪብብ" በአይጦቹ መንጎራደዷ እንደቀጠለ ነው:: "መኪብብ..... መኪብብ.... ፍቺውን ታውቀዋለህ?"

"ምን ታደናግራለች?" አልኩ በሆዴ በአፌ "አላውቀውም"

"የትልቅ ሰው ስም ነው:: የንጉሥ ሰለሞን ስም! ንጉሥ ሰለሞንን ታውቃላችሁ?" ወደ ልጆቹ መለስ ብላ፡-

"አዎ" አሉ::

"የጠቢቡ፣ የእሱ ስም ነው:: ፍቺውን ከከፍል ስወጣ ጠይቀኝ። ባይ ዘዌይ መኪብብ ያነሳው የፈላስፋ ጥያቄ ነው"

ደስታዬን በዘዴ እንዳቀጠነችብኝ ገባኝ:: አቀረቀርኩ፣ መንትያ አይጥ የመሰሉ ጫማዎቿ በሁለት ዴስክ መካከል ከወዲያ ወዲህ ሲሉ ታዩኝ:: ጋሽ ጥበቡ ባጠመዷቸውና "በእናንተ እኔና እግዚአብሔር ስንቴ እንቀሰል?" እያሉ በሾተል በቦዳደሏቸው::


t.me/OLDBOOKSPDF

አቀረቀርኩ፣ ሁለቱ አይጦቿ በቀሚስ ውድቅት ተጋርደዋል፡፡

"ቻው"

አይጦቿ በግርዶሽ ተንቀሳቀሱ፡፡

"ከፉ ናት" አልኩ እናቴ ዓይኖቿን ፊት በሚከልሉ የጢንዚዛ ሠንጋዎች አራሷን ደብቃ የመጣች መሰለኝ፡፡ እናቴን እስከ ሞት ያደረሳት የእኔና የአባቴ ለአይና ቋንቋ ከተገቢው በላይ መሽቆጥቆጥ ነበር፡፡ መርበድበድ፣ መራድ.... ለምን? የቤተሰብ ሞት ለምን?

"ቱሪስት፣ ቱሪስት ቲቸር ሙናን ምን ጠየቀች? ምን አለችህ? ተቆጣችህ?....." ጓደኞቼ ከበቡኝ፡፡ ዓይኖቼ መርጠው የተመለከቱት ሦስቱን የሠፈር ጓደኞቼን ነው፡፡ ጦጤ፣ ጠኔ እና ንዳዴ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

# 4

# ወርቃማ መንገዶች

ጦጤ፣ ጠኔና ንዳዴን የተዋወኳቸው በማይረሳ አኳኋን ነበር:: ገና ከአዲስ አበባ በመጣሁባቸው የመጀሪያ ወራት:: የሞጆ አየር እንደ መርግ ተጭኖኝ ቁሪማንቁሪ ዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጫለሁ:: የሞጆ አየሩ ብቻ ሳይሆን ነገሮች ሁሉ መጨበጫ እጀታቸው ተደናግሮኝ የፈዘዘኩበት ወቅት፣ በእኔ ዕድሜ የሆኑ አምስት ልጆች ከወደመጋላ ሲመጡ አየሁ:: አካሄዳቸው ወደ ባቡር ሐዲድ እንደሆነ ጠርጥሬአለሁ:: የሞጆ ልጆች ጨዋታቸውም፣ ሥራቸውም ከባቡር ጋር የተያያዘ ነው::

አምስቱ ልጆች ተቀምጬ ሲያዩኝ ዝም ብለው ሊያልፉኝ የፈለጉ አይመስሉም::

"አንቺ?" አለኝ (ጦጤ መሆኑ ነው) ቀና ብዬ አየሁት የሞጆ እንኩሮ አላዩ ላይ ተነፍቷል:: ሁሉም ያውናቸው::

"የአዲስ አበባ ልጅ ነሽ?"

"አዎ" (እንዴት አወቀ?)

"ለዚህ ነው ጃኬትህን ቆልፈህ የምትቀቀለው?" አለኝ (ጠኔ መሆኑ ነው) ሁሉም ሳቁብኝ::

አዲስ ሙሉ ልብስ ከአዲስ ጫማ ጋር አድርጌአለሁ:: አለባበሴ እንዲደፍሩኝ የገፋፋቸው መሆኑ ገባኝ:: የቤት ልጅ መሰያቸው::

"አትናገርም?" የሴት ድምፅ:: አንዷ ለካ ሴት ኖራለች:: አለባበሷም ፀጉሯም ምኗም ሴት አትመስልም:: ትንሽ መልኳ፣ ጎላ ጎላ ያሉ ዓይኖች" (ናፍቆት መሆኗ ነው) ንፁህን አስታወሰችኝ የቀበናዋን::



t.me/OLDBOOKSPDF

"ምን ይዘጋኻል? እናትንና" አለችኝ

"ምን አረኩሽ?" አልኳት ተነስቼ ቆምኩ።

ሁሉም ሳቁ።

ሴትን በዱላ የመፍራት በሽታዬ መጣ

"ና" አለችኝ እየተጠጋች።።

"ምን አድርጌሽ ነው?" ወደቱሪማንቱሪው ግንድ አፈገፈግሁ። ብትመታኝ ምን አደርጋታለሁ? ጠኔ ከሁሉም በላይ አፉን ከፍቶ ይስቃል። ንዳዴ ባልተጋነ ፈገግታ ያየኛል።

"ይዋጣላችሁ፣ ትችላታለህ?" ጦጤ ነበር።

"አልችላትም፤ በእናትሽ አልችልሽም" ግንዱ ላይ ልጥፍ አልኩ።

"እናትንና" ብላ ተጠግታ በእርግጫ መታችኝ

"እሺ፣ እንደፈለግሽ"

"ብራቮ ናፊ፣ ብራቮ ናፊ!"

"በቃ ተይው፣ ፈሪ" (ንዳዴ መሆኑ ነው)

እስካሁን አንዱ ልጅ ብቻ ዝም ብሎ ያያል። እንደ ጢሪሪ ካልነኩት የማይነካ መሆን አለበት ስል አሰብኩ።

"ይገብር" አለ (ጠኔ መሆኑ ነው።)

ናፍቆት ኪሴን ፈትሻ ያገኘችውን ሳንቲም ለንዳዴ ሰጠችው። መሪያቸው እሱ መሆን አለበት ስል አሰብኩ።

"ነገም ፍራንክ ይዘህ እንድትመጣ" አለችኝ

"እሺ"

እየተሳሳቁ ከእኔ ኪስ የተገኘውን ሳንቲም ሲቆጥሩ እኔ መቶ ኪሎ አየር ተሸክሜ ወደ ቤት አመራሁ።

t.me/OLDBOOKSPDF

ሠፈራችን 'ልዑል መውደቂያ' ይባላል:: በኋላ እንደሰማሁት የዐፄ ኀይለ ሥላሴ ልጅ ሞጆ ላይ በመኪና አደጋ ሲሞቱ የወደቁት እዚህ ሠፈር በመሆኑ ነው ሠፈራችን ልዑል መውደቂያ የተባለው:: መንገዱ አጭር ቢሆንም ብዙ ጊዜ እያረፍኩ ደረስኩ::

ከመቼው ቤት ገብቼ ለሰላሳ ጠጥቼ እያልኩ በመጓጓት ስንተት አክስቴ ከወደ ገቢያው አቅጣጫ እየተቻኮለች ስትመጣ አየኋት ከበስተኋላዋ ሦስት እህል አውራጅና ጫኞች ተከትለዋታል:: ሊደርሱባት ፈልገው አልቻሉም::

ገና ስታየኝ "ማነው? ማን አባቱ ነው የመታብኝ?" ስትል ጠየቀችኝ:: ወሬው ቀድሞኝ ደርሶ ኖሯል:: በየት አልፎ? እንዴት አልፎ? መልስ የለም::

"ማንም" አልኳት

"እስኪ" ጉንጮቼን በሁለት እጆቿ ደግፋ ፊቴን አየችው:: ዓይኗን ስላላመነች ደባበሰችኝ::

"ምንህን ነው የመቱህ?"

"ማን?"

"እንጃ! የምሰማው ታዲያ ምንድነው? መጋላዎች......" ፊቴን ወደ አንገቷ ውስጥ ወሸቀችው:: የመደንገጧ ይሁን የመሮጧ ልቧ ይደልቃል:: ሽቶዋ የሰባተኛው ሰማይን የቅዳሴ ዕጣን ይተካከላል:: የአንገትጌዋ ጥልፍ ፊቴን እየኮሰኮሰ ፍቅሯን ሙሉዕ ከመሆን ሊያናጥበው ይሞክራል::

"እነዚህ ሟርተኞች በምን አይናቸው አዩብኝ? ዐይናቸው ይጥፋና... አንተስ በፀሐይ ቤትህ ቁጭ አትልም? ካልሆነ እኔጋ አትመጣም?" ይዛኝ ወደ ቤት ስትገባ እህል ጫኝና አውራጆቹ ወደ ገቢያው ተመለሱ::

ወሬውን አፍኜ የማልችለው ሆነ:: ከአስደንጋጭነት ወደ አስቂኝነት ተሸጋግሮ ማዛባበቻ ሆንኩ:: ከእህል አውራጆቹ አንዱ....

"አፈር ብላ፣ ሴት ትመታሀ?" አለኝ (አለ? መሆኑ ነው) ቤት ድረስ መጥቶ:: ለምን እንደሚመጣ አውቃለሁ::

"ቤት ናት ብዬ ነው" አልኩ



t.me/OLDBOOKSPDF

"ትሁና! ደርሰህ አትንካት እንጂ ከተማገደችብህ ማገደድ ነው እንጂ:: ዳሩ ነብሪት መች ተችላ:: አንደባለለችህ አሉ"

በዐይኔ ነክሼ ያዝኩት:: የምለው ጠፋኝ

"ለሁለተኛው ነጠላህን ወደዚያ አትሂድ:: ገላጋይ ይዘህ ነው ባይሆን"

ንቀቱ ቆጠቆጠኝ

"ሴት ናት ብዬ ነው አልኩህ" እውነቱን የማስረዳበት አቅም አጠረኝ:: አለነ ዝም ብሎ ይገለፍጣል:: ቀይ ድድ፣ ቀጫጫ ጥርስ:: ሳቁን የማከስምበት ዘዴው ጠፋኝ::

"ከፈለከ ይዘኸኝ ሂድና ከወንዶቹ ጋር ይዋጣልን" አልኩት -

"ሙቼም ቆሞ አያስደበድበኝም ብለህ ነው? አሃሃሃሃሃ...... ከቴም ከወንዶቹ ጋር፣ የሴቷ አልሆንልህ"

ከቤት ስወጣ ሳቁ ሸኘኝ:: ሳልርቅ ወዲያው መለሰ ስል ከሠራተኛዋ ከሎሚ ጋር ሆድ ለሆድ ገጥመው እንደቆሙ ደረስኩ:: ደነገጠ:: መለስ ብዬ በር ላይ ቆምኩ፣ መጣ:: ዘወር ብዬም ሳላየው

"ይዘኸኝ ሄደህ ከወንዶቹ ጋር በተራ በተራ እንዲዋጣልኝ ካላደረክ አሁን ያየሁትን ለየሺወርቅ እነግራታለሁ" አልኩት

"እን..." የጎረሰው እንዳነቀው ሆነ::

አለነ ወስዶ ለማደባደብ እስኪወስን ድረስ ወሬው ልዑል መውደቂያን አዳረሰ:: ያዩኝ ሁሉ የወሬውን እውነትነት አረጋገጡ:: አለባበሴ መሆን አለበት::

"ውይ ይሄማ በምን ይችላታል:: እሷ ነጥቆ በል ነች::"

የሚያም ነገር ከልቤ ላይ ሲነሳ ይታወቀኛል፣ መላ ሰውነቴን ሲያዳርሰው::

ናፍቆት ደሞ ሠፈር ወይም ገበያ ድረስ እየመጣች "ጉብር" ትለኛለች ቶሎ እንድትሄድልኝ ያለኝን እሰጣታለሁ:: ግን ሠዎች ያይዋታል:: ይስቃሉ አንዳንዶቹም እንዴት እንደመታችኝ ይጠይቋታል::


t.me/OLDBOOKSPDF

እሚያምር ዓይኗን ሹፈት ሽፍና "በእናትሽ በእናትሽ አለ" ትላለች:: ናፍቆት ንፁህ ተንጣቆላ እንደሆነች አስባለሁ:: የሞጆ አየር ስለከበደኝ ግንፍሌ እንደ ትሬንታ ኳትሮ እያጓራች ወደ እኔ ስትመጣ፣ ድንገት ከላይዋ ላይ ንፁህ ወርዳ ባዝና ባዝና እዚህ የደረሰች:: መባዘኗ ከብዶ ከእኔ ጋር ያረሳሳት::

በቅጡ ስለማላውቃት ናፍቆትን ማብሸቂያ እጣለሁ::

"ናፍቆት መጣችልህ" ይሉኛል አንዳንድ አብሻቂዎች:: አገናዘቤ ውሸት መሆኑን እስካውቅ አበረግጋለሁ:: ከመጣችም "ጉበር" ትለኛለች:: እከስቴ ስር ከተቆመጥኩና እነእለነ አካባቢው ላይ ካሉ አፏጭታ ትጣራለች::

ሳንቲሙን ከሰጠኋት በኋላ "ናፍቆት በእናትሽ እላታለሁ::

"ምንሆንክ?"

"ከወንዶቹ ጋር ይዋጣልኝ፣ በእድሜ እንዳይመቱኝ እድርጊና...."

ከት ብላ ትስቃለች:: እናቷ እያስገደዷት ሳይሆን እይቀርም በቁምጣ ላይ ቀሚስ መልበስ ጀምራለች::

"ለራስሽ እኔን ያልቻልሽ" እሃሃሃሃ "ጠኔን ትችለዋለህ? ንዳዴ እንኳን ይቅርብህ ይገድልሃል::" ሹፈት::

"ንዳዴ ይምጣልኝ"

ከት ብላ እየሳቀች ትሄዳለች::

እለነ እድፍጦ ዝም ብሎኛል:: እጠገቡ ሄጄ የሎሚ መእት እዘፍናለሁ::

"ሎሚ ብወረውር እሃሃሃሃ"

ድንግጥ ይላል:: ከሎሚ ጋር ያደረጉትን ለየሺወርቅ መንገሪያዬ እንደደረሰ ይገምትና በእይነቁራኛ ይከተለኛል::

"ሎሚ ተራ ተራ፣ ሎ.....ሚተራ ተራ...."
ሎሚ ተራ ተራ
ሎሚ ተራ ተራ
እለነን እደራ"


t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ በቃ" ይለኛል:: ቀጥሮኝ ዝም::

ጋሽ በረደድ ለአክስቴ ምኞት መጥተው ጣልቃ እየገባሁ ስለቸገራቸው:: "አይዛላ ብላሽ! ቆመና መልካም ነበርክ ታዲያ....." ብለው በነገር ይወጋጉኛል::

ጋሽ ጥበቡ እንኳን አይጥ ማስገሪያቸውን ይዘው ሲሄዱ ካጋጠምኳቸው ገርመም የሚያደርጉኝ በሹፈት ይመስለኛል::

ልዑል መውደቂያን ጠላሁ፣ እራሴን ጠላሁ፣ አክስቴንና ቤቷን ጠላሁ፣ ሞጆን ጠላሁ..... ሁሉንም ጠላሁ::

ናፍቆት መጥታ "ገብር" ከማለቷ በፊት ቀድሜ ሄድኩ፣ ቱሪማንቱሪ ዛፍ ሥር ቁጭ ብዬ ጠበኳቸው:: ጥቂት አረፍ እንዳልኩ ነበር የመጡት::

ጠኔ ቀደም ቀደም ብሎ "ገብር" አለኝ:: ትክ ብዬ ስመለከተው ያልጠበቀው በመሆኑ ግራ ተጋባ::

"የሚበላ አልያዝክም? ገብር" አለ የቀድሞው ባልሆነ ደምፀት::

በዚህ መሃል ናፍቆት መጣች "ገብር"

ዝም ብዬ አየኋት:: የተቀመጥኩበት አግሬን በእግሯ መታ አድርጋ "አትሰማም?" አለች::

"ኧረ ትዕቢት"

ጦጤና ንዳዴ ራቅ ብለው ይመለከቱናል:: ለእኔ ናፍቆትና ጠኔ እንደሚበቁኝ ሳይወስኑ አልቀሩም:: ከተቀመጥኩበት ተነሣሁና እንኩሮዬን ከሱሪዬ ላይ አራገፍኩ::

ናፍቆት ስመለከታት ንፁህ "እናንተ ዱርዬዎች" በማለቷ ከግፍ ተቆጥሮባት ዱርዬ የተደረገች መሰለችኝ::

"ከእነሱ ጋር ብቻ ለብቻ ካልተዋጣልኝ አልገብርም" አልኩ:: ከቤት እንደመጣሁ ቢሆን አልሞከረውም ነበር:: አሁን መቶ ኪሎው አየር ከላዩ ላይ ተራግፎ ሃያ ኪሎ ያህል ቢቀር ነው:: ከፎርድ ላይ በእነእለነ እንደሚራገፈው የአክስቴ እህል......


t.me/OLDBOOKSPDF

"ኧረረረረ የሚለውን ሰማችሁ? አንድ በአንድ ይዋጣልን እኮ ነው"

ናፍቆት ነገር አግለበለበች:: እነ ጦጢ ቀረብ አሉ:: ጦጢ በጦጣኛ ሳቀ:: ትላልቅ ጆሮዎቹ እስኪንቀጠቀጡ ሳቀ:: ንዳዴ ብቻ በንቀት ፈገግ እንዳለ ያየኛል::

"ከጠኔ ጋር ይዋጣላችሁ?" አለች ናፍቆት::

ጠኔ እጁ ላይ ሞቶ በነፍስ እንደጠየቅ መሰለኝ::

"አዎ፣ ከእኔ ጋር ይዋጣልን" አለ ጠኔ::

ጠኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጣላ ሳይሆን አይቀርም:: ከእሱ ያነሰ ሰው ያገኘ ስለመሰለው::

"መጀመሪያ የምጣላው ከእሱ ጋር ነው" አልኩ ወደ ንዳዴ እየጠቆምኩ::

"አንተ ልጅ መሞት አምሮሃል?" ናፍቆት ባለማወቄ አሳዘኛታለሁ:: በጩኸት ሃሳቤን ልታስቀይረኝ ሞከረች::

"ግዴለሽም" አልኳት::

ለአፍታ ፀጥታ ወረረን:: አንዳንዴ ብቻ የበረሃ ነፋስ ሲያፏጭ ሞከሮ ሲከሸፍበት ይሰማል::

"እዛ ጥላ ሥር ይዋጣልን" አልኩና ጃኬቴን አወለኩ:: ለናፍቆት ሰጠኋት:: ናፍቆት እንደሌሎቹ አልተቁነጠነጠችም:: ፈዛ ጃኬቴን ተቀበለች:: እንደቆረጥኩ ሲገባት ፀቡን ወደራሷ ለማዞር ሞከረች::

"እናትንና ከፈለክ ከእኔ ጋር......"

"ግዴለሽም"

"ከጠኔ ጋር......"

"ግዴለሽም" ሴትነቷ አሁን መጣ ከተደበቀበት፣ ከተሸሸገበት:: በእግሯ ተነሚነጨች፣ የሞጆን እንኩሮ በእግሯ በተነች::

"እናትንና ምን ዓይነት ጅል ነው"

ንዳዴ በንቀት ፈገግ እንዳለ ቀረብ አለኝ:: አመጣጡ ጆሮዬን በቁንጥጫ ይዞ በእናትህ፣ በእናትህ ሊያስብለኝ ይመስላል:: የሹፈት ፈገግታው ከፊቱ ሳይጠፋ


t.me/OLDBOOKSPDF

"አሁን ደም እሱ ይምጣለኝ" አልኩ ወደ ጦጢ ጠቁሜ::

"እናትን!" አለች ናፍቆት እንደመባነን ብላ "ከእኔ ጋር ነው የሚዋጣልን"

"አንቺን አልችልሽም" አፈገፈኩ::

"እረፊ" አለ ንዳዴ ሳይነሳ "ከእኔ ጋር አልጨረስንም ነገ እንቀጥላለን"

ዝም ብዬ አየሁት:: ተነሥቶ ቁጭ አለ::

"ነገ ትመጣለህ?"

"አዎ"

"መጀመሪያውኑ ሳታስበው መትቶህ እኮ ነው" አለች ናፍቆት

እኔ ጃኬቴን ከወደቀበት አነሳሁ::

"እንበለው?" አለ ጦጢ:: "ለእራሱ ፈርቶ እንደሆን ገባኝ::" ብቻውን እንዳይገጥመኝ በጋራ......

ትክ ብዬ አየሁት:: ዓይኑ ሸሸኝ::

ናፍቆት ንዳዴን ደግፋ ልታነሳው ስትል አመነጫጨቃትና "አንድ ሰው እንዳይነካው" አለ::

ግንባሬን በቴስታ የገጨኝ አሞኛል:: እነሱ ፊት ግን ማሻሸት አልፈለኩም:: ንዳዴ ግንባሩ ላይ ሦስት ቀያይ ብዮች በቅለውበታል:: እራሱ የገጨበት ነው:: ሲደግፉት ሲሉ እየተመናጨቀ ወደ ባቡር ሃዲድ ሳይሆን ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ:: እኔም ወደ ሠፈር ሄድኩ::

ዓለም እንደዚሁ ናት:: ለውርደትህ እንጂ ለድልህ አትፈጥንም:: ስለፈጸምኩት ገድል የሰማም አልነበረ:: እንዳለፈው ሁኔታ ቢሆን ኖሮ አከስቴ ዞንባባ ይዛ በጠበቀችኝ ነበር:: ግን ጭር እንዳለ ነው:: ወደ እህል በረንዳ መሄድ አልፈለኩም:: ግንባሬ አብጧል:: አንድ ብይ በቅሎበታል:: ንዳዴ ግንባር ላይ ሦስት ብዮች ማብቀሌን ማን ይቆጥርልኛል?

በቀጣዩ ቀን አቤት ድረስ መጥተው አፏጩ፣ ወጣሁ:: ናፍቆት እንቢ ብዬ የምቀር መስሏት ስለ ነበር ተገረመች:: እነሱ ፊት ፊት እኔ ከኋላ ሄድን:: ብዙ


t.me/OLDBOOKSPDF

መራቅ አልፈለኩም፡፡ ይደክመኛል፣ የሞጆ አየር ይጫጊንብኛል፡፡ ከልቡሏ መውደቂያ ወጣ እንዳልን

"እዚሁ ይቀጣልኝ" አልኩ፡፡

"ለምን እዛ ሰው የማይመጣበት፣ የትናንቱን ቦታ__" እነ ጣጤ ናቸው፡፡

"እሺ" አለ ንዳዴ፡፡ ለፅብ ቸኩሏል፡፡ ጃኬቱን ሳወልቅ የእኔን ዘዴ ተጠቀመ፤ በቦክስ አከታተለብኝ፡፡ እኔም የእሱን መላ ተጠቀምኩ፣ ተለጠፍኩበት፡፡ በጉልበቱ ቆለጤን እንዳይመታኝ ጭኔን ጭኑ መካከል ከተትኩ፡፡ ሳልላቀቅ ከድንጋጤዩና ከዱላው አገገምኩ፡፡ የሚያደርገኝ ጠፍቶት ዝም ብሎ ይፍጨረጨራል፡፡ አዘናግቼ ከተለጠፍኩበት ወጣሁ፡፡ ከዚህ በኋላ መያያዝ አልፈለኩም፡፡ ከራራ ነገር ነው፡፡ ጥንክርክር ያለ፣ እንደመቀጩጩ አይደለም፡፡ እነ ጣጤ ለንዳዴ ይቶፍዛሉ፡፡

"አይዞህ ንዳዴ"

"ብራቮ ንዳዴ"

ናፍቆትን የት እንዳለች አጣኋት፡፡

ንዳዴ ለመያያዝ ሲሞክር እኔ በቦክስና በእርግጫ አስቀረዋለሁ፡፡ እንዲህ እያልን ብዙ ቆየን፡፡ ከእሱ ከሚመታው ይልቅ፣ እኔ የምመታው እየደከምኩ መጣሁ፡፡ ስለዚህ፣ በዚህ መቀጠሉ እንደማያዋጣኝ አሰቤ በቴስታ ገባሁበት በቴስታ ተቀበለኝ፡፡ የቴስታው ጫና መንጋጭላዬ ላይ ይሰማኛል፡፡ እየከበደኝ መጣ፡፡

"ልሸነፍ?"

በዚህ መካከል የአንድ ትልቅ ሰው ድምፅ ጣልቃ ገባ፡፡

"እናንተ ተው! ተው" ጋሽ በረደድ እንደሆኑ አወቅሁ፡፡ "ተላቀቁ፣ ሌባ ሁሉ! እንዴ? እንዴ? አንተ የሞጆ ወርቅ ልጅ አይደለህም እንዴ? ምን አጣላችሁ? በየትኛው እርስት ተገናኛችሁ? ብቻህን?"

ጋሽ በረደድ ከኔ ወገን ሆነው ቆሙ፡፡ ንዳዴን አየሁት፡፡ የትናንቱ እፍንጫው አገርሽቶ ደም በደም ሆኗል፡፡ ትንሽ ብንቆይ ኖሮ ከእኔ ቀድሞ እሱ በቃኝ ይል እንደነበር ገባኝ፡፡ ፊቱ ሁሉ ነፍርቋል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

እኔ ከፍል መግባቷን በሽቶዋ አወኩ፡፡ የሽቶ ምስጢር አልገባህ ይለኛል፡፡ አንዲት ሽቶ አጣጥሞ መውደድ፣ ሌላ ሲሸተት እንደገና ሌላ ሽታ? ልዩነቱን መግለጽ ግን አይቻልም፡፡ ለምን?

"አንተ? የኔ ጌታዬ?..."

ገዘም!

"ለምን ትጣላለህ! እኔ ስጨነቅ·በህ ይሻልሃል? እስኪ ፊትህ? ይሄ ግንባርህ ያበጠው..... ምን ይሻለኛል....."

"እነሱ ናቸዋ" አልኳት

"ገዘም አትላቸውም"

"ለምን?"

"እነሱ ዱርዬዎች ናቸው"

"ከፈራኋቸውኮ ያበዙታል፡፡" ዱርዬዎች፣ ዱርዬዎች፣ ዱርዬዎች... ነፁህ እንድትናፍቀኝ የሚያደርግ ቃል፡፡

"ሕግ አለኮ፡፡ እንቢ ካሉ እነ አለን አሉ· ዋጋቸውን ይሰጡዋቸዋል፡፡" እቅፍ ስታደርገኝ ሽቶዋ ውስጥ ሰመጥኩ፡፡ የአንገትጌ ጥልፏና ሀብሏ የመታቀፍ ድሎቴን ቀነሰብኝ፡፡

አከስቴ ወጥታ "ሎሚ፣ ሎሚ፣ እስኪ አጥሚት አሙቂለት፡፡ ቆንጆ አድርገሽ በቅቤ፤ ልባድርጊ...." ሄደች፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

# 5

# የወዳጅነት ተዳፋቶች

በቀጣዩ ቀን ጠዋት አከስቴ ቀስቅሳ ወደ እህል በረንዳ ወሰደችኝ:: ከአንድ ቀን በላይ የማታደርገው የሐበሻ ልብሷ ብርሃን ይተፋል:: በነጭ ብርሃን ተከብቤ አዘያው ደረስኩ:: ከአጠገቧ እንዳልለይ ጭኗን አንተርሳ ራሴን ታሻሽኛለች:: ብርሃንና ሽቶ የፅድቅ ምሳሌዎች መሆናቸውን የተቀበልኩት ከዚያች ቀን አንስቼ ነው::

ረፋድ ላይ ናፍቆት መጥታ አፏጨች:: ከእሷ ጋር ጦጤና ጠኔ ብቻ አሉ:: ንዳዴ የለም:: የእሱ አለመኖር እንድጠራጠር አደረገኝ:: ደህንነት አልሰማኝ አለ:: ንዳዴ ስለሚቆጣቸው እንጂ በእድማ ለመቀጥቀጥ አይመለሱም::

ቀስ ብዬ ተነሳሁ:: አዘናግቼ ሄድኩ::

"ንዳዴስ?"

"መጥቷል እዛ ተቀምጦ ነው" አለች ናፍቆት

"አልሄድም፣ እራሱ ይምጣ"

"እናትንና ደከሞታል፣ ሊደባደብ ነው የመጣ ልትገድለው ነው?"

ትከ ብዬ አየኋት:: እንደጎረምሳ ጭንቅላቷን ግራና ቀኝ ታማታላች:: ትቻት ልሄድ ስል

"እሺ በእናትህ" አለችኝ

እንዳለቀሰች ገባኝ "ምን?" አልኳት::

"እሉህ ይዞት ነው እንጂ .....በቃ እንሂድና አልችልህም በለው"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔ አልለውም፣ እራሱ አልችልህም ይበለኝ" አልኳት

"እናትንና፣ እሱ መቼም አይልህም ይሞታታል እንጂ ትገድለዋለህ:: በእናትህ፣ በእናትህ" እግሬ ላይ ለመውደቅ ዳዳት::

እሠፋ ጢሪሪ ትዝ አለኝ:: ላይማታ ድንጋይ የሚይዘው፣ ላይናከስ የሚያገጠው፣ ላይዘረጥጥ እግር ሙጥኝ የሚለው::

"እሺ" አልኳት

ጭንቅላቷን ግራ ቀኝ እያማታች እንባዋን ለመዋጥ ሞከረች:: እዚህ ውስጥ ምስጋናዋ እንዳለ ገባኝ::

አጥወለወለኝ:: እሷን ለማንበርከክ ያን ያህል መጓዝ ነበረብኝ? ከጎኔ ሆና እንባዋ እንዳይታይ ትጣጣራለች:: ጦጢና ጠኔ ከኋላ ይከተሉናል:: ብዙም ሳንርቅ ንዳዴን ቁሪማንቱሪ ዛፍ ጥላ ሥር ተዘረጋግቶ ተቀምጧል:: እኛን ሲያይ ተነስቶ ቆመ::

ደነገጥኩ:: ፊቱ ገርጥቷል:: ደሙ የተንጠፈጠፈ ያህል ፊቱ ላይ ሕይወት አይታይም:: ዓይኑ ጎድጉዶ አፍንጫው ድልድል ብሎ፣ አብጧል::

"ይቅርታ! አልችልህም" አልኩት::

የቆመበት እንባው ዱብ ዱብ ማለት ጀመረ:: እልህ ደረቱ ላይ ቆሞ መተንፈስ የከለከለው ይመስላል:: እጎንብሶ አፈር አፍሶ ጭንቅላቱ ላይ እየነሰነሰ አጓራ::

"እናንተ ናችሁ! ውሸት! ውሸት! አልችልህም ያለው እናንተ መከራችሁት ነው::"

ደረቱን አፈር ባፈሰበት እጁ ደቃ!

"እናትንና! አልችልህም አለ አይደለ?" ናፍቆት ተንጨረጨረች::

"በእናትህ፣ በእናትህ ይዋጣልን:: በእናትህ"

"ኡ! ኡ! ኡ!" ናፍቆት ጮኸች::

"ወይኔ ወይኔ እናታችሁን" እሷ ባሰች:: "ብትደባደቡ ሁለታችሁንም በድንጋይ ጨፍጭፌ ነው የምገድላችሁ"


t.me/OLDBOOKSPDF

ሐዘን ልቤን በሳሰከው፡፡ ወደ ንዳዴ ተጠግቼ "ያው ምታኝ፣ እኔ አልችልህም" አልኩ፡፡

"በእናትህ! በእናትህ! በእናታችሁ፣ እንደዚህ አይደለም..." እያለ በተስፋ መቁረጥ አለቀሰ፡፡ ከተንበረከከበት አንስቼ አቀፍኩት፡፡ "አይደለም፣ አይደለም፣ አይደለም"

*　　　*　　　*

የናፍቆት ፉጨት እንደቀጠለ ነው፡፡

"ፊርርርርር......"

ድንግጥ ብዬ አዞራለሁ፡፡ እጇን ከፍ አድርጋ ትጠራኛለች፡፡ እሄዳለሁ፡፡

"ጨላ አለህ?" (ሃምሳ ሳንቲም ማለቷ ነው)

"ግብር ነው?"

"ኢ..ይ፣ ንዳዴ ታሟል ከቆቃ ተራ አንዳንድ ነገር ገዝቼለት እንዲበላ ነው፡፡"

ኪሶቼ እሰጣታለሁ፡፡

ጭንቅላቷን ግራና ቀኝ እያማታች እንባዋን ለመዋጥ፣ የምትሞክር መሰለች፡፡ እዚህ ሁኔታዋ ውስጥ ምስጋናዋ እንዳለ ይገባኛል፡፡ እንዴት እንደሆን ግን ግልጽ አይሆንልኝም፡፡

"ጦጤስ?"

"እሱንም እንደዚህ ልታደርገው ነው?"

"ኸረ አይደለም፡፡" ጥፋተኛነት ተሰማኝ፡፡ "ሁሌ ካንቺ አይለዩም ጦጢም፣ ጠኔም ለዚያ ነው፡፡"

"ንዳዴጋ ናቸው" እሱ ግን አያናግራቸውም፡፡ ሁላችንንም"

"ቆቃ ተራ አብረን እንሂድ?" ስል ጠየኳት

"ለምን?"

ምክንያቱ ምን እንደሆን እራሴም አልተከሰተልኝም፡፡ ከእሷ ጋር የመሆን ስሜት ብቻ ይገፋፋኛል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

"በ...ቃ! የምትገገርበት ፍራንክ ካነስ እጨምራለሁ:: የዛሸውን እግዝሻለሁ...... በቃ!"

ናፍቆት አንገራገረች::

"ተይው በቃ" አልኳት

"ኢ...ሺ፡ ና ግን የምንሄደው ቆቃ ተራ አይደለም:: እዚያ እንጨት ተራ ነው::"

ቆቃ ተራ ፍራፍሬ የሚሸጥበት ገበያ እንደሆን አውቃለሁ:: እንጨት ተራ ግን... እንጨት ልትገዛ?

"ለማንኛውም ፍራንክ ልጨምር ቆይኝ" ብዬ ወደ እከስቴ በረንዳ ሄድኩ::

አንድ ጥንክርክር ያለ ሰውዬ ዱላውን ተደግፎ ከስቴን በብልግናና በመዳፈር ያናግራታል:: ስለሰውየው ከዚህ ቀደም ሰምቻለሁ:: ሥራው ከምንጃር፡ ከሸንኮራና ከቡልጋ አካባቢ ከብቶች እያመጣ ሞጆ ገበያ ላይ መሸጥ ነው:: ዘወትር በማስፈራራትና በመንጠቅ ጭምር ስለሚጠጣ የከብት ንግዱን የሚያካሂድበት ገንዘብ እንደሌለውና ከብቶቹን ሰርቆ እንደሚያመጣ በሞጆዎች ተደምድሟል:: ስለዚህ "በረት ገልባጭ" ይሉታል:: ከበስተኋላው፤ ፊትለፊት ግን የሚደፍር የለም::

'በረት ገልባጭ' እንደ አባቴ የተጋነነ ሰውነት የለውም:: ግን ደፋርና ባለጌ ስለሆነ ሰው ሁሉ ይፈራዋል... ይሸሸዋል::

"ምን አለ በይኝ፣ አንቺን አንድ ቀን ተሸከሜ...." ይላል:: እህል አውራጆቹ እነ እሱን ያልሰሙ ለመምሰል በመጣር ለሥራ ይጣደፋሉ:: እከስቴ ዝም ብላ በትዝብት ታየዋለች::

"አንቺን የሚደፍር ወንድ ይጥፋ? በየመጠጡ ቤት የሚወራው ስለ አንቺ፣ ግጥም የሚኾንደጎደው ላንቺ፣ ታዲያ..."

በመካከል ጣልቃ የምገባበት ነገር አጣሁ እከስቴ ጥልፏና ወርቋ እየተብረቀረቀ እሷ ደብዝዛ ተቀምጣለች:: ነገር ሳጣ በእካል ሁለቱ መካከል ቆምኩ:: እከስቴ ለብ ባለ ፊት እየችኝ::

t.me/OLDBOOKSPDF

"ትምህርት መቼ ነው የምጀምረው?" አልኳት

"ሲከፈት፣ ደርሷል"

በረት ገልባጭ በእጁ ገሸሽ ሊያደርገኝ ሞከረ:: ዞሬ አፈጠጥኩበት:: አባቴ የፈለገ ትልቅ ቢሆን ለፀብ የከጀልከውን አይኑ ውስጥ እየው:: በፍፁም አይንህን እንዳታረግብ:: ካረገብክ ለውሻ የመሮጥን ያህል አደገኛ ነው ይለኝ ነበር የበረት ገልባጭን እንደ ቋጥኝ የከበደ ዓይን ማቀፊያ ሰርስሬ በመግባት ብሌኑ ላይ አፈጠጥኩ::

ገሸሽ ለማድረግ የሞከረበት እጁ ተንከርፍፎ ቀረ:: ዓይኔን አልነቀልኩም:: መጀመሪያ እሱም ለማፍጠጥ እና የእኔን ዓይን ለመስበር ሞከረ፣ ቀጥሎ ተደናገረ፣ በመጨረሻ ግን ዓይኑ ሲንበረከክ ታወቀኝ:: መፋጠጥ እንደመታገል ነው::

"የእነትሽን ልጅ አዋቂ ሲጫወት ዘወር እንዲል አላስተማርሽውም?" አለ::

"እንዴት አይነት ጨዋታ?" አልኩት ለመጀመሪያ ጊዜ ትልቅ መሆንን አጥብቄ ተመኘሁ::

"ኸረ ይሄ የእንጭቅ ልጅ" አለኝ::

እንጭቅ ምንድነው?

አክስቴ የማይቀረውን ፀብ ለመቀበል ተነሳች::

"ኸረ ተው ማናዬ፣ ትንሽ ልጅ ምን አድርግ ትላለህ? ግፍ አትፈራም? ቀና ብሎ አሉን ማየት ደግ ነው::"

ጠቋሚ ጣቷን ወደ ላይ ሳትቀስር አልቀረችም:: እኔ ሙሉ ኃይሌን ዓይኔ ላይ አድርጌ በረት ገልባጭ ዓይን ውስጥ ገብቻለሁ:: ዓይኑን መለስ ቀለስ እያደረገ ተንቆራጠጠ::

የእፍታ ፀጥታ ተቆጣጠረችን::

"ቆይ" አለ::

እኔም በፊቴ ንቅናቄ "ቆይ" አልኩት::

ይሄን ጊዜ የአክስቴ አህል አውራጆች መካከል ገቡ:: "ተው እንጂ ጋሽ ማናዬ" ሁኔታቸው ግን እንደ ንግግራቸው ትሕትና የለውም:: ገፋ፣ ገፋ ያደርጉታል:: እኔ በቀደድኩት እንደገቡ አወቅሁ::

t.me/OLDBOOKSPDF

"ጥሩ፣ ጥሩ፣ ጥሩ......" እያለ ሄደ፡፡፡

ሙሉ የእህል ተራ ነጋዴና ሸማች እኛ ላይ እንዳፈጠጠ አየሁ፡፡

ናፍቆትም መጥታ አበረንዳው ሥር ቆማ ነበር፡፡ ይዤ ልሄድ ያሰብኩትን ሳንቲም ከአክስቴ ገረወይና ውስጥ ማውጣት ስላስፈራኝ እንሂድ ብዬ አስከተልኳት

"ወዴት? መኪብቤ? አንተ?" አክስቴ ነበረች፡፡

"እዚህ ነኝ፡፡" አልኳት አክስቴ ሁኔታዎች ተምታተውባት እንደቆመች እና ናፍቆት ሄድን

"መኩብቤ ልባድርግ፣ አንዷች ብለህ......"

የገበያውን ሰው ዓይን ሸሸሁ፡፡

በረት ገልባጭ ላይ ያፈሰስኩት ኀይል ልቤን እየንተተኝ ነው፡፡ ቁና ቁና እተነፍሳለሁ፡፡

"በቃ ተመለስ እኔ እሄዳለሁ" አለች ናፍቆት

"ግዴለሽም፤ ግን ብዙ መግዛት ትፈልጊያለሽ? ተጨማሪ ፍራንክ ሳልይዝ..."

"ኢ..ይ፣ ዳቦ እንገዛና ሻይ እናፈላለታለን"

"ከዚያ በፊት ምን ለመግዛት አስበሽ ነበር?"

"ሁለት እንጀራ፣ ሽሮ፣ ሽንኩርትና ዘይት"

"እናቱስ?"

"የእኔ አክስት ናት፡፡ የሚበላ ትከለክለዋለች፡አትወደውም"

ግራ ተጋባሁ፡፡ እናት፣ ባይሆን እንደ እኔ እናት ምግብ አታጣፍጥም እንጂ ትከለክላለች? እንዴት ለእሱ ሳትሰጥ ለራሷ ትበላለች እንዴት? ግራ በግራ ሆንኩ፡፡

"አክስቴ ንዳዴን አትወልደውም፡፡ የእንጀራ ልጇ ነው፡፡ በዚህ ላይ አባቱ ጥሎት ጠፍቷል በቃ!" ጭንቅላቷን ግራና ቀኝ አማታች፡፡ እንዳዘነች ገባኝ፡፡ እንዴት? እንጃ!

ከድብድቢ ውጪት ጋር በተለየ መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ተዋወቅሁ ማለት እችላለሁ፡፡ በጥቃት፣ በእልህ፣ በቁጭት፣ በበቀል የምናካሂደው ድብድብ ውጤት

t.me/OLDBOOKSPDF

ኩብር ስንለው በወዲያ በኩል ውርደት ሊሆን እንደሚችል ተገለፀልኝ:: ከነዳይ ጋር የገጠምኩት እንሼ መታየትን በመጥላት ቢሆንም አሸንፌም ከትንሽነት እንዳልወጣሁ እዚህ ቆሜ ገባኝ:: ተሯሩጦ እራሱን የሚያስተዳድርን ባተሌ ሰንከሎ በቁስልና በረሃብ መቅጣት እንዴት ያለማነስ ምልክት ሊሆን ይችላል? እራሴን ጠላሁ፤ ሰው መሆንን አነወርኩ፤ በሴት መመታትን በመፀየፍ የደነገጉትን ተፀየፍኩ::

"እዚህ ጠብቂኝ" ብዬ ወደ አከስቴጋ ሄድኩ:: አስባ ስለነበር ስሄድ ደስ አላት:: እቅፏ ሽቶዋ ውስጥ አሰጠመችኝ:: ጭኗ ላይ አስተኝታ ጭንቅላቴን ለመደባበስ ስትሞክር ከገረወይና ውስጥ ድፍን አስር ብር አንስቼ ስሜያት ሄድኩ::

ናፍቆት ሴታ ሴት ወንድ መስላ እንደቆመች አገኘኋት:: በፊት ወንዳወንድ ሴት ትመስለኝ ነበር:: ሁለቱ ያን ያህል ለውጥ አለው? ፀሐይ ያጠቋቆረው ቅላት ይታየኛል:: የፈረንጅ ጋዴ ጫማ አድርጋለች:: ጥልፍልፉ መጫሚያዋ እግሯ ላይ የሚኮምከ ይመስላል:: እረጃጅም የእግር ጣቶች አሏት:: የሞጀን አንኩሮ አፈር ቅመውም ያማምራሉ:: አስር ብሩን ሰጠኋት::

"እንዴ? ይሄ ሁሉ? ምንድን ነው?"

"ቅድም ያልሸውን ግዢ:: ሥጋ ግዢ፤ እንደውም የጎድን እጥንት ገዝተሽ ሾርባ ስሪለት፤ እ? ደሞ ቆቃ ተራ ሄደሽ ብዙ ዓይነት ፍራፍሬ ጨምሪለት፤ ነገም ስለምሰጥሽ አትቆጥቢ::"

ጭንቅላቷን በጎረምሳ ትዕቢት ስትነቀንቅ አመሰግናለሁ የሚል ፍቺ ሰጠኝ እንዴት? እንጃ! እኔ ቀረሁ፤ እሷ እየሮጠች ሄደች:: ለምን እንደሆን ሳላውቀው "ንፁህ፤ ንፁህ፤ ንፁህ፤ የሚል መዝሙር ከልቤ ሲፈልቅ ተሰማኝ:: ብዙ ትርጉም ያለው የአንድ ቃል ስንኝ፤ የአንድ ቃል ቅኔ፤ የአንድ ቃል ማኅሌት....እለ?- እንጃ!


t.me/OLDBOOKSPDF

# 6

# የሞጆ ስርጓጉጦች

የሞጆ አድባር ተቀበለኝ፣ ወይም እኔ የሞጆ አድባርን ተቀበልኩ:: ከእነ ናፍቆት ጋር አዞራለሁ:: ጦጢ አሁንም አላመነኝም:: ነገር ፈልጌ ቂሟን እንደምቀጣበት ያስባል፣ ይጠነቀቃል::

የሞጆ ልጆች ጨዋታ ከግንፍሌዎች ጋር አይገጥምም:: ባቡሩ ከድሬዳዋ ሲመጣ ወይም ከአዲስ አበባ ሲሄድ ሞጆ ላይ ጥቂር ቅልጥም መስሎ ይጋደማል:: ሎሚ፣ ቆሎ፣ ብስኩት..... የሚሸጡ የሞጆ ልጆች እንደ ጉንዳን ይወርሩታል:: እነ ጦጤ ይሄኔ እየተዟዟሩ ፉርጎውንና ተሳፋሪዎቹን ይቃኛሉ:: ጠኔ የሚቃኘው የሚበላ የያዙ ሰዎችን ነው:: ጦጤ የሚቃኘው የሚሸጥ ነገር የያዙትን ነው::

ባቡሩ የሞጆ ኬላ ግዴታዎቹን ተወጥቶ ሊንቀሳቀስ ሲል እነ ጦጤ ቀድመው ይሮጣሉ:: ባቡሩ ሲደርስባቸው ጥልጥል ይሉና ቅድሚያ የሰለሉትን ነገር ነጥቀው ይወርዳሉ::

ጦጤ ሻሽ፣ ነጠላ፣ ስካርፕ፣ የቤት ቦርሳ፣ ፎጣ.... ይነጥቃል:: ጠኔ ደግሞ ቸርኦሊያ ብስኩት፣ ሸንኮራ፣ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ጎድጓዳ ሰሃን ከነ ምግቡ.... ይመንትፋል:: የጠኔ ይበላል፣ የጦጤ ይሸጣል::

ናፍቆት በጠኔ ትበሳጫለች::

"ጃኪት አትነጥቅም? ሱሪ አትመንትፍም? ቲሸርትና ጃለቢያ አይጌህ እያይም? እናትንና ሁሌ ምግብ!"

ጦጤ የነጠቀው ጨርቅ ተራ ተወስዶ ይሸጣል:: የተገኘው ነገር ላይ የተለየ የባለቤትነት መብት የሚያነሳ የለም:: ለተፈለገው ነገር ናፍቆት ታውለዋለች::

t.me/OLDBOOKSPDF

"የጦጢ እናት ቸስተዋል ይሰጣቸው"

"ይሰጣቸው"

"የጠኔ ጫማ አልቋል ሞጋ (ከመኪና ጎማ የሚሠራ ጫማ) ይሠራለት::

"ይሠራለት"

የንዳዴን ወጪ እኔ ስለምሸፍን ለእሱ ማሰብ ቀርቷል::

ሞጆን ከሞጆዎች ጋር አሰስኳት:: ቁጠባ እንሄዳለን:: የሞጆ ቆዳ ፋብሪካ ሠራተኞች መኖሪያ በመሆኑ ቀን ቀን ጭር ይላል::

ብዙ የተንኮል ሥራዎችን እንሠራለን:: አንዳንድ ዝንጉዎች ውጭ የተውት ዕቃ ካለ እንሰርቃለን:: ካዛሚር ከደረሰ ለመብላት፣ ካልደረሰ ለመደባደቢያነት እንቀጥፋለን:: የቧንቧ ውኃ ከፍተን እንራጫለን:: አመድ ካገኘን እንነሰንሳለን::

ከዚያ ኮልባ ሠፈር ሄደን ጊዮርጊስን እንሳለማለን:: ከኮልባ ሠፈር ቀጥታ ወደ ጦጣ ካምፕ እናመራለን:: ጦጣዎች አይተን ባናውቅም በቁልቋል አጥሩ እያሾለቅን::

"ያቺት አንድ ጦጣ" እንላለን

"የታለች? የታለች? እውነትም!" (ባይታየንም) አካባቢው ጦጣ ካምፕ የተባለው በፊት ጦጣ ስለሚረባበት ነበር ይባላል:: ጦጢ የተወለደው ከዚህ ነው እያልን እናሾፍበታለን:: እውነትም የጦጣ መልክ እና ድርጊት አለው:: ባቡር ላይ ሲንጠላጠል ቅልጥፍናው የጦጣ በመሆኑ ነው ጦጢ የተባለው::

"እነዚህ ደሞ አማረብን ብለው ነው እንዴ?" ይለኛል:: እኛ ብቻ ሳንሆን የጦጢ ብለው ነው'ዴ?" ይላል ጦጢ ልምዱ ይኼው ነው:: እናትም፣ ልጃቸውን ሲያበሽቁ "ልጄን ያገኘሁት ጦጣ ካምፕ ነው" ይላሉ::

ጦጢ "ይቺ ደሞ" ይላል "አማረብሽ መሰለሽ?"

"ኸረ የት አባቱ ሊሰድበኝ ነው እንዴ?" ለማስፈራራት አፈፋንም ምኑንም ይቧጥጣሉ፣ ይሸሻል::

"አማወይ" እንላቸዋለን::

"ምናባታችሁ"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ጦጤን የት አገኙት?"

"ምን እነዚህ ደሞ፣ አማረብን ብላችሁ ነው?"

ይነጫነጫል:: ጦጤ ከዚህ ያለፈ የከፋ ነገር ሲናገር ሰምቼው አላውቅም:: አንዳንዴ ያስቀኛል:: መጥፎ ነገር ያደርግና ምላሽ ሲሰጠውም "ምን እነዚህ ደሞ አማረብኝ ብለው ነው'ንዴ? ይላል::

አንድ ቀን እየተሳሳቅን ወደ አንዲት ሴት ቀረብን:: ጦጤ ድምፁን አቅጥኖ "ስምና ቂጥ" አለ:: ሴትዮዋ ጥሩ የሚባል አይነት ቂጥ ይኑራት እንጂ የይጋርዱ ቂጦን ያየ የዚችኛዋ ምኑም አይደለም:: ሴትዮዋ ተናደደች:: የበለጠ ቂጧን እየነቀነቀች "ከዚህ ጋር አውራ" ብላ ወደ መቀመጫዋ በጣቷ ጠቆመች::

ጦጤ ደስ ብሎት ይፍነከነካል::

"ስምና ቂጥ" ጦጤ

"ከዚህ ጋር አውራ" ሴትዮዋ

ለምንድን ነው ስምና ቂጥ የምትላት?" ብዬ ጦጤን ጠየቅኩት::

"ስምና ቂጥ ብቻ ነዋ ያላት" አለኝ::

"ስሟ ማነው?"

"ሲኞሪና"

ገረመኝ::

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነው ጦጤ ያቺ ሴት የምትገኝበት ቦታ ወሰደን::

"ስምና ቂጥ" ይላታል::

ሴትዮዋ "ከዚህ ጋር አውራ" አላለችውም:: ሌላ መልስ አዘጋጅታ ጠበቀችው:-

"ጦጣና መላጣ" አለችው::

ጦጤ ያልጠበቀው ምላሽ ስለሆነ ደነገጠ:: እኛን አየ:: ሁላችንም እየሳቅን ነበር::


t.me/OLDBOOKSPDF

የእነ ንዳዴ ቤት ጭልምልም ያለ ነው፡፡ የእኛን የማንፍሌ ቤት ያስታውሰኛል፡፡ ምናልባት እናቴ እዚህ ቤት አድጋ ይሆናል ቤታችንን ያጨላለመችው እያልኩ አሰባሁ፡፡ ብዙ ጊዜ የንዳዴ እንጀራ እናት ቤት ውስጥ አትኖርም፡፡ በውኃ የሳሳች ነጠላዋን ተከናንባ አመሻሽ ላይ ትመጣለች፡፡ አፍንጫዋን በንቀትና አጥብቆ በማሽተት ሰቅላ ታልጎመጉማለች፡፡

"ሌማት ከፍታችሁ እንደሆን ዛሬ ውርድ ከራሴ ነው"

ንዳዴና እንጀራ እናቱ መልካቸው መመሳሰሉ አስገርሞኝ ልሞት፡፡ ጓዳ ገብታ እንጀራዋ አለመበላቱን ስታረጋግጥ ሌላ ማልጎምጎም ጣል ታደርጋለች፡፡

"ብቻ ሰርቃችሁ በሌባ ተቀባይ እንዳታሳስሩኝ"

"ሰርቀን ባሳሰርናት" የሚል ምኞት ያድርብኛል፡፡

ስለ ከፋቷ በደግነት ማቁሰል ያሰኘኛል፡፡ እንድትሰማ አድርጌ

"የሚበላ አትሰጪያትም?" እላለሁ ናፍቆትን "ብርቱካንም፣ ፓፓየም፣ ዘይቱናም...... ከእንጀራውም ስጪያት"

"ልስጥሽ አክስቴ?" ትላታለች፡፡

በከፋ ዓይኗ እኔን እያየችኝ ልታሳፍረኝ ትሞክራለች፡፡ አይኔን ሳላረግብ አፈጠጥኩባት፡፡

"እዛው እናንተ አቡኩት" አለችና ነጠላዋን ከላይዋ ላይ ገፍፋ ወደጓዳ ወረወረችው፡፡ እግሯ የሞጀን እንኩሮ ቅሟል፡፡ የት ደርሳ መጥታ ይሆን? ዓይኗን ከዓይኔ ላይ ሳትነቅል ወጥታ በር ላይ ተቀመጠች፡፡ እኛን ሽሽት ይሁን ሌላ ጥበቃ አልተገለጸልኝም፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

# ፯

## ሙና እንደገና

አንዳንድ ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭም መምህርት ሙናን አስባታለሁ፤ በጥላቻ:: አእምሮዬ ያላግጥባታል:: ያመናትላታል::

"መ" እና "ና" እንዴት ሆነ ሙና? ሒሳብ ትምህርት ማለት ይሄው ነው:: ሥራ ላለመፍታት ቆብ ቀድዶ መስፋት:: የሙናን ስሌታዊ አመጣጥ አሰረዳ ከተባለ ደግሞ፡-

ሙና ይሆናል ምንሚና:: ምን..ምን እንዲሁም ምን...ምን፤ በመቀጠል ሙንን.. ሙንን ስትል በመታየቷ ሙንንዬ ተባለች:: "ሙንንዬ" አንድ "ን" ቀንሰው "ሙንዬ" አሏት:: ሙንዬን ቋሚ ስም ለማድረግ "ሙና" ተባለ::

መልመጃ አንድ (ፕሮብሌም)

ሙና ምንሚና ያሉዋት ሃሳን አይተው ነው? ቀሚሷን? ሻሿን? መነፅሯን? እሷ እንደሆን የተወለደችው ከእነ መነፅሯ ነው:: መነፅሯ ከፊቷ ጋር የሚያድግ በመሆኑ አልለወጠችውም:: ብቻ መነፅሯ ስለደላው (ስለተመቸው) እድገቱ አጥፍ ሆኖ ፊቷን ሊሸፍን ከንፈሯ ብቻ ቀርቶታል:: ይሄ አልቅት መነፅር::

ክፍል ውስጥ አይታዋን ለማደናገዝና መነፅሯን እንድታወልቅ ለማስገደድ ሙብራት አጥፍቼ መስኮቱን በሙሉ እዘጋለሁ:: እሷ ግን የገባችበትን በር በልቅጣ ትተውና ጭንቅላቷን በእኔ ተቃራኒ አድርጋ እይኗንና ነገሯን እኔ ላይ ትተክላለች::

"የተንከል ይመስላል፤ መስኮት ከፈቱ ወይም ሙብራት አብሩ" ትላለች፤ ድምጿ የእሷ አይመስልም:: ዓይን ጨፍነው ሲያዳምጡት በደመና ላይ የምትንሳፈፍ ቆንጆ ሴት ለዓይነ ኅሊና ትቀርባለች::



t.me/OLDBOOKSPDF

# 7

## ሙና እንደገና

አንዳንድ ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጭም መምህርት ሙናን አስባታለሁ፤ በጥላቻ:: አለምሮዬ ያላግጥባታል:: ያሙናትላታል::

"ሙ" እና "ና" እንዴት ሆነ ሙና? ሒሳብ ትምህርት ማለት ይሄው ነው:: ሥራ ላለመፍታት ቆብ ቀድዶ መስፋት:: የሙናን ስሌታዊ አመጣጥ አስረዳ ከተባለ ደግሞ:-

ሙና ይሆናል ምንሟና:: ምን..ሞን እንዲሁም ሞን...ሞን፤ በመቀጠል ሙንን.. ሙንን ስትል በመታዩቷ ሙንንዬ ተባለች:: "ሙንንዬ" አንድ "ን" ቀንሰው "ሙንዬ" አሏት:: ሙንዬን ቋሚ ስም ለማድረግ "ሙና" ተባለ::

መልመጃ አንድ (ፕሮብሌም)

ሙና ምንሟና ያሉዋት ፁኗን አይተው ነው? ቀሚሷን? ሻሿን? መነፅሯን? እሷ እንደሆነ የተወለደችው ከእነ መነፅሯ ነው:: መነፅሯ ከፊቷ ጋር የሚያድግ በመሆኑ አልለወጠችውም:: ብቻ መነፅሯ ስለደላው (ስለተመቸው) እድገቱ እጥፍ ሆኖ ፊቷን ሊሸፍን ከንፈሯ ብቻ ቀርቶታል:: ይሄ አልቅት መነፅር::

ከፍል ውስጥ አይታዋን ለማደናገዝና መነፅሯን እንድታወልቅ ለማስገደድ መብራት አጥፍቼ መስኮቱን በሙሉ እዘጋለሁ:: እሷ ግን የገባችበትን በር በልቅጣ ትተውና ጭንቅላቷን በእኔ ተቃራኒ አድርጋ አይኗንና ነገሯን እኔ ላይ ትተክላለች::

"የተንኮል ይመስላል፤ መስኮት ከፈቱ ወይም መብራት አብሩ" ትላለች፤ ድምጿ የእሷ አይመስልም:: ዓይን ጨፍነው ሲያዳምጡት በደመና ላይ የምትንሳፈፍ ቆንጆ ሴት ለዓይነ ኀሊና ትቀርባለች::



t.me/OLDBOOKSPDF

"የቤት ሥራ ያልሠራ?" እጅ እናወጣለን:: ተሽቀዳድሜ የማወጣው እኔ ነኝ:: የነጠላ ወረቀት ጠርዝ በመሰለ ከንፈሯ ትንቀናለች::

"እሺ አውርዱ"

ለምን ፊቷ ወደ እኔ አይዞርም? ለምን ሰርቃ ታጤነኛለች? ለምንስ ትኩረቷን መንፈግ ፈለገች? ዓይኗ የሚናገረው ምንድነው? ነው ወይስ ፍትፍት ያለ አስቀያሚና ዘግናኝ፣ አሰፀያፊ በሽታ ያኮላሸው ዓይን ነው ያላት?

"መጽሐፍ ያልያዛችሁ?"

አሁንም እኔ አንደኛ ነኝ እጅ ሳወጣ::

"እሺ አንተ ከእሱ ጋር፣ አንቺ ከእሷ ጋር...... አንተ ደሞ ከእሷ ጋር..." መጽሐፍ ያልያዝነውን እንደጎራዴ አስፈሪ ስለት ባለው ከንፈሯ ታሸሚጥጠናለች::

ከንግግር ውጭ ያለ መግባቢያ ሁሉ መጠፋፊያ እንደሆነ አውቃለሁ::

ካስረዳችን በኋላ የክፍል ሥራ ትሰጠናለች:: ስንሠራ እየዞረች ታያለች:: ከጀርባዬ ቆማ ደብተሬን ለመመልከት ስትሞክር የመተኛት ያህል ክልያት አፅፋለሁ::

"ለምንድነው?" ትለኛለች::

"ሳልጨርስ ሲመለከቱብኝ አልወድም" እላታለሁ:: በነጠላ ከንፈሯ "ጉረኛ" ብላኝ ትሄዳለች:: ሆኑ ብዬ ሒሳብ ስለማጠና የእልሄ ትምህርት ሆኗል:: ቀድሜ አሳያታለሁ:: ኢክስ ካለ ብቻ የጥያቄ ምልክት አድርጋ ትመልስልኛለች::

"ይሄን እንደገና ሞክር" ትለኛለች::

በመነፅሯ ማዕዘን በኩል ዓይኖቿን ለመመልከት ስለምጥር ያለችኝን አልሰማም::

"ለማኸኝ? ጥያቄ ምልክት ያደረኩባቸውን እንደገና ሞክር:: ጠፍቶህ ሳይሆን ስለቸኮልክ የሳትካቸው ናቸው::"

በሚቀጥለው ክፍለ ጊዜ ቀድሜ ብሠራም ቀድሜ አላሳያትም:: መጨረሻ ከተደወለ በኋላ ወደ እኔ መጥታ


t.me/OLDBOOKSPDF

"ዛሬስ ከበደህ?"

"አልከበደኝም"

"ታዲያ?"

"ሁሌ አንደኛ መሆን አይሰለችም?"

በብረት ምጣድ ጠርዟ "ጉረኛ" ትለኛለች:: እንዴት ገባኝ? እንጃ!

"ትናንት አልመጣህም፣ ለምን?"

"ሁሌ መምጣት አይሰለችም?"

የከንፈሯ ሜፍ ብቻውን ሲንቀሳቀስ አየሁት:: ይሄኔ "ጋጠወጥ" ነው ያለችኝ:: ስለምን በንግግር ለመግባባት አትሞክርም? በመዋኛ መነፅሯ በትክታ አይታኝ ለመሄድ ከቃጣች በኋላ መለስ አለች::

"ችግር ወዳንተ ከመምጣቱ በፊት ለምን በግድ ትጠራዋለህ?" አለችኝ፡፡

ድል የመታኋት ሆኖ ተሰማኝ፡፡ አንድ ቀን ደግሞ መነፅሯን አስወልቃታለሁ:: የሰሜት ምሽጓን አፈርሰዋለሁ::

"መነፅሯ ሊወልቅ ይችላል ያልኩበትን ሁሉ ለመሞከር ቆርጬ ነበር፡፡ እና ጦጤ ግን አልተባበር አሉኝ፡፡ ስትሄድ እየተባረርን ከኋላዋ መገፍተር::

"እረ በለው! ከእሷ አይን ምን አለን?" አለ ጦጤ

"መነፅሯ አይበላ፣ አንሸጠው....."አለ ጠኔ

"ይኼ ደሞ አማረብኝ ብሎ ነው እንዴ? የከሸፈ እቅዴ በእንቅልፍ ልቤ የሚያባትት ቅዠት ሆኖ በተደጋጋሚ ይታየኛል:: እኔና ጦጤ እየተባረርን ስንገፈትራት መነፅሯ ወልቆ ዞር ስትል በዓይኖቿ ፋንታ ሁለት ጥልቅ ጉድጓዶች ይጋረጡብኛል::

ሁለተኛው ዕቅዴ በምሽት ቤቷ ሄዶ በርዋን መቆርቆር:: ጭለማ ስለሚሆንባት የግዷን መነፅሯን አውልቃ ትወጣለች:: ይሄም ዕቅድ ቅዠት እንጂ እውን ሲሆን አልቻለም:: ብቻዬን በራፏ ላይ ቆሜ ስቆረቁር በሩ ተከፍቶ


t.me/OLDBOOKSPDF

ከመምህርት ሙና ዘለግ ያለች ሴት ትወጣለች። መነፅሯ ሻሿ፣ ቀሚሷና ጫማዋ ግን የመምህርቷ ነው። መነፅሯን ስታወልቅ እናቴ ትሆናለች። ያ ጥልቅ ጉድጓድ የአይኗን ማቀፊያ ሞልቶት።

ይሄን ቅዠት ባየሁ ማግስት አንዳች አስደንጋጭ ግጥምጥሞሽ ተከሰተ። መምህርት ሙና የክፍል ሥራ ሰጥታን እየተንጎራደደች እኔ መቀመጫጋ ደረሰች። ደብተሬን ለማየት ስትሞክር ለጥ ብዬ ጋረድኩባት። በዚህ መካከል እንዲህ ስትል ጠየቀችኝ።

"ትናንት እኔ ቤት መጥተህ ነበር?"

መልስ መስጠት ተሳነኝ። እባው ለጥ ያልኩበት ሟሟሁ። መልስ ሳትጠብቅ ሄደች። አጋጣሚ ወይስ በምናምኑ የተወታተፈ ዓይኗ የሰው ሀልም አሻግሮ ይማትራል? ፈራኋት።

እሷን መፈታተኔም በፍርሃት ጋብ አለ።

*   *   *

የእኔ መፈታተን ጋብ ሲል መምህርቷን እኔን እንድትፈታተን ሳይገፋፋት አልቀረም። አንድ ቀን ከፍለ ጊዜው እንደተጠናቀቀ ጠርታኝ ወጣች። ሞት ሞት ከሚሸት መነፅሯ ጋር መፋጠጡን ብጠላም ታዘዝኳት። ስታናግረኝ አልቆሶችም።

"የሚኒስትሪ ዝግጅት እንዴት ነው?"

"ምን መዘጋጀት ያስፈልጋል? ዝም ብሎ መፈተን"

ተቃውሞዋን ጠብቄ ነበር። ፀጥታዋ የእናቴ ሳይሆን የአክስቴ ነው። ሁሉንም የመቀበል...

"ምን ስታደርግ ትውላለህ?"

"ስዞር፣ ባቡር ላይ ስንጠላጠል፣ ስነጥቅ፣ ስደባደብ...."

"ሁሌ እንደዛ ማድረግ አይሰለችም?"

የአራሲው ዱላ አራሴ ላይ ተሰነዘረ። ይቺ ሴት ከእኔ የምትፈልገው ምንድነው? የገዛ ጥያቄዬ መልሶ መልስ እኛ ላይ ተሰነዘረ። እኔስ ከእሷ የምፈልገው ምንድነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

አጥቷል፡፡ በመጨረሻም በፍቅር አምባ ጓሮ የተነሣ ፍልሚያ ገጥሞ ገና በሃያ ሁለት ዓመቱ ሞቷል፡፡ እንግዲህ ዝናው መናኘት የሚጀምረው እሱ ከሞተ በኋላ መሆኑ ነው፡፡ ደስ ያለኝ ነገር ቢኖር ግን በጠላትነት የቆየ መምህሩ ሳይቀር በተማሪው ተሸንፎ የሰጠው አስተያየት ነው፡፡

"እንግዳ የሆነ ልጅ በእርግጥም እንግዳ የሆነ" ነበር ያለው፡፡

ይቺን ቃል ከመምህርት ሙና ለማግኘት እስከ የት ድረስ መጓዝ ይኖርብኝ ይሆን? ደግሞስ ይሄን ሳታገኝ በሃያ አንድ ዓመትህ ትሞታለህ ማለቷ ይሆን? ሞት ምንድነው? ስምህ ምድር ላይ የት እንደደረሰ አለመረዳት ይሆን? ጣጣህን ሁሉ እንደ ሥጋህ አውልቀህ ወዳልታወቀ አቅጣጫ መኰብለል ይሆን? ጋሎይስ በሕይወት እያለ ዝናውን ቢያገኝ ከሞተ በኋላ የሚኖረው ጥቅም ምንድን ይሆን? ለመሆኑ እኔ ለሚችቱ እናቴ ምንድነኝ? ከአካሏ ጋር እዚሁ የቀረሁ? የተረሳሁ? ምድራዊ ጣጣዋ ብቻ?.......

እ..ሁሁሁሁ....... መምህርት ሙና ከነበርኩበት ዕድሜ፣ ቦታ፣ ጉዳይ.... አውጥታ የት ጣለችኝ? ሰው፣ አቅጣጫ፣ ድንበር..... የሌለበት ጭው ያለ የሐሳብ ምድረ በዳ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF .

# ፰

# ተሰናባቹ ልጅነት

ጦጢ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት ልጅ አይቶ ደነገጠ፡፡ አደነጋገጡ የሚያስደነግጥ ነበር፡፡ የተደነገጠባት ልጅ ከአዲስ አበባ ወደ ድሬዳዋ በባቡር የምትጓዝ የጸኛ አኩያ ነበረች፡፡ በስስ አስካርፕ ፊቷን ከብባ ፈገግ ብላ ታየን ነበር፡፡ የመግቢያ መንጠልጠያ ብረቱን ይዛ በሩ ላይ ቆማለች፡፡ ባቡሩ ሲንቀሳቀስ ጦጢ እንደ መባነን ብሎ ተከትሎት ሮጠ፡፡ የኋለኛውን ፉርጉ ይዞ ተንጠላጠለና ከፍርጎ ፉርጎ ተሸጋግሮ ልጅቷ ያለችበት ደረሰ፡፡ አስካርፕዋን ይገፍፋታል ብለን ስንጠብቅ ከንፈሯ ላይ ስሟት ወረደ፡፡

ዝም ተባባልን፡፡ ናፍቆት "አናትንና!" ትላለች ብሎ ስንጠብቅ አንገቷን ደፍታ መንገዷን ቀጠለች፤ ንዳዴ ምንም እንዳልተፈጠረ ሁሉ በተረጋጋ ፈገግታው ታጅቦ መሬት መሬት አየ፡፡ ጠኔ ብቻ ይነጫነጫል፡-

"አንድም የሚበላ የያዘ የለም"

ትናንት ስካርፕ ፍለጋ መጣን ከንፈር አልታየንም ነበር፡፡ ዛሬ ምን ተፈጠረ? እድሜያችን ላይ በትናንት እና በዛሬ መካከል ምን ተደንግጉብን ጠበቀን?.....

..... ለምንስ እኔና ናፍቆት መተያየት ተሳነን? ጦጢ ውስጥ የተፈጠረውን ፍላጎት ያለ ጥያቄ እንዴት ተረዳችው? እሷም ውስጥ ጉዳዩ አለ ማለት ነው?....

.... እኔምኮ የጦጢ አገዛማሚያ ያለ አስረጂ ገብቶኛል፡፡ ዛሬ ሴት የምመኘው ቀደም ሲል ንፁህን ስመኝ በነበረበት መንገድ አይደለም ይሆን?

"ዛሬ ቅዳሜ ነው" አለች ናፍቆት "ከብት ገበያ ሄደን የበረት ገለባዎን በሬ እናስፈርጥጥበት" ካለንበት የጋራ መደናገር ለመውጣት የታሰበ ይመስላል፡፡

"እኔ ቤት ገብቼ እተኛለሁ" አለ ጦጢ.



t.me/OLDBOOKSPDF

ከንፈር መሳም እራስ ያሞቃል? ያደክማል? ሆድ ይቆርጣል? ወይስ ምን?

ጣጤ ለመጀመሪያ ጊዜ እራሱን ደፍቶ ሄደ:: እኛም የበሬ ቂጥ የምንወጋበትን መርፌ እንጨት ላይ አስረን ወደ ከብት ገበያ ሄድን:: በሬው ደንበሮ፣ በረት ገልባጭ አብሮ ሮጦ፣ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ጭራውን ይዞ መሬት ለመሬት በደረቱ ተንፏቆ፣ ፊቱ ተጋግጦ፣ በሬው ተይዞ ወደየቤታችን እስከንመለስ ድረስ "ጣጤን ያነሳ ጣጤን ይሁን በሚለው ባልተነጋገርንበት የልብ ውል እንደጸናን ነበር። ጣጤን መሆን አይቀርልን ይሆን?

* * *

ልጅነት የተሸኘው ጣጤ ልጅቷን ሲስም እንደሆነ አድርጌ ደምድሜ ነበር:: ግን ሌላ የዕድሜ ኪላ ደግሞ በመምህርት ሙና መጽሐፍ በኩል መጣ:: ከማንበቢ በፊትና በኋላ ተመሳሳይ ዕድሜ ላይ ነበርኩ ማለት ይከብደኛል:: ለማንበብ ወደ ክፍሏ ስገባ የነበረኝ ግብ፣ አንብቤ ስወጣ ተቀዛቅዞ ነበር:: መጽሐፉን ስመልስላት መምህርቷ ተደንቀች ስትቀበለኝ.... "አንብበኩት እንዳትለኝ?" አለች::

"አዎ" በኩራት

"የጋሎይስ ሀገር የት ነው?" መፈተን ወይስ መፈታተን?

"ፈረንሳይ"

"በስንት ዓመተ ምሕረት ተወለደ?" መጽሐፉን አስቀመጪ የመለስኩላት ሳይመስላት አልቀረም::

"በ1811"

"የሞተውስ?"

"1832"

"የሚያፈቅራትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየት የት ነው?"

"እስር ቤት"

"በምን ሞተ?"

"በፍልሚያ" ሌላ ለመጠየቅ ሳትችል በፊት እኔ ግራ ያገባኝን ጠየኳት::



t.me/OLDBOOKSPDF

"ፍልሚያ ምንድነው?"

"የጥንቶቹ አውሮፓውያን ደንብ ነው:: ክብራቸው በተነካ ጊዜ ክብራቸውን ለማስመለስ ካዋረዳቸው ጋር ቀደም ሲል በጎራዴ በኋለኛው ዘመን ደግሞ በሽጉጥ ገጥመው ይገዳደላሉ::"

ይሄ ደንብ እኛ ዘንድ ቢኖር ከስንት ሰው ጋር እፋለም ነበር? ከጋሙዱ ከጋንጩር ከጋሙዱ እናት፣ ከይጋርዱ ቂጦ ባል፣ ከጋሽ ድንቁ፣ ከማናሉ_ ከጋንጩር፣ ከሴት ጋር መፋለም ይፈቀድ ይሆን?

ሙና መጽሐፉን ስሰጣት አሁንም አልተቀበለችኝም:: ዝም ብላ የጠላ ቂጣ እንጎቻ በመሰለ መነፅሯ አፈጠጠችብኝ:: ከንፈሯ "ባራቮ" አለኝ::

"ውሰደው መጽሐፉን፣ ሌላ ደግሞ አመጣልሃለሁ" አለች:: በሁለት አይጠቿ ፍርቅርቅ ስትጓዝ በፀጥታ አየኋትና

"ቲቸር!" ስል ተጣራሁ:: ሦስት ቀን ተዘግቼ የማንበቤ ግብ ውኃ ያነሳ አልመስል አለኝ::

ቆም አለች፣ ጆሮዋን ወደእኔ አጋደለች:: ከዚያ ዞረች::

"ቲቸር መጽሐፉን አላነበብኩትም:: እንግሊዘኛ ለሚያውቅ ከፍቼ አስነበብኩት:: እሱ ተረከልኝ:: በቃ" ስትሽማቀቅ፣ ሳትጠላኝ ለመመለከት ፈልጌ ነበር:: መፈታተኗ ማምለጫ ቀዳዳ እንደማይታጣለት ለማሳየት:: ግን ፊቷ አይታይም:: ከንፈሮቿ ብቻ:: ከንፈር ደግሞ በውኃ ጥም ይከስል እንደሆን እንጂ በንዴት አይጠቁርም::

መምህርቷ ቀስ እያለች ወደ እኔ ተመለሰችና እንዲህ አለችኝ::

"አንባቢነት የሚጀመረው ሌሎች ያነበቡትን ሲተርኩ በማድመጥም ነው:: እኔም ያነበብኳቸውን መጻሕፍት ልተርክልህ እሞክራለሁ::" ፊቷን አዙራ መንገዷን ቀጠለች:: እንደ ደደብ እንጨት መፍለጫ ምሳር ሳሳርፍባት እንጥራ መለሰችው::

"አልፈልግም" አልኳት ድምጼን ዘለግ አድርጌ:: "የእርስዎን መጽሐፍ ከእንግዲህ አልፈልገውም"


t.me/OLDBOOKSPDF

ዘወር ብላ አየችኝ:: መነፅሯ ከሩቅ ፊቷን መንጋጋ አፈሙዝ ያለው ጠበንጃ አስመስሎታል:: የሆነ ነገር ተከሳለች:: አንድም የከሸፈ ወይም የመታ አለበለዚያም የሳተ ጥይት::

"ለካፊ! ምንድን ነች ይቺ ሴትዮ....."

መጽሐፉ እጄ ላይ እንዳለ ልብ ያልከት መምህርቷ ከዓይኔ ከተሰወረች በኋላ ሆነ እንጂ እያየችኝ አወረውረው ነበር:: እናቴ በዓይኗ እያብጠለጠለች የሰጠችኝን ሽልጦ ሰለምን አላሽቀነጠርኩትም ነበር ያኔ ... ያኔ.... ያኔ....



t.me/OLDBOOKSPDF

# 9

# ብረር ብረር አለኝ

ናፍቆት ደጋግማ ስትመጣ ደጋግሜ የለም እስባልኩ:: ጋሎይስን ለሦስተኛ ጊዜ ማንበቤ ነው:: አንዳንዴ መንገዱ መንገዴ ይመስለኛል:: ሌላ ጊዜ በእልሁ ከእኔ ይልቅ አሰፋ ጢሪሪን ወይም ንዳዴን መስሎ ይታየኛል::

መኝታ ክፍሌ ተዘግቶ ማንበብ ስለሰለቸኝ ወጥቼ ካከስቴ ቤት ሥር የቱሪማንቱሪ ቅጠል እንጥፌ ተቀመጥኩ:: መጽሐፉ የተዘጋጀው ለመኝታ ቤት ውስጥ ይመስላል!! ሌላ ቦታ ለማንበብ አይመችም:: በደረት አልጋ ላይ ተንበልብሎ በግራ በኩል መጽሐፉን፣ በቀኝ በኩል መዝገበ ቃላቱን አድርጎ በብዙ ማስታወሻ ወረቀቶች ተከብቦ ሲነበብ የበለጠ ይገባል:: ግን ሰለቸኝ::

ልዑል መውደቂያ ዘወትር ጭር እንዳለች ነው:: አሁን ግን አንድ ናዝሬት ሚሽን የሚማር ልጅ ለከረምት ዕረፍት ወላጆቹጋ መጥቶ ይረብሻታል:: ግራር ላይ ወይም የቱሪማንቱሪ ጫፍ ላይ ወጥቶ የተለያዩ ዘፈኖችን በረጅሙ ይለቅቃል አሁንም አለ:: የት እንደሆነ ግን ላየው አልቻልኩም ዘፈኑ ብቻ እየመጣ ከጆሮዬ ጋር ይላጋል::

"ልቢ ቢቀርበትም ነው
ልቤ ቢቀርበት ምነው
ምኞት እኮ ህልም ነው::"

አባቴ በልጅነቱ ይኼን ልጅ ሳይሆን አይቀርም ስል አሰብኩ:: ዘፈኑን ማስታወስ ከማልፈልገው አባቴ መንጭቄ የምጥልበት ስፈልግ ጋሽ በረደድ ትዝ አሉኝ አከስቴ ላይ ያላቸው ምኞት ህልም እንደሆነ ከዚህ ዘፈን ሊማሩ ይገባቸዋል:: መኖሪያቸው ከአከስቴ ቤት መደዳ ጫፍ ላይ ነው:: ቤታቸው በእኛ


t.me/OLDBOOKSPDF

እንክሮአማ አቧራ አላንገበበበትም:: በአየር ላይ ተንሳፋ ካልመጣች በቀር እንዲህ ንፁህ ሊሆን እንደማይችል የታመነ ነው:: የአግሯ ጣቶች በሽብር ዓይነን እንዲያፈገፍግ ያስገድዳሉ::

ቡኒ ዓይነት ሱሪ ታጥቃ በዚያ ላይ ረኸርም ካናቴራ የመሰለ ቀሚስ ደርባለች:: ቀሚሱ አጭር ሆኖ ቡኒው ሱሪ ፀሐይ ያጠቆረው ቀይ ጭን መስሎ ይታያል:: ጆሮዬ "እናትንና" የሚል ድምጿን እየጠበቀ እንገት ሙሉ ቡላማ ካናቴራዋን አልፌ ፊቷ ላይ አንገበብኩ:: የሚያማምሩ ክብ ዓይኖቿ የሚያብረቀርቅ ብርማ እንባ አንቆርዝዘዋል::

"ምን ሆንሽ?" ማለት ተሳነኝ:: ዝም ብሎ መመልከትም ከበደኝ፤ እኛ መካከል ምን ጉድ ገባ?

• "ስመጣ የለም ይሉኛል" አለች::

"እ...." ብዬ ዝም አልኩ ሳትጋበዝ አጠገቤ ቁጭ አለች:: የቱሪማንቱሪ ቅጠሉን በመፈለግ ይሁን ወይም በሌላ እንጃ በጣም ተጠግታኛለች:: ልቤ እንደ እንግዳ ቆጥሯት መፈራገጥ ያዘ::

"ናፍቆት እኮ ናት" አልኩት ልቤን "አረሳሃት? እጄ ሲያቅፋት የነበረ?..... ገላዬ ሲላፋት የነበረ?...... እንዴት አረሳሃት?"

ዝም..... ዝም፤ ብዙ ዝምች

በጎንዮሽ ሰርቄ አየኋት:: የእንባዋ ግት አለ:: ግን ደግሞ በጉንጯ ላይ የወረደ እንባ ዱካውን ትቶ አልፏል:: ለምን? የእስከዛሬ ለቅሶዋ እንደ ወንድ ቁጭትና ጥቃት የሞላው እራስ መነቅነቅ ነበር:: ዛሬ ግን ምን?

"ምን ሆንሽ?" ማለት ተሳነኝ:: በገዛ ጥያቄዬ የታሰረ የነገር አወሬ ፊትቼ እንዲያሳድደኝ ማድረግ መሰለኝ::

"ንዳዴ አብዷል፤ ጦጤ አብዷል፤ አንተ......" አልጨረሰችውም::

"እንዴት?"

"ንዳዴ ከኮልባ ሠፈር ልጆች ጋር ገጥሞ በየቀኑ ይሰከራል፤ ጦጤ ወደ ድሬዳዋ እሄዳለሁ ይላል::"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እኔስ?" ብዬ መጠየቅ እምሮኝ አልቻልኩም:: ፊቷ የተንከራታች ወንድ ልጅ ገጽታው ተገፍሮ ከቤት የማትወጣ ኮረዳ ፀዳል ፈሰሶበታል::

"ጦጢ ምን? ማለቴ ድሬዳዋ ምን ያደርጋል?" አፌ ተወለካከፈ::

"ልጅቷን አፈልጋለሁ ይላል:: እንደማገኛት በህልሜ ታይቶኛል ይላል::"

የባቡር መንጠላጠያ እጀታ ይዛ በዓይኖቿ ፈገግ እንዳለች ያየችን በድሪያ የተከበበበ ፊት ያላት ልጅ በአየር ላይ እንደምትንሳፈፍ ሁሉ ሳትንቀሳቀስ ከዓይናችን የራቀችው ልጅ..... እኔ ሳስባት መቼም ከባቡር የማትወርድ ሆና ትታየኛለች:: ፈገግታዋ እንደ ሞናሊዛ ዘላለማዊነት ተላብሶ እንደ ፍቅር አምላክ በየሐዲዱ ዳር ያሉ ዕኩዮቿን በፍቅር እየመረዘች የምትኖር::

"አንተን ይፈልግሃል" አለች::

"ማን?"

"ጦጤ"

"ለምን?"

"ፍራንክ እንድትሰጠው:: መሳፈሪያ ወደ ድሬዳዋ፤ አብዷል.. አብዷል::"

"ታ..ዲ...ያ..."

"እንዳትሰጠው:: መቼም አይመለሰም፤ ቢያገኛትም ባያገኛትም ጠፍቶ ይቀራል"

ይሄን ሁሉ ሐዘን ይዛ ነው እንዲህ አምሮባት የመጣችው? ተደብቆ ሲያደምጠን እንደቆየ ሁሉ ፀጥ ብሎ የነበረው የቱሪማንቱሪ ላይ ዘፋኝ እንዲ አምባረቀ::

"የእኔ እያልኩ አድርጌሽ የግሌ፣
ነው ልብሽ ከሌላ አዝናለሁ በዕድሌ"

ናፍቆትን አየኋት የልጁን ድንገተኛ ዘፈን ያደመጠችውም አይመስልም:: እንግዷን ደፍታለች ፀጉሯ ሲበዛ ሉጫ ነው:: ወንድ እጅ እንደገባ ሁሉ በወጉ ባይያዝም ናፍቆትን የተሻለች ለማድረግ መፍጨርጨሩ አልቀረም.. ፀጉሯ"


t.me/OLDBOOKSPDF

"ጦጢ አሁን የት ነው?"

"ሐዲድ መገንጠያ ነው::" በፊት ቢሆን "እናቱንና" የሚል ታስከትል ነበር:: እኔንም እናትንና እንዳትሰጠው" ትለኝ ነበር:: ዛሬ ምን ነካቷታል እኔስ ዛሬ ምን ነኩቶኛል?

መጽሐፎቼን ወደ ቤት አስገብቼ ስወጣ የሎሚ ተግለብላቢ ምላስ ተከተለኝ:: "አትዬ ሾርባ ስሪለት ብለው ደርሷልኮ፣ ካልሆነ እኔ አጠጣዋለሁ እንጂ አይበላሽም መቼም....."

ናፍቆት ቆማ ትጠብቀኝ ነበር:: ከከርሷ በላይ ያዝ አድርጌ በእንዛይ መራኋት:: ከናፍቆት ጋር መነካካቱ ተደርጎ የማይታወቅ ነገር እንዳደረኩ ሁሉ ሆኜ የማላውቀውን ሆንኩ:: ልቤ....

"ልቤ ተው... ናፍቆት እኮ ናት፣ አረሳሃት?" የናፍቆትም ሁኔታ አንዳች ነገር ይጋብዛል ምን? እንጃ! አፋራምነት ከየት አመጣች? አቀርቅሮ መቆመጥ፣ አቀርቅሮ መጓዝ፣ አቀርቅሮ ማየት፣ አቀርቅሮ ማውራት... ከየት መጣባት? አልቅሳ ባባበልኳት፣ እቅፌ እንገቴ ውስጥ በከተትኳት፣ በአፍንጫዋ አየር ስትስብ የአንገቴ ቆዳ ድርርር ባለ:: እንደ ጋሎይስ ስለዚች ልጅ ከብር ከባላንጣዋ ጋር እፋለማለሁ:: ተፋልሚ መግደል አይደለም ከብሬ መሞት::

የቱሪማንቱሪው ላይ ድምጻዊ እንደ ባንድ የተለያዩ ድምጾች እየደራረበ አንድ በቅጡ ያላወቅኩትን ዘፈን ዜማ ይጫወታል::

"ዱሩሩ፣ ቱቱቱ፣ ዳራራራራ...."

ተና ብዬ አየሁት" ደምስሩ ተግተርትሮ በፍጹም መከስተር ውስጥ ነው:: "ድን..ድን..ድን፣ ኢ..ሆ..ሆሆ..." እንደ ጦጣ በእግሩም ቅርንጫፍ ቆንጥጧል::

"ጦጢ፣ ጦጢ፣ ጦጢ....."

ጦጢ እኔ መጀመሪያ የተቀመጥኩባት ቱሪማንቱሪ ዛፍ ሥር ቁጭ ብሏል:: ሁለመናው የያኔውን እኔን መስሏል፣ የሞጆ አየር አሳድጎ ከዳው? እንደ እኔ መቶ ኪሎ ሆኖ ተጫነበት? ወይስ ምንድነው?.....


t.me/OLDBOOKSPDF

....ለመሆኑ ከሞጆ አየር ጋር እንዲህ የታረቅኩት መቼ ነው? የት ነው? እንዴት ነው..... መቶ ኪሎ መርጉን መቼ እንዲነሳልኝ ወሰነ? የት አስቀምጦ አሁን ጠጤ ላይ ሚነው?

"ያው" አለች ናፍቆት "ያው መጥቆልሃል:: የለኝም ብሎሃል" በትንሽ በትንሹ የበፊቷ ናፍቆት ብቅ አለች::

"አማረብኝ መሰለህ ነው? ይቅር፣ ተይው፣ ተወው፣..." እንደተዳከመ ያስታውቃል:: ጉልበቱን እንደ ምርኩዝ ተደግፎ ተነሣ

"ምን ልታደርግ?" አለችው ናፍቆት

"በእግሬ እሄዳለሁ"

"ድሬዳዋ ድረስ?"

"እዎ"

"እናትንና፣ መቼ ልትደርስ ነው? መንገድ ላይ መሞት አምሮሃል?"

"ትኬት ሳልቆርጥ ባቡር ላይ ተሳፍሬ ፊናንስ ፖሊስ ከባቡር ላይ ከሚወረውረኝ ይሻላል::" በተዳከመ ሁኔታ አሁኑኑ ወደ ድሬዳዋ መንገድ ጀመረ::

እኔና ናፍቆት ተያየን:: ብቻችንን ሰንሆን እንደነበረችው አይደለችም:: ወንዳ ወንድ ብስጭቷ ውስጥ ነች::

በተሰፋ መቁረጥ ወደ ጠጠ ተመለከትኩ የስንብት አይነት ያየኛል::

"ቆይ እስኪ...." አልኩት:: "የት ብለህ ትሄዳለህ? ድሬዳዋ እኮ ከሞጆም ትሰፋለች:: አዲስ አበባን ልታክል ምንም አይቀራት" አውቃት ይመስል

"እኔ እንጃ! እኔ እንጃ..... ብቻ ከዚህ እንድሄድ የሚገፋፋኝ ነገር አለ:: ይጎተጉተኛል:: የሚጎተጉተኝ ደግሞ ሁሉም ነገር እንዲያስጠላኝ በማድረግ ነው:: ሞጆ፣ እናቴ፣ እናንተ፣ ትምህርቴ፣ ሃይማኖቴ..... ሁሉም አስጠላኝ:: ያስጠላል በጣም.....በ...ጣ..ም!"

የጠጤ ብልግብልጥ ጠጣነት ተገፍፎ መነኩሴነት ተጭኖበታል:: ዓይኖቹ ቀዝዘዋል:: ጠጣነትና መነኩሴነት ይቀራረቡ ኖሯል? ሲስቅ ይንቀጠቀጡ የነበሩ ትላልቅ ጆሮዎቹ የጠወለጉ ቅጠል መስለዋል::



t.me/OLDBOOKSPDF

"ዛሬ በህልሜ አየኋት በተሰፋ መቁረጥ ጭንቅላቷን ግራ ቀኝ እያማታች ማልቀስ ጀመረች።"

"እናትንና.... እናትንና.... እናትንና...."

'በቃ ስጠው' ማለቷ እንደሆን ገባኝ እንዴት? እንጃ! ጦጢም የናፍቆት ፍቃድ ገብቶታል። ፊቱን ወደ ባቡር ጣቢያው መለሰ ዛሬን ሞጆ ማደር እንዳልፈለገ ገባኝ።

*　　　*　　　*

ልጅነት እንደ ያደረገውን ፍቅር ይበትነዋል? ጦጤ እርጅቶ ባቡር ላይ ወጣ። ባቡሩ ወገቡ እንደንበጠ አዛውንት እቃስቶ ተነስቶ፣ ቀስ በቀስ እየወበራ ሄደ። ጦጢ የፍርጎ ብረቱን ይያዝ እንጂ ፊቱ ወደ እኛ አልነበረም። ወደ ድሬዳዋ መልሶታል።

ከጦጤ በላይ ናፍቆት አርጅታለች። ባቡሩ ወደ ጠፋበት አቅጣጫ እፏም በሐሳብ ጠፍታለች። ድካም በተጫጫነው እኳኋን ዓይታኝ ለመሄድ ተነሣች። ቀኝ እጇን ከንዴ ውስጥ ወሽቃ የመንጠልጠል ያህል ወደታች ጎተተችኝ። የቁጭቷን መጠን እንድረዳ ይሆን? ጉዞ ጀመርን። ሆን ብላ በጫማዋ ጫፍ ቡላማውን አፈር እየጫረች ትጓዛለች።

"አንተስ መቼ ነው የምትለየኝ?"

"ወዴት?"

ትከሻዋን በአላውቅም ሰበቀች።

ለመልስ የቸገረ ሆኖብኝ። እግር እግሮቿን ማየት ቀጠልኩ። እነሱን ማየት ልብን ደስ ያሰኛል።

"አዲስ አበባ የምትወድዳት የለችም?" ምን ነክቷታል ዛሬ? አለች ብል ስለጥፋቱ ለመቅጣት የተዘጋጀች እናት መስለችኝ የጦጤን እልህ ሁሉ እኔ ላይ የምታወራርድ።

"አለች" አልኩ ንግግሬን ለቀልድ አዘጋጅቼ።



t.me/OLDBOOKSPDF

"እናትንና አትቀልድ" እንዲህ ስትለኝ እንዴት ደስ ይለኛል?

"አልቀለድኩም"

"እሺ ካልቀለድክ ማን ትባላለች?"

"እንቺ እንኳን አትባልም፡፡ ግን ስሟ ይጋርዱ ነው፡፡ ይጋርዱ ቂጦ ይባላሉ፡፡"

በዓይኖቿ እናትን አለችኝ

"እውነት!"

"እኔ ውሸት አልፈልግም"

"ውሸት አይደለም መጀመሪያ አድምጪኝና...."

"እሺ ንገረኝ፣ ብቻ ውሸት ይሁንና......."

"ይኸውልሽ" ብዬ ጀመርኩ፡፡ "ይጋርዱ ቂጦ የተባሉት ለምን እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ቂጣቸው ብታይው በጣም ት..ል..ቅ.. ነው፡፡"

"ባለጌ! እሺ..."

"የሰፈራችን ወንዶች ሁሉ እሳቸው ሲያልፉ ወ..ከ..ከ፣ ድር..ከ..ከ፣ ሙ..ከ..ከ፣ ሏ..ከ..ከ... ይላሉ፡፡"

"እናትንና አታጋን" ከመጥፎ ስሜቷ ወደ መላቀቁ እንደሆነች ስላወቅሁ ጨምሬ ጨማምሬ ማውራት ቀጠልኩ፡፡ እኔ ይጋርዱ ቂጦን በጣም እንደምወዳቸውና አንድ ቀን ስከተላቸው ባላቸው እንደያዙኝ...."

ከንዴን ለቅቃ ከት ብላ ሳቀች፡፡ ሳቋ የሚያባራ አይነት አይደለም፡፡ በየመኻሉ "ወይኔ ጉድህ" እያለች ትስቃለች፡፡ እኔ ሆን ብዬ አኮረፍኩ፡፡

"እሺ... እሺ ይቅርታ፣ ሳቄ እምቢ ብሎኝ ነው፡፡ ግን እውነትህን ነው? እናትንና ትልቅ ሴትዮ...." ሳቋ ይቀጥላል፡፡ "እሺ ምን ተባልክ?"

"ትንሽ አይከብድሽም" በኩርፊያዬ ቀጠልኩ

"እሺ በቃ፣ በእናትህ ንገረኝ"

በኋላ ሰፈሩ ጉድ አለ፡፡ ወሬው እየተጨማመረ መከብብ የይጋርዱን ቂጥ መታ ተባለ፡፡"


t.me/OLDBOOKSPDF

"ወይኔ ጉድህ፣ እሺ "

"እኔ አልመታሁም፤ ለመውደዱ ግን ቂጣቸውን እወደዋለሁ አልኩ"

"እሳቸው ማለቴ ይጋርዱ ምን አሉ"

"እሳቸውማ፣ ፎቃቃ ሁሉ አሹ! ደግ አድርጎ ቂጤን መታው! እኔ ነኝ እንደውም ስትወደው ለምን ይቅርብህ ምታው ያልኩት፡፡ አሉ"

"እውነትህን ነው?"

"ታዲያ ውሸቴን ነው? ይኸውልሽ ባልየው ቀበሌ ፍርድ ሸንጎ ከሰሱኝ፡፡ ይጋርዱ ቂጦ ሲጠየቁ ወንድና ቢላዋ የሰባ ይወዳል፡፡ ደግሞስ የወንድና የቢላዎ ትንሽ የታለው? ካገኙ ሁለቱም ይቆርጣሉ፡፡ ይልቅ በከንቱ አትታከቱ፤ እኔ ነኝ ምታልኝ ቂጤን ያልኩት፡፡ አሉ፡፡"

"እሺ?"

"ባልየው አፍር ብለው ወደ ቤታቸው"

"እሺ"

"ይኸውልሽ አንድ ቀን ተደብቄ ቂጥ ቂጣቸውን ሳይ......"

"ባለጌ"

"አይተውኝ ኖሮ...."

"ማን?"

"ይጋርዱ ቂጦ"

"እሺ?"

"ከዚያ የተደበቅሁበት ድረስ መጡና እንዲህ አይንህ ከሚንከራተት አግባኝ አሉኝ"

"እ? እውነትህን ነው? እሺ?"

"ባልዎትስ? ባሻስ? አልኳቸው፡፡ እሳቸው ላንቲካ ናቸው፡፡ ሰልችተውኛል፡፡ ልፈታቸው አሰቤአለሁ፡፡ ይልቅዬ ሽማግሌ ላክብኝ አሉኝ፡፡"

"እናትንና፣ ይቺ ውሸት ናት"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ያልኳቸውን ሳልነግርሽ"

"እሺ ምን አልካቸው?"

"እርስዎም ትዳርን አያፍርሱ!! ለእኔ ካዘኑልኝ በእየዓመቱ እየመጣሁ እንዴ ቂጦትን ልምታው:: ወዲያውም ትምህርቴ አይስተጓጎልም አልኳቸው በዚሁ ተሰማማን:: አሁን ዓመቱ ደርሷል እሄዳለሁ"

"እናትንና አትሄድም፣ ባለጌ....."

ናፍቆት ፀሽየች ደስ አለኝ::

"እንዴ? አያፍርም እንዴ?" ትላለች እየቆየች:: "ግን እውነትህን ነው?"

"ወደዚህ ስመጣኮ የዓመቱን እንዴ ቸብ አድርጌአቸው ነው:: እ..ቤ..ት እንዴት ደስ ይላል ብቻ ሳልጠግባቸው እንዳይሞቱብኝ::"

"አንተ ብትሞት ይሻልሃል ቀልድ፣ እውነት፣ መጠራጠር.... የተቀላቀሉበት ሚናውን ያልለየ ፊት አሳየችኝ:: በብዙ መደፋፈር ሳብ አድርጌ አቀፍኳት::

"ነገ ትመጪ የለ?" አልኳት:: እፈለጋለሁ እንዴ? ነገ እንድትመጣ በእርግጥ እፈልጋለሁ? እንጃ!

"የት?"

"እቤት እኔጋ..."

"እሺ"

የበለጠ ለሰለሰች ፊቷን አንገቴ ውስጥ ከትቼ አባበልኳት:: የእረጅም ዘመን ናፍቆት ያለብኝ ያህል ያለመርካት ተሰማኝ:: በዚሁ ተሰነባበትን::

የናፍቆትን ሐዘን እኔ አለዝቢዋለሁ ብዬ እገምታለሁ:: በየመኻሉ ጦጢ ቢታሰባት እንኳን ጨዋታዬ እየተሰነቀረ አንባዋን ሳቅ እንደሚያደናቅፈው አልተጠራጠርኩም:: ለእኔስ ማን ሐዘኔን ያለዝብልኝ? ያዘንኩት ለጦጢ አይደለም:: ለራሴ ነው:: ጦጢ የሆነ ነገሬን እናግቶትና ፈታትሾኝ ነው የሄደው:: ጦጢ የደፈረውን አደፍራለሁን? ልቤን ፈተሸኩ፣ ነፍሴን ፈተሸኩ፣ መንፈሴን ፈተሸኩ.... የጦጢ ድፍረት፣ ወኔና አፈጣጠር እኔ ውስጥ የለም::



t.me/OLDBOOKSPDF

የእኔ ባቡር ወደ ፍቅር ሳይሆን ከፍቅር ለመሸሽ አፍንጫውን በተቃራኒው የቀሰረ ነው፡፡ በዚህ ተሞክሮዬ እንቅስቃሴ አልባ ፍቅር እንደሌለ ተረድቼአለሁ፡፡ አንድም ወደ ፍቅር መገስገስ ወይም ከፍቅር የመሸሽ እንቅስቃሴ በሕይወት ውስጥ ያሉ ሁለት አማራጮች ናቸው፡፡

ጦጢን ከሸኘሁበት ሰአት ጀምሮ እራሴን መርምሬአለሁ፡፡ የፍቅር ሽሽግ ነው ሕይወቴ ብዬ የተቀመጥኩት፡፡ ከእናቴ በአክስቴ ሸሸሁ.... ከንፁህ በናፍቆት ሸሸሁ..... ከእነጋንጩር በእነ ጦጢ ሸሸሁ፡፡ አንዱን በሌላኛው ለማካካስ እንጂ የእኔ የሆነውን ላለማግኘት ምንም የማድረግ ወኔ የለኝም፡፡ ከአክስቴ፣ ከናፍቆት፣ ከሞጂ_ የምሸሽበት ባቡር እስኪቀርብ ድረስ ብቻ በአዘናጊነት እድፍጬ እኖራለሁ፡፡ እንደ ናፍቆት ሰው ላጣ ነው በሚል ፍርሃት ውስጥ መሆኔን አላረጋግጥም፡፡ እንደ ጦጢ ሕልሜንና ስሜቴን መሪ ኮከብ አድርጌ የሰብአ ሰገሎችን ጉዞ አልጀምርም፡፡ ፈራሁ፣ በጣም ፈራሁ የፍቅር መነሻዬም፣ መድረሻዬም የማደርገው እራሴን ብቻ ነው?

ይሄንን ያሰብኩት ያኔ በወቅቱ ይሁን አሁን ካለፈ እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ደግሞም ለጽሁፉ ምንም ለውጥ አያመጣም፡፡ በዚያን ጊዜ እንዲያ ነበርኩ፡፡ የማይካደው እውነት ይሄ ብቻ ነው፡፡ ናፍቆትን እወዳታለሁ፣ ነገር ግን እንኳን ፈልጌአት ልሄድ ፈልጋኝ ስትመጣ አልቀበላትም፡፡ የልቤን ምት እወደዋለሁም እጠላዋለሁም፡፡ የምወደው በሚሰጠኝ እንግዳ ስሜት ነው፡፡ የምጠላው ደግሞ የልቤ ምት ተያይዞ የመጠፋፋት ደወል ስለሚመስለኝ ነው፡፡ ብቻ ያኔ እንደዚህ ምክንያት አበጅቼና አበጥሬ ለይቼ አውቄው ላይሆን ይችላል፡፡ አሁን ላይ ሆኜ ሳስበው ግን እንደዚያ ያውጠነጠንኩ መሆኔ ላይ እርግጠኛነት ይሰማኛል፡፡

በቀጣዩ ቀን ማለዳ ናፍቆት መጥታ አስጠራችኝ፡፡ የለም አሰባልኩ፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

# 10

## ሀሰሳ ነፍስ

መምህርት ሙና የአከስቴን አህል በረንዳ ለይታ ስላወቀች ይመስለኛል መጻሕፍት ትልከልኝ ጀመር፡፡ ብዙ ጠንካራ የሒሳብ ሊቆችን ታሪክ አነበብኩ፡፡ ከተላኩልኝ መጽሐፍት ውስጥ ዘጠኝ ያህሉ ስለ ሒሳብ ሊቆች ሕይወትና ሥራ የሚተርኩ ናቸው፡፡ ፓይታጎራስ የተባለው ግሪካዊ የጥንት የሒሳብ ሊቅ ለቁጥር የተለየ ቦታ ከመስጠቱ የተነሣ ያመልከባቸው እንደነበር ሳነብ ግርም አለኝ፡፡ ከፍል ውስጥ ሒሳብን የተቸሁበት መንገድ ተራ መዳፈር ሲመስለኝ ለካ የሰው ሃይማኖት ማጣጣል ኖሯል? ስል እሳቢ ሳቅ ውስጥ ተደፈቅሁ፡፡

ከፓይታጎረስ ጋር ሊሎች ሁለት ጥንታዊ የሒሳብ ሊቆች ታሪካቸው ተዳብሎ በአንድ መጽሐፍ ነበር፡፡ ዩክሊድ እና አርኪሜደስ፡፡ የሒሳብ ግኝታቸው ሳይሆን የወጡበት የወረዱበት ሕይወት የበለጠ እየሳበኝ አነበብኳቸው፡፡

የአንዳንዶቹ የሒሳብ ሊቅነት ከፍልስፍና ጋር የተጎራበተ በመሆኑ እግረ መንገዴን ወደ ፍልስፍና ጎራ የማለቱ እድል ገጠመኝ፡፡ ሬኔ ዴስካርተስ (በኋላ ሙና ዴስካርተስ ሳይሆን ዴካርት ነው አለችኝ) ብሌዝ ፓስካልና አይዛክ ኒውተን ሒሳብን ከፍልስፍና አቆራኝተው የሚመራመሩ ሆነው አገኘኋቸው፡፡ መጻሕፍቱ እንግሊዝኛ ቋንቋ ሁለተኛቸው ለሆነ ሰዎች የተዘጋጁ ስለነበሩ ይመስለኛል በተለይ ፍልስፍናውን ጠልቀው አይገቡበትም፡፡ ይሁንና ለእኔ በጣም ከባድ ነበር፡፡ በተለይ ተፈጥሮና ፈጣሪ ላይ የሚያነሱት የድፍረት ሐሳብ ከእራሴ ጋር እጅግ ያወዘገበኝ ጉዳይ ሆኗል፡፡

ሳይንስ ከፈጣሪ ሕልውና ጋር ሲያገናኝ ያነበብኩት የመጀሪያው ሰው ኢዛክ ኒውተን ነበር፡፡ የእሱ አሳብ አደረጃጀት የእኔን እምነት መለስ ብዬ እንድመረምር

t.me/OLDBOOKSPDF

የእነ ንዳዴ በራፍ በሳ እህያ በመሳሰሉ ልጆች ተከቧል:: ናፍቆት ልጆቹን ስታይ የረሳችውን ጭንቅላት ግራ ቀኝ ማማታት ጀመረች::

"ናፊ፣ ናፊ፣ ናፊ..." አሏት

"አሰከራችሁት አይደል፣ እናታችሁንና" አለች

አውራ የመሰለው ቡላ አህያ "እራሱ ነው የሚጠጣው:: ይኸው እኛ ጠጥተናል አሁን፣ እንቢ ስንለው ብቻውን ነው የሚጠጣው"

"ኮርማ፣ ሁሉንም አውቃለሁ" አለች ናፍቆት ጉርምስናዋ እንደቀጠለ ነው::

"እኛ እንቅማለን እንጂ አንጠጣም፣ ምንድነው የምታውቂው?" አለ ኮርማ የተባለው ሌሎቹ ቁልጭ ቁልጭ ይላሉ:: ይሄን ያህል መፈራቷ ገረመኝ::

"የሆነች ገርል አጣብሳችሁት ነው ያበደው? እሷን እኔ አገኛታለሁ:: እወጋታለሁ እናቷንና"

"ናፊ ሙች እሷ 'አኪ' ናት:: እሱ ግን ካላመሸሸ፣ ካላደርሸ እያለ ነው የሚጠጣው::" የቡላዎቹ አውራ አሁን ገና ያየኝ ይመስላል:: ነቃ ብሎ

"ቁሪስት እሱ ነው?" አላት

"አዎ" አለችው::

"ኮርማ እባላለሁ" ብሎ በቡላ እጁ ጨበጠኝ:: እጁ እንደ በሬ ሸሆና አጭርና ጠንካራ ነው:: በእሱ ቡጢ የተመታ ክብት አረገጠው መባል አለበት "ጎደለኛ ተደባዳቢ ነህ አሉ፣ አሪፍ ነው:: ሰሞኑን የእመዴ ሠፈር ልጆች ትዕቢት ትዕቢት ብሏቸዋል:: ብቻ ለብቻ ከገጠምን የእኛን ሠፈር እናስወክልሃለን::"

በቅጽል ስሙ መኩራራቱ አስገረመኝ:: ኮርማ ከሆነ የበረት ገልባጭ ልጅ መሆን ይኖርበታል:: ከጅሩ፣ ከሸንኮራ፣ ከምንጃር ወይም ከቡልጋ በረት ገልብጦ ያመጣው::

በዚህ መካከል ንዳዴ ጮኸ:: ወደ በሩ ጠጋ ብዬ አንገቴን አስገግኩ:: ንዳዴ ሲታመም ተኝቶ የነበረበት አልጋ ላይ በደረቱ ተንጥፏል:: እንጀራ እናቱ አጠገቡ ቆማ አከርራ በጨበጠችው እጇ ትደልቀዋለች::

"ተውዋት ትደልቀኝ" ይላል ንዳዴ፤ ትበጭቀዋለች::



t.me/OLDBOOKSPDF

"እለቅሽ መስሎሻል እናትሽንና"

"ስምሽ ማነው?" አልኳት

"ምዕራፍ" አለችኝ ወደ ኋላ እያየች:: ለጊዜው ፊቷ በማጅራቷ በኩል ቢሆን፣ ወይም ፊቷን አዙራ ወደኋላ ብትሄድ የወደደች ይመስላል:: "ገና ድሮ ስለ እሷ ሲወራ እፈራት ነበር:: የፈራሁት ደረሰ:: ትገድለኛለች" በፍርሃት ተንዘፈዘፈች:: አሁንም ወገቤን አልለቀቀችም::

"አይዞሽ፣ አትነካሽም"

"እግዚአብሔር ይስጥህ:: አንተ ባትኖር ኖሮ......" አሁንም ትገላመጣለች:: እኔም ተገላመጥኩ:: ናፍቆት በእልህ መሬት ትሮግራለች:: ከኮርማ አይታ የተማረችው የበሬ ጠባይ ሳይሆን አይቀርም::

"በቃ ሂጂ" አልኳት ቆሜ

"እዚሁ ቁምልኝ እሺ?" ብላኝ ከአንኮርማ ጋር ለመቀላቀል ሮጥ ሮጥ አለች:: ዘለግ ያለ ሸንጥ አላት:: ሙትት ያለ ሰውነት:: ዘወር አለች:: ሰልካካ አፍንጫ ከናፍቆት ጋር የሚያመሳስላቸው ዓይን አላት:: ኸረ ፀጉራቸውም አንድ ነው:: ብቻ የምዕራፍ በወጉ የተያዘ ረኸርም ነው::


t.me/OLDBOOKSPDF

# 11

## ዳርዳርታዎች

"እቴ ገላ፣ እቴ ገላየኛ
ምን አለሽ ያ - ደገኛ
        ገላ - ኮርተሽ ተቀመጪ
        ገላ- አንቺ ምን ቸገረሽ፣
        ገላ- በውበት ማራኪ
        ገላ - እርን ከፈጠረሽ::"

በዕድሜ ወደ ኋላ ተጉዤ፣ ከመወለዴ በፊት የነበረው አባቴን በልጅነቱ ያገኘሁት መሰለኝ:: ይኼ የቱሪማንቱሪ ላይ ዘፋኝ እያናደደኝ ነው "ምናባቱ" ብዬ ተነሳሁ:: የሌሊት ልብሴን ሳልቀይር ነጠላ ጫማ እንዳጠለቅኩ:: የመኝታ ክፍሌን በር ስከፍት ሎሚ በሬ ሥር የተለጠፈች ይመስል ግጥም ቅንድቧን ፊቴ ላይ ደቀነች::

"እትዬ ፍርፍር በቅቤ ቁርሴ ስሪለት...."

"ብይው" አልኳት በእጭሩ ለመገላገል

"ብይው?" ያልጠበቀችው ይመስል ፊቷ ፈካ:: አናደደችኝ::

"ወይም አለነን አብይው" ይቺን ሴትዮ የሚጠቅማት የምግብ ፈቃድ ሳይሆን ዘመዶቿ እንዳቀዱላት ለቆሪጥ መስዋዕት መሆኗ ነው:: እስከ ወዲያው ሆዷን ትገላገለው ነበር:: ደንግጣ እያየችኝ ገፋ አድርጊያት ወጣሁ::

"ወይኔ ጉዴ!" ስትል ሰማኋት:: አያውቅም ብላ ታስብ ነበር ማለት ነው?

በቱሪማንቱሪ ዘፋኝ ላይ ያደረብኝ ንዴት በሎሚ ላይ በርዶ ነበር:: ቀጥታ ወደ ቱሪማንቱሪው:: ጥላ ሥር ሽበጡ ተነባብሮ ተቀምጧል:: ቀና ብዬ አየሁት::


t.me/OLDBOOKSPDF

እንደ ጆፌ አሞራ በእግሩ ጣቶች ቀጭን ቅርንጫፍ ጨምድዶ ይዞ መንቁሩን ከፍቷል፡፡

"እቱ ገላ - እቱ ገላ የኛ......" ይላል፡፡

"አንተ?" አልኩት፡፡

"አቤት፣ ጋሼ" አለኝ፡፡

ጋሼ ሲለኝ የናፍቆትን አባት የሆንኩ መሰለኝ፡፡ "አብዮታዊት ኢትዮጵያ፣ እዚህ መንቆራም ዘፋኝ ላይ ደረሰሽ?" ማለት አሰኘኝ፡፡

"ይኼ ዘፈን የማን እንደሆን ታውቃለህ?"

"የመሐሙድ አህመድ ነው፣ ጋሼ"

"አይደለም"

"ታዲያ፣ ጋሼ?"

"የእኔ አባት ነው፡፡" ለምን እንደነገርኩት ግራ ተጋባሁ፡፡ አንዳንዶቹ ቅርንጫፎች እየተቀነጣጠሉ በፍጥነት ወረደ፡፡

"አይ ጋሼ፣ በልደታ፣ በልደታ፣ ካባቶ ያገናኙኝ" አለ፡፡ ወርዶ ሲመለከተኝ ጋሼውን ይተዋል ብዬ ነበር ቀጠለ፡፡ "ጋሼ፣ አከስትዎ ድሮ ሲያወሩ ሰምቼ ነበር፡፡ የእህቴ ባል መዚቀኛ ነው ብለውኛል፡፡ ጋሼ አባቶን ያገናኙኝ" ሁለት እጁን ለልመና ዘርግቶ መዳፉ ላይ ያስቀመጠውን ይመዝን ይመስል አንዘፈዘፈ፡፡

አተኮርኩበት እንደ ጆፌ አሞራ አይኖቹ ነጭ የሌለባቸው ሙሉ ጥቁር ናቸው፡፡ ጭንቅላቱ ላባውን የተላጨ ዶሮ እራስ ነው፡፡ .

"አባቴ የለም፡፡"

"የት ሄዱ ጋሼ?"

"የለም፣ የለም" ቱግ አልኩ፡፡ ተገርሞ ሲመለከተኝ ወደ ቤት ሄጄ ጥላ ሥር ቁጭ አልኩ፡፡ ይሄ መንቁራም አካባቢውን እንድጠላ እያደረገኝ ነው፡፡ እዚያው ቱሪማንቱሪው ላይ ተሰቅሎ ማንቋረር ጀመረ፡፡ ዓለም ጠበበችብኝ፡፡ የት ብሄድ


t.me/OLDBOOKSPDF

መፍትሔውም እዚሁ አካባቢ ነው፡፡ ናፍቆትን እዚህ ቤት እያመጣሁ እክሰቱ እንድታያት ማድረግ፡፡ በናፍቆት መጠርጠር ይሻላል፡፡

ልቤ እረፍ አለች፡፡ እንደውም መሳቅ ከጀለኝ፡፡ ጋሽ በረድድ ግን ጥሩ ነገር መካች ናቸው፡፡ እሳቸውን እብከነከናለሁ ብዬ ሳስብ መከተው ተብከንካኝ አደረጉኝ፡፡

"እናታቸውንና....." አልኳቸው፡፡

ጫማዬን አድርጌ ስለ ሊዮናርድ ኢዩለር የሚተርከውን ትንሽ መፅሐፍ ይዤ ከቤት ወጣሁ፡፡ ከድሮ ዳቦ ላይ ለአንድ ሰው ጉርሻ የተቆረሰች የምትመስል መዝገበ-ቃላትም ያዝኩ፡፡ ኢዩለር የሒሳብ ሊቅ ነው፡፡ እነዚህ የሒሳብ ሊቆች ተከታትለውብኝ እንደሆን እንጃ እየታከቱኝ መጥተዋል፡፡ ኢዩለር የመጨረሻዬ ይሆናል ስል አሰብኩ፡፡ ወዲያው ደግሞ የመፅሐፍ ምርጫዬ ያለው በሙና እጅ መሆኑን እስታውሼ ሳቅ ከጀለኝ፡፡

በቱሪማንቱሪው ሥር ሳልፍ "ጋሼ" አለኝ ጆፌው ዘማሪ "ጋሼ አባትህን አገናኘኝ፣ በልደታ፤ በመሐሙድ አህሙድ ሞት!"

"መንቆራም!" አልኩ በሆዴ ግን ዘፈኑ የመሐሙድ አህመድ ነው እንዴ? አባቴስ?....ይኼን ማሰብ አልፈልግም፡፡

ወዴት ልሂድ? የት ሄጄ ላንብብ? እንደ ግንፍሌ ወንዝ ቢኖር በውሃ ቻቻታ ታጅቤ አነብ ነበር፡፡ ይሄን ይሄን ሳስብ ሞጆ ተፈጥሮ ያረጠችበት ቦታ ሆኖ ተሰማኝ፡፡ ቀጥታ ወደ ናፍቆት ቤት አመራሁ፡፡

አንዲት ጠንጋራ የቤት ሠራተኛ ወጥታ እያመናጨረች፣ ከእኔ ጀርባ ያለ ቱሪማንቱሪ እያየች "ምን ነበር?" አለችኝ፡፡

ቱሪማንቱሪውን መሰለኝ "ናፍቆትን....."

"የለችም፡፡"

ንፁህን ሳጣት የሚሰማኝ ስሜት መጣ፡፡ 'ናፍቆት! ናፍቆት! ናፍቆት!'

"የት ሄዳ ነው?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እንጃ!"

ስመለስ የማስበው ስለሰራተኛዋ አወዳደ አነጋገራ እኔ ላይ መተኮስ ነበር:: ለምን ጠንጋራ ገረድ ቀጠሩ? ጠንጋራ ዋጋው ይቀንሳል? ወይስ የናፍቆት አባት የታዩ ሳይመስላቸው ለመታየት ፈልገው?

"ወይ አብዮታዊት ኢትዮጵያ!........"

"ቱሪስት! ቱሪስት!" ከበስተኋላዬ ተጠራሁ:: ዞርኩ:: ናፍቆት ነበረች:: አስተያየቴ ሐፍረት ሳይለቅባት አልቀረም:: እቀርቅራ መጣች:: ብዙ ጠቃጠቆ ያለበት አጭር ቀሚስ ከሰሪ ጋር አድርጋለች:: የእግሮቿ ጣቶች!

"አውቃ እኮ ነው የለችም የምትለው እናቷንና" አለች:: እንዳቀረቀረች በጭንቅላቷ ጎረምሰኛ ተነሚነጨች::

"አንተ አልመሰልከኝም ነበር:: ገና ዛሬ እኛ ቤት ስትመጣ"

"በፊትም መጥቻለሁ አውቀዋለሁ" አልኳት

"ማለቴ እኔን ፈልገህ እራስህ ስትመጣ"

"ለዚህ ነው ብድር ልትመልሺ የለችም ያስባልሽው?" አልኳት

ቀና ብላ አፈጠጠችብኝ እውነት ፈራኋት:: አይኖቿን መለስ እስኪታደርግ ጠብቄ

"አልችልሽም" አልኳት

በሳቅ ፈነዳች:: እኔም አሷም በተመሳሳይ የትዝታ መጓጓዣ ወደ መጀመሪያዋ ቀን ግንኙነታችን ተመለስን:: ሳቋን ስትጨርስ አንገቴ ላይ ተጠመጠመች:: አንገቷና ጉንጯ መጋጠሚያ ላይ ሳምኳት::

"እንደዚህ አታድርግ" ስትል ጆሮዬ ላይ አንሾካሾከች:: እኔም 'እንደዚህ አታድርጊ' ማለት አሰኘኝ:: ማንሾካሾክ ከመሳም ይበልጣል::

የመተፋፈር አንድነት አሳይተን ጉዞ ቀጠልን:: ወዴት?

ጥቂት "ሞጆ ውስጥ ወንዝ የለም?" አልኳት::

"አለ" አለችኝ ያልጠበቅኩት መልስ ሆነብኝ::

"የት? ምን ጋ?"


t.me/OLDBOOKSPDF

"እንደውም ሁለት ወንዝ ነው ያለው፡፡ አንዱ ከቆዳ ፋብሪካው ጋዶ ፏፏቴ ወንዝ ይባላል፡፡ ሌላኛው ደግሞ ኒኮላ ወንዝ ይባላል፡፡"

"ኒኮላ ወንዝ ውሰጂኝ" አልኳት፡፡ ስሙ ደስ ይላል፡፡ ይሄኔ እንደ ግንፍሌ ወንዝ ማግበስበሱን የሚያጧጡፍበት ወቅት ሳይሆን አይቀርም፡፡ ልዩ ልዩ አበቦችም አዲስ አመት ለመቀበል አፋራም አንገታቸውን የሚያቀኑበት፡፡

እጇን ወገቤ ላይ አሳርፋ ወደ ኒኮላ ወንዝ መራችኝ፡፡ ጀርባዬ ውስጥ የወሸቅኩትን መፅሐፍ ዳስሳ "ምንድን ነው?" አለች

"መፅሐፍ ነው"

"ታነቢያለሽ እንዴ" አለችኝ፡፡ "ድብድብም መፅሐፍ ውስጥ ነው ያገኘሽው?"

"ምን ዋጋ አለው፣ እንቺን አላሸነፍኩ"

ቀና ብላ ደስ በሚል አኳኋን አየችኝ፡፡ እጇን ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጊ ተጓዝን፡፡

ኒኮላ ወንዝ ውሃውን ከየቤቱ በጣሳ የተበደረው ይመስላል፡፡ ዙሪያውን ረጃጅም የበርሃ ሳር አልፎ አልፎ በቅሏል እንጂ መላጣ ነው፡፡ ሳማ የለ፣ ሳማው ላይ አባ ጨጓሬ የለ፣ በዙሪያው የሚበሩ ቢራቢሮዎች የሉ፡፡

ዘወር ብዬ ናፍቆትን አየኋት አያየችኝ ነበር፡፡ ዐይኗን ዐይኔ አደናቀፈባት፡፡

ኒኮላ ወንዝ የከሸፈ ፏፏቴም አለው፡፡ ቁመቱ ከአንድ መኖሪያ ቤት ቁመት አይበልጥም፡፡ እዚያ ነጭ ሳር የመሰለች ውሃ እየተንጫነጨች ትፈጠፈጣለች፡፡ የውሃዋ መፈጥፈጥ ሥር አንዳች የዛገ ብረት ተጠምዶ አፋፍ ላይ ወዳለ የሳንቃ ቤት ያመራል፡፡ ቤቱ ከመፈራረሱ በላይ በብዙ የብረት ኩይሳዎች ደጃፉ ተገረከርኳል፡፡

"ያ ምንድን ነው?" አልኳት

"ኒኮላ የሚባል ጣሊያናዊ የተከለው የውሃ ወፍጮ ነው፡፡ አብዮቱ ሲመጣ ጥሎ ጠፋ ይላሉ፡፡"

ኒኮላ ወንዝ አካባቢ ያለው ዐይን የሚስብ ነገር ናፍቆት ብቻ ናት፡፡ ቁራማንቱሬ ዛፍ ሥር ቁጭ አልን፡፡ በእርግጥም እዚህ አካባቢ ህይወት መከናለች


t.me/OLDBOOKSPDF

ስል አሰብኩ፡፡ አካባቢው ላይ ዐይን የምትስብ ብቸኛ ቆንጆ አጠገቤ አስቀምጬ፣ እስሬ የምወሽቅበትን መብት ተቆናጥጬ፣ ከደፈርኩም ከንፈሯን ከፈራሁ ጉንጯን መጥምጬ..........

"ደስ አለኝ" አለች

"ለምን?"

"አንተ ስትፈልገኝ"

ዝም፣ የኒኮላ እንጨት ዛኒጋባ ላይ ጥቁር ቁራ አርፎ እንደ ቱሪማንቱሪው ላይ ዘፋኝ መንቆሩን አላቀቀ፡፡ ድምፁ ቆይቶ ደረሰ፡፡ "ቋ.......ቅ"

ፊቷን ዘወር አድርጋ ትከሻዬን በጀርባዋ ተደገፈች፡፡ ማጅራቷ በሁለት አቅጣጫ ወደ አንገቷ መሄድ እንደሚቻል ይጠቁማል፡፡ ሳማት፣ሳማት አለኝ፡፡ ማቀምቀም ከጀመረው ጢሜ ጋር ከንፈሬ ላይ ምን በቀለ? ምን መጣፈጥ ተጨመረ?

"ሁሌ ፈልገኝ፣ ለሌኔ ምን ማለት እንደሆነ አይገባህም!"

ማጅራቷ ላይ አተኮርኩ፡፡ ለጫ ፀጉሯ ጀርባዋ ላይ ለመድረስ መንገድ የጀመረ ይመስላል፡፡ ለጊዜው የአንገቷ አጋማሽ ላይ ደርሷል፡፡

"እሺ?" አለችኝ

እሺም እምቢም አፌን ከበዱት፡፡ አንዱ ሲከብድ ሌላው መቅለል አልነበረበትም? መፅሐፌን ከጀርባዬ አውጥቼ ማንቀላበጥ ጀመርኩ፡፡ "ቋ.....ቅ"

"እንቢ ነው?"

"ዋናው መገናኘታችን ነው፡፡ አንቺ ፈለግሽ እኔ ፈለግኩ ለውጥ አያመጣም፡፡" አልኩ፡፡ መፈለግ፣ መፈለግ፣ መፈለግ.....እንዴ መፈለግ ከጀመርኩ በንቱን አዳርሰዋለሁ? አባቴን?...ንፀሀን?...ማናሉን?....ንዳዴን? ጦጤን?....እሁሁሁሁ.....

ናፍቆት ቅዝዝ ብላ የእንቅልፍ ልብ የመሰለ ንግግር አደረገች፡፡

"አለመፈለግን ብቻ ሳይሆን ፈልጌ ማጣትን ገና ከልጅነቴ ጀምሬ አውቀዋለሁ፡፡ እናቴ ጥላኝ ስትሄድ ገና የአምስት አመት ልጅ ነበርኩ፡፡ ግማሽ

t.me/OLDBOOKSPDF

መንገድ እያለቀሰኩ ተከተልኳት:: አልተመለሰችም:: ርምጃዋን አፋጠነች:: ነጠላዋን ተከናነበች፣ ሄደች:: ካደኩ በኋላ አፈላልጌና አጠያይቄ መቂ አገኘኋት:: አልፈለገችኝም:: 'ደህና የተረጋጋ ኑሮዬን አትበጥብጪ፣ እዚያው እርፈሽ ተቀመጪ' አለችኝ:: ሌላ ባል፣ ሌላ ልጅ፣ ሌላ ህይወት እናት ይቀማል? እናት ያልፈለገችው ልጅ....."

"ቋ.......ቅ!"

ናፍቆት አልመሰለችኝም:: አስፈሪ እርጋታ፣ ለለቅሶ ያዘመመ ስሜት፣ የመረረ ሐሳብ...እናት ሁነኝ ልትለኝ ነው? ሁኔታችንን ጠላሁት:: ለመሆኑ የእሷ እናት እንደኔ አባት ሲጠፋ አባቷ ምን አሉ? ምን ሆኑ?

"የእኔ ብቻ ሳትሆን የአብዮታዊት ኢትዮጵያም ሚስት ነች፤ ጓዶች ያፈላልጓታል" ብለው ሥራቸውን ቀጠሉ? ናፍቆት እያለቀሰች ስታስቸግራቸውስ?

"ቋ.......ቅ!"

"የአንቺ ብቻ ሳትሆን የአብዮታዊት ኢትዮጵያም እናት ነች፤ ጓዶች ያፈላልጓታል::"

ሳቅ ከጀለኝ:: የእኔና የናፍቆትን ሁኔታ አልወደድኩትም:: የተደገፈችውን ትከሻየን ሽተት አድርጌ ከንዴ ላይ አስተኛኋት:: እሷም ይሄንን ሁኔታ ለመሸሽ ይመስል ዓይኖቿን ጨፈነች:: ከንፈሯን በለዘብታ ስሜ አፏን ለጆሮዬ አስጠጋሁት::

"ተው፣ እንደዚህ አታድርግ" ስትል አንሾካሾከች:: ማንሾካሾክ ከመሳም በላይ፣ ከመኖር በላይ ይጣፍጣል:: ናፍቆትን ለሰው ሳስተዋውቃት ምን ልላት ነው? የከንፈር ወዳጅ? ይሄ ጣዕሟን መቀነስ ነው:: ናፍቆት የማንሾካሾክ ወዳጄ ናት::

* * *

ሆን ብዬ ናፍቆት በአከስቴ ከቤት መውጫ ሰዓት እንድትመጣ አደረኩ:: ወደ ቤት መመለሻዋም ላይ ትኖራለች:: አከስቴ በወርቆቿ ትስቃለች፣ በጥበብ ልብስ ጥልፏ ትንከተከታለች፣ ከሻሽ ባፈተለኩ አፋራም ፀጉሯ ታጮልቃለች::


t.me/OLDBOOKSPDF

"ጠኔስ?" እላታለሁ፡፡

"እሱ ባቡር ሃዲድ ብቻውን ይሄዳል፡፡ እኔን እንሂድ ሲለኝ እምቢ አልኩት" ብቻ፡፡

ብቻ የሰመጊ ጉዳይ ደለይ እንጂ..... እላታለሁ፡፡ የምቆርጥ ግን አይመስለኝም፡፡ ጠረኗ የአከሰቴን እየሆነ ሄዷል፡፡ የሚጣፍጥ፣ ስትሄድ የማይሄድ ለማዳ ሽቶ፡፡ እንገቷ ሥር ገብቼ እስማታለሁ፡፡

"ተው፣ እንደሱ አታድርግ" ትለኛለች፡፡

ዝም ያልኳት ቀን ይጨንቃታል፡፡

"ምን ሆንክ?" ፊቷ ላይ ያለመፈለግ ሥጋት፡፡ እኔ ደግሞ የመረረ ወሬ እንዳይመጣ ሥጋት..

"ይጋርዱ ቂጦ ትገ፤ ብለውኝ፡፡" እላታለሁ፡፡

"ባለጌ፣ እናትንና"

"እውነት፣ ይሄን ሰሞን በዓይኔ ላይ ይመላለሳል፡፡"

"ምኑ?" ካለች በኋላ እንዳልመልስላት አፌን በመዳፏ ትከድናለች፡፡ "ዝም በል፣ ዝም በል እናትንና" በዚያው ልፊያ ይጀመራል፡፡ ልፊያን ቁርጥራጭ የመተቃቀፍ ፍርፍር ልንለው እንችላለን፡፡ አንዱ አውቆ ሲሸነፍ ልፊያው ወደ መተቃቀፍ ይሸጋገራል፡፡ ደስ የሚል መተቃቀፍ ደረት ላይ ልብ እየናረ በድካም ይሁን በሌላ ያልለየ ትንፋሽ እየበረከተ.....ልጥፍ፡፡ ምን እንዳስገደደኝ ሳላውቅ፡-

"እወድሻለሁ"

"እናትንና ዝም በል"

ያኮረፍኩ ሲመስላት ጭንቅላቴን ይዛ አንገቷ ውስጥ ትወሽቀኛለች፡፡ "እኔም፣ እኔም በጣም እወድሃለሁ" እያለች ጆሮዬ ላይ ተለግታ ታንሾካሹካለች፡፡ ናፍቆት የተፈጠረችው ጆሮ ላይ ተለግቶ ለማንሾካሾክ ጥበብ ነው፡፡ እግዚኦ የማንሾካሾክ አምላክ! ምኗን አንሾካሿኪ ጣልኩብኝ? ፍቅር በጆሮ ይገባል? ምን እንዳስገደደኝ ሳላውቅ፡-"እወድሻለሁ!" የቁሪማንቁሪው ላይ ዘፋኝ ልሆን ነው እንዴ?


t.me/OLDBOOKSPDF

# 12

# የታላቁ ሰዓት ሠሪ መዘዝ

ናፍቆት የሰመሚን ጥርጣሬ ከመከላቷ ባሻገር ብዙ ያሚላችልኝ ነገር እንዳለ ይሰማኛል:: ምን ተብዬ ብጠየቅ የማልዘረዝረው ቢሆንም:: ግን ደግሞ አንድ ነገር ቀርቶብኛል:: ማንበብ አልቻልኩም:: ስለዚህ ቤት መጥታ ከማንኳኳቷ በፊት ወደ ኒኮላ ወንዝ ወርጄ ቱሬማንቱሪ ዛፍ ሥር እቀመጣለሁ:: አካባቢው ምስጢር የማያውቅ ግልጥልጥ ስለሆነ ምን ይመጣ ይሆን? በሚል ሥጋት ወጥሮ አይይዝም:: የኒኮላ እንጨት ቤት፣ የውሃ ወፍጮው አስከሬን፣ በጉርብጥብጥ ፊት ላይ የሚወርድ እንባ የሚመስለው ፏፏቴ፣ ሚካኤል የረገጠው ሴጣን ፊት የበቀለው የእንግጫ ቋጠሮ......ቢታ!

ስለ ሊዮናርድ ኢዩሊየርን የሚተርከውን መፅሐፍ ከጭብጦ መዝገበ ቃላቱ ጋር ይዤ ማንበብ ጀመርኩ:: ኢዩለር የሲውዘርላንድ ሰው ነው:: የኢዩለርን ታሪክ አንድ ሰው እስኪቀላቀለው ድረስ አጅግም አስገራሚነት አላገኘሁበትም ነበር:: የእሱ ሐሳብ ግኝት ከታላላቆቹ ሊቆች ጎን የሚያሰልፈው እንደሆነ ቢነገርም እሱን ችላ ብዬ ታሪኩን ተከታተልኩ::

ኢዩሊየር፣ ዳንኤል ቤርኖውሊ በተሰኘ ጓደኛው ገፋፊነት ሐይማኖታዊ ፅሁፎችን ማቅረብ ይጀምራል:: እንግዲህ ከዚህ በኋላ ነው ያ አንድ ሰው ተቃዋሚው ሆኖ ታሪኩ ውስጥ የሚገባው:: ቮልቴር ይባላል:: ቮልቴር በኢዩለር በኩል አድርጎ እኔም ህይወት ውስጥ ገባ::

ደነገጥኩ:: ጥርጥሬ እንደ አውሎ ነፋስ ሰማዩን እንስቶት አለፈ:: ቮልቴር ከዶ. እስኪያሳየኝ ድረስ ስለ እግዚአብሔር እስቤ አላውቅም ነበር:: ሁሌም እንዲጠላ ተፈጥሯዊ ድባብ ሁሉ ድንገት ሲገነጣጠል ለአደጋ እንደተጋለጥኩ ሆኖ ተሰማኝ::


t.me/OLDBOOKSPDF

አፊ «እሺ» አለ:: እጁ ግን ለአፊ እሺታ አልታዘዝ አለኝ:: የውስጥ-ሱሪዋ ጠርዝ ሌላ የሐሳብ መስመር አለው:: በስሱ የታፋዋን ላይ ላይ ከብቦ ይዟል:: እጄ አዚያ የሐሳብ መስመር ደርዝ ላይ ተመላለሰ:: በእጄ እንደዚህ ተጠቅሜና ጥሞኝ አላውቅም:: አፊ አፏን ዳግም ፈለገ::

ከበስተጓላዬ የምፈራውና የምሸሸው ስለአለ ይሆናል:: ናፍቆት ላይ ተጣበቅሁ:: ሙጥኝ አልኳት::

«ቱሪስት? ቱሪስት? ቱሪስት?...» ነቅቶ የማንቃት ጥሪ አልነበረም:: የሚጣራ፣ የሚታቀፍ፣ የሚስም ቃላት እንጂ::

እጄን ውስጥ-ሱሪዋ ጠርዝ ላይ ማመላለሴን ትቼ ወደታች ጎተትኩት:: ብስክሌት እንደምትነዳ ሁሉ እግሯን በተራ ከፍ ዝቅ እያደረገች የውስጥ-ሱሪዋን ወደ ግርጌ ሰደደችው:: እላይዋ ላይ ወጣሁ:: ምኔ እንደሆን የማላውቀው፣ ምኗ እንደሆን ያልተረዳሁት ውስጥ ሲገባ ናፍቆት ካለችበት ተመንጥቃ ረጅም የአሮጌ ሳንቃ ድምፅ አሰማች::

ነቃሁ ...ፀፀት አብሮኝ ነበር::

...እግዚአብሔር ሰውን ለአእምሮው ሳይሆን ለሴጣን ትቶት ነው የሄደው::



t.me/OLDBOOKSPDF

# 13

## የጠፋውን ፈጣሪ ፍለጋ

የሞጆን አውራ ጎዳና ተሻግርኩ «የአብዮት ፍሬ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት»የሚል የቆርቆሮ ቀስተዳመና ላይ ተፅፏል:: «የአብዮት ፍሬ»ተብሎ የተለወጠው በናፍቆት አባት ሳይሆን አይቀርም:: በፊት «የሞጆ ፍሬ»ነበር ስሙ:: «የሞጆ ፍሬ» ብለው ያወጡለት ደግሞ ጋሽ በረደድ ሳይሆኑ አይቀርም:: የሞጆ ወርቅ መሆን ያቃታት ሎሚ ከአነ ሰው ሰራሽ ቅንድቧ መጥታ ተደቀነች:: ሎሚን በናፍቆት ከላኳት:: ናፍቆትንስ?

የአንደኛ ደረጃ መምህርትና ሙና ከጀርባዬ ቀርተዋል:: ልጅነትም እንዲሁ.. ሪዛቸው ያቀመቀመ፣ የተላጨና ያጎፈረ ተማሪዎች ከዘጠኝ እስከ አስራሁለተኛ ክፍል ይማራሉ:: የትምህርቱ ፕሮግራም በሦስት ፈረቃ ይካሄዳል:: ጠዋት ከአንድ ሰዓት ከሩብ እስከ ለአምስት ሰዓት ሩብ ጉዳይ ድረስ ሁለተኛው ፕሮግራም ከአምስት ሰዓት እስከ ስምንት ተኩል ሦስተኛው ፕሮግራም ከዘጠኝ ሩብ ጉዳይ እስከ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል::

ግቢው ሰፊና ንፁህ ነው:: ወደ ቢሮው ሳመራ መምህርት ሙና በአዲስ ዓመት ውስጥ የሚንጠራወዝ የአሮጌ አመት ቁራጭ መሰላ መጣች:: የእሷን ማየትና አለማየት ማረጋገጥ አይቻልም? ፊቷ ላይ የተከደነው መንታ መግላሊት ወዴት እንደምታይ አያስታውቅም::

ምንድን ነው የምትከታተለኝ? መጽሐፏን ስላሽቀነጠርኩም ለፀብ ፈልጋኝ ይሆን የመጣችው? ወይስ የእሷን አስጠ'ኚነት ስላልተቀበልኩት?.... ዓይኗ እንዳላየ ላልፍ ስል እንደ ወፍ እየዘመረች ጠራችኝ::

"ሰባኪው መከብብ?"

ዝም ብዬ ቆምኩ::



t.me/OLDBOOKSPDF

"ልትመዘገብ ከሆነ እዚህ ግባ" አለችኝ፣ ከፊቷ ሰፋ እያደረገች:: ቀድሞኝ ስለተሰለፈች ቤቷ የመጣሁ ያህል የማስተናገድ ኃላፊነት እራሷ ላይ መጣሏ አስገረመኝ::

"አይ፣ ነገ ነው የምመዘገበው...."

በተኳለ ዐይኗ ፊቴን መኳኳል ያዘች። ልትነግረኝ የፈለገችው አንዳች ነገር ውስጧ ሲቋነጠነጥ ይሰማኛል:: ናፍቆትን አሳርፍልኝ ልትል ይሆን?

"እሺ፣ በቃ እስከ በሩ አብረን እንሂድ" ብላ ከወረፋዋ መስመር አፈነገጠች:: ከኋላዋ ላለ ጎረምሳ እንደምትመለስ ስትነግረው በዛገ ጥርሱ ፈገግ አለላት:: አቀርቅራ ከጎን ከጎኔ መሄድ ጀመረች::

"ከየት ትምህርት ቤት ነው እዚህ የተመደብሽው?" የወሬ ዳርዳርታየን ከፈትኩ::

"ከፋብሪካ ነው::"

"የፋብሪካ ልጅ ነሽ?" አልኳት

"እዎ" አለች::

እኔ፣ ጦጤ፣ ናፍቆት፣ ንዳዴና ጠኔ ሆነን እንረብሸው የነበረ የፋብሪካ ሠራተኞች መኖሪያ ትዝ አለኝ:: ይኼኔ የእሷኑ ቤት ምድጃ ገልብጠናል፣ ቧንቧውን ከፍተን ተራጭተናል፣ የደጅ አምፖሉን ሰብረናል.....

"አሁን እኔን የቸገረኝ የብዙዬ ነገር ነው?"

"ጀሮው ላይ ላንሾካሹክ ስትይ እምቢ አለ?" ብዬ ለመጠየቅ ዳዳኝ::

"ምን አደረገ?"

"አስቸጋሪ ሆኗል፣ ብታየው" አለችና የተኳለ ዐይኗን አሳዝና "አሁንማ ብሶበታል፤ ትምህርት አልቀጥልም፣ አልመዘገብም ይላል::"

"ለምን?"

"ውትድርና እሄዳለሁ" እንባዋ ዱብ ዱብ አለ:: ዐይኗ ላይ ሲታይ ለተቋረጠ የሚያደላው እንባዋ ሲወርድ የቆዳዋን ቀለም ይዞ ይንቆረቆራል::



t.me/OLDBOOKSPDF

የከሳችው የጠቆረችውኮ እሷ ናት። የፍርጃ ፍቅሯ ከመውለድ በላይ ሆነባት። ሽቶዋን ሳጣ መንፈሷ እንደሌለ ሆኖ ተሰማኝ። እናቴ ናት ጠሷን እሷ ላይ ጥላ የሞተችው። መረረኝ፣ አስጠላኝ......


t.me/OLDBOOKSPDF

# 14

## የጠፋውን ለማግኘት

"እኔ ልሁን እንጂ
የማልጠቅም ርካሽ፤
ምንም ጊዜ ቢሆን
አንቺን ክፉ አይንካሽ፤
.....መኖሬ ይሰረዝ
ህይወቴ ይበል ውድም፤
ልማትሽን እንጂ አሃሃሃሃ
ጥፋትሽን አልወድም
አያያያያያይ
አያያያያያይ
ዋዋዋዋዋ
ዋዋዋዋዋ....."

የቱሪማንቱሪው ላይ ጃፌ በማለዳ ቀሰቀሰኝ። የአባቴ አጥሬ መንፈስ እንደሰፈረበት የተረዳ አይመስልም። ብዙም ሳይቆይ ደጃፌ ተቆረቆረ። ማነው? ሳልል ከፈትኩት። የቱሪማንቱሪው ላይ ጃፌ ነበር። ጥቁር ብቻ በሆነ አንድ ዐይኑ እንደ ጭልፊት ገደድ ብሎ በጎን ተመለከተኝ።

"ጋሼ፣ መሄጃ ነው እንግዲህ" ቱሪማንቱሪ ቱሪማንቱሪ ይሸታል።

'ጋሼ' ሲለኝ ውሃ ሰማያዊ የናፍቆት አባት ትዝ አሉኝ። አማችነት እንደ ሥጋ ጠርቷቸው ተዋሱኝ። የጭንቅላት ውስጥ ጨዋታዬ ወገቡን እንደተባለ አባብ መካከል ላይ ቆምጥ ሲል ታወቀኝ።

"ወዴት?"



t.me/OLDBOOKSPDF

ቁመት ባላቸው ወንበሮች ተከበዋል:: የወንበሮቹ ሆነ የጠረጴዛዎቹ አደራደር የመማሪያ ክፍል ወግ ሳይሆን የታላቅ ስብሰባ ሥርዓት አላቸው::

በስተ ጎን በዘመን ብዛት ወደ ነጭነት ያደላ ቡናማ ጥቁር ስሌዳ አለ:: ሙና ፊት ለፊቴ ተቀመጠች::

"የጠፋው እግዚአብሔር ተገኘ? ማለቴ ባንተ የእውነት ሀሰሳ" የአባባይ ወፍ ድምፅ

ምን ልበላት? ድንገት ሆነብኝ:: የእሷ ዘና ማለት እኔም ተጨናንቄ መነጋገር እንደሌለብኝ ሹክ አለኝ::

"አልተገኘም፤ እሱን ስፈልግ እኔ ጠፋሁ" ፈገግ አልኩላት:: ሁኔታዬ እሷ ወደምትፈልገው እንዳደረሰኝ ባውቅም ገዴት አልተሰማኝም:: እንደ ፈረስ በዳበሳ ገራችኝ? እሷና አከሰቱ::

ጭንቅላቷን ፈንግላ ሳቀች:: ደባደቦ ሹራብ አድርጋ የመምህሮች ካኪ ካፖርት ስለደረበች አንገቷ ጠፍቶ ከወገቧ በላይ አጥራለች::

"እንዴት ጠፋህ? እስኪ ንገረኝ?" ሳቋ ሳይጠናቀቅ ስላወራች ቁርጥራጭ ካካታዎች ንግግሯን ጉራማይሌ ውበት ሰጡት::

"ቢቃ፤ ዛሬ ሌሊት ያየሁትን ልንገርዎት?"

"ንገረኝ" ወፍ ከሳቅ ጋር ብትዘምር እንዲህ ነው::

"እግዚአብሔር ደከሞትና ጫማው ሰፍቶት በሆነ የብርሃን ጉበን በኩል አልፎ ወደ ጨለማ አለም ሲጠልቅ አየሁት:: ከዚህ በፊት በተደጋጋሚ ባየውም አልከተለውም ነበር:: ዛሬ ሌሊት ግን ተከተልኩት:: ከጨለማ የተዋቀሩ ጥቂት ዛኒጋባዎችን ብቻ አገኘሁ:: እሱ የለም:: ወደ መመለሻዬ ስመለከት የብርሃን ጉበኑ ከበታው ተነስቶ ድቅድቅ ጨለማ ብቻ:: ላብድ ነው::"

"አታብድም፤ ጭንቅላትህ የማሰብ አቅሙ አስገራሚ ነው:: ግን የአቅሙን ያህል የተለያዩ ዕውቀቶችን አልሰጠኸውም:: መልሶ መላልሶ ከተለያየ አቅጣጫ የሚያስበው አንዴ የተገረምከበት የእግዚአብሔርን መጥፋት ጉዳይ ነው::"


t.me/OLDBOOKSPDF

"እውቀትም ከሆነ መቼም የዚህ ተቃራኒ ሌላ እውቀት ሳይኖር አይቀርም::"

"እሰ! እሱም እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ:: ጭለማና ብርሃን አደረገ:: ወዘተ ብሎ ጭጭ!"

"ይሄ አማራጭ መዳረሻው ቅርብና ፍፁማዊ አይመስልዎትም? ከተፈጥሮ ጋር በአዲስ መልክ በተዋወቁ ቁጥር እግዚአብሔርን እንደ አዲስ ማንሳት መጣል መቆሚያው የት ነው? አይታክትም? እኔን ታክቶኛል:: መድረሻው የማይታወቅ ጉዞ ሆኖብኛል:: ጠቀሜታውም አልታይህ ብሎኛል::" ሁሉንም ነገር አፈራርሼ መውጣት አሰኝቶኝ ነበር:: ሙና ተናገረች:-

"የሰው ልጅ ቢፈልግ እንኳን የማያገኘው አለማሰብ፣ አለመጠየቅና አለመመርመርን ነው:: ማሰብ መመርመርና መጠየቅ የሰው ልጅ እጣ ፈንታዎች ናቸው:: ማሰብ ስለተውከው አይተውህም:: እጅ መስጠትን የሰው ልጅ አጠቃላይ መፍትሄ አድርገህ ለማቅረብ እየሞከርክ ነው:: እጅ በመስጠት ባርነት እንጂ ሠላም አይገኝም::"

አልቻልም እንጂ ከዚህ በላይ ብጠነክርባት፣ ከዚህ በላይ ታይላለች:: ፈራኋት::

በዚች ቅፅበት በተከፈተው የቤተ ሙከራ መስኮት በኩል ምዕራፍ ብቅ ብላ ጭንቅላቷን ስትሰበስብ በጨረፍታ አየኋት:: ትከታተለኝ ነበር? ምን ጠርጥራ፣ ምን ለማየት ተንጇከከች?


t.me/OLDBOOKSPDF

# 15

## ህልም ሽሽት

ቮልቴር ስራይ ሆኖ የማይነቀል ህልም ተከለብኝ:: ከመደጋገሙ የተነሳ እንደ ወዳጅ ቤት ከደጃፍ እስከ ጓዳ ጎድጓዳ የማውቀው ህልም ገና ሲጀምረኝ አውቃለሁ::

"ዛሬስ አያመልጠኝም፣ ዛሬስ አያመልጠኝም......" እላለሁ:: እንደተለመደው እግዚአብሄር ከኋላዬ መጥቶ ጫማውን እየጎተተ ያልፋል:: የብርሃን ጉበኑን ከማለፉ በፊት እደርስበታለሁ:: ጫማው ብቻ ቀን የሰበሰበችውን ብርሃን በጨለማው ትታለባለች:: የጥንድ እግሮቹን ፍርቅርቅ እያጤንኩ "ፈጥረህ ወዴት? አድርገህ ወዴት? ይሁን ስትል አልሆነምን? በቃልህ ካለመኖር ወደ መኖር የመጣትን በትነህ ወዴት?......." እያልኩ እነዘንዝዋለሁ:: በመካከሉ መኃል ጫማው ግርማውን ሲያጣና ሲቀል ቀና እላለሁ:: እግዚአብሄር የሚራመድ ጫማውን ትቶልኝ ሄዷል:: እንባ የሌለው ደረቅ ለቅሶ......

......የእኔ ደረቅ ለቅሶ ደረቅ የሴት ጩኸት ተቀላቀለው ነቃሁ:: የእኔ ለቅሶ ቢቆምም የሴቷ ግን ቀጥሏል:: እንደውም አጃቢ ጩኸቶች ከበቡት::

"ኡ! ኡ! ኡ!"

"ምንድን ነው? ምንድነው?"......"

"በስመአብ!"

አከሰቴ ትገዝ አለችኝ:: ተስፈንጥሬ ተነሳሁ:: በባዶ እግሬ የጓሮውን በር ከፍቼ ወጣሁ:: በረት ገልባጭን መንፈሴ አላመነውም:: ሰዎች ወዳተኮሩበት በደመነፍስ አመራሁ:: አንዳንድ ሰዎች ከፊቴ ይንቶስቶሳሉ:: ከእቅሌ ሳልሆን ጋሽ በረደድ


t.me/OLDBOOKSPDF

እንደው ነው አለችኝ:: እየሳምኩ እያሻሸሁ አላይዋ ላይ ወጣሁ: ተው ልትል አልቻለችም:: እጥበቴ መሳሜን ቀጠልኩ እየፈለፈልኩ እየፈለፈልኩ እግሯ መካከል ገባሁና በቀዳዳዋ ልክ አስደግፌ ተውኩት"

"ፓንቷ እያለ?" ድፎ...

"አዎ" ከመዘዘው ጫት ቀንጣጥቦ አፉ ከተተና ቀጠለ "በወገቢ እየሰራሁ መሳሜን ቀጠልኩ ሰውነቷ ሁሉ ሲወጣጠር ይሰማኛል:: ዝም ብዬ እየተንቀሳቀስኩ፣ እየሳምኩ እያለ አፏን በግድ አልላቃ አንዴ እንደሆነ ከነጢያት ተመዘግቧል አለችኝ:: በለኝ በታንክ!...."

"ምን ማለቷ ነው?" ድፎ፣ ንዳዴ እታቋርጥ በሚል ጎሸም አደረገው::

"በ...ለ...ኝ.... ነዋ፤ በፍጥነት ፓንቷን አወለቅና ስራራኋታ! አልኳት፣ አልኳት፣ በመጨረሻ ምን ብትል ጥሩ ነው?::

"ምን አለች?" ድፎ

"በያም ሻይ ነው ብለህ ወተት እንዳጠጣኸኝ ስለሚቆጠር ኀጢያቱ ባንተ ነው:: በለኝ በታንክ!!"

ወሬው ሲጠናቀቅ መጠነኛ ጭቅጭቅ ተተካ:: "ጫቱ ትንሽ ነው:: ማግምሻችንን በጊዜ ልትጨርሰው ነው?" አለ ንዳዴ::

"እንዴ? መዝሏል እንዴ?" ድፎ ድምፁ ሆምጥጧል:: ከተበካበት እርሾ ይሆን? ጭቅጭቁ ቀጠለ፡-

"ቤቱ ነው ብለህ ነው? አበዛኸው" ንዳዴ እንደናፍቆት በጭንቅላት ውዝዋዜ ለመነጫነጭ ሞከሮ አሏጋው ስላላመቸው ተወው::

በዚህ መካከል ሁለት ብር አውጥቼ ሰጠኋቸው:: ኮርማ ማመን አልቻለም:: እየተርበተበተ ድፎን ላከው::

የብር ከሃምሳ ሙሉ ጫት፤ እ? ሲጋራ ደግሞ በሰሙኒው አምስት ግዛ፤ በፍጥነት! ስኳር ሻይ ቅጠል....."

ንዳዴ በስጋት አየኝ ገብቶኛል:: ሲጋራ ስለተነሣ ነው:: ኮርማ መከተንግዶውን አጧጧፈብኝ:: አሏጋ ላይ በግድ ውጣ አለኝ:: ጫማዬን ሳወልቅ



t.me/OLDBOOKSPDF

እያፈረች "ተው እንደዚህ አትበለኝ" አለችኝ::

"ናፈ ሙት፤ ጆሮ ጌጥም አድርገሻል"

የበሰጠ በማፈር እስሬ ገባታ ተሏመጣመጠች:: ያቺ ቀንድ እጅ በትዝብት ታየናለች:: ሳፈጥባት ኮርማን በሥራ የምታግገ መሰለች:: እሷን አሳፍሬ ስመለስ ንፃይ በተመሳሳይ አይታ ላይ ነበር::

የተንደረከከው ክሰል ላይ የሻይ ጀበና ተጣደ:: "ኮርማ ተፍተፉን ትቶ ተቀመጠ:: ሰቷ በሬ ትክሻውን ተደግፎ እንደመታከክ ያደርጋታል:: በዚህ መካከል በር ተከፍቶ አንድ ብልጣ ብልጥ ልጅ ገባ:: አጭር ነው፤ ሰውነት የለውም:: ጠይም ፊቱን ጎላ ያለ አፍንጫው ሞሌቶታል:: ንፁህና ፀጉሩን በአግባቡ ያበጠረ ነው::

"ቆቋ፤ ቆቋ፤ ቆቋ" ተንጫጩ:: ሁሉም የሚወዱት ልጅ ሳይሆን አይቀርም:: ቃልቡ ደጅ እንዳለ ያስታውቃል:: መሰሰ ብሎ እንዴት የቀትር ፀሐይ የመሰለች ልጅ መገዞ አስገባ:: ዘለግ ያለች ናት:: ትኩስ ፍቅር ላይ፤ እንደሆኑ ያስታውቃል:: ሁለቱም ጨብጠውን ወደላይኛው አልጋ በመሰላል ወጡ:: የልጅቷ እግር እይኔ ላይ ተላከኮ ቀረ:: ረጃጅም ጣት:: እንዴት ያምራል እልኩ ሰራሴ:: ናፍቆት በትዝብት ያየችኝ መሰለኝ::

"እግሯ ያንቺን ይመስላል" አልኳት

"ተው እንደሱ አትበል" ሐፍረቷን ተከናንባ እስሬ ገባች::

ድሮ ሲመጣ ኮርማ ቀድሞ ጫቱን ተቀብሎ ብዛቱንና ጥራቱን መፈተሽ ጀመረ:: ድሮ ላብ፤ በላብ ሆኗል:: መጠለያችን በድሮ ዳቦ ሽታ ተሞላች::

"ሲጋራውስ?" አለ ኮርማ:: የሚያጨስ በሬ ታይቶም አይታወቅ ስል አሰብኩ:: ድሮ አውጥቶ የሲጋራ ፓኬት ሰጠው:: "እንዴ? እንዴ? ማን ጉሬዛ ግዛ አለህ?"

"አምስት ከሚገዛ አስር አይሻልም?"

"በለኝ በታንክ!ኒያላ አይደል እንዴ የተባልከው? ለዚህ ለዚህ ፓኬቱን ጉሬዛ በአስራ አምስት ሳንቲም አትገዛም?"


t.me/OLDBOOKSPDF

"እሺ."

"በለኝ በታንክ!! እናትን እሺ? አሁን ቶሎ ሄደህ በኒያላ ቀይረው"

ድሮ ድሮ መሸተቱን ይዞ ወጣ። ከሻዩ ሽታ ጋር እናቴ በዓመት በዓል ሰሞን የምታቀርብልኝ አስልቺ ምግብ ትዝ አለኝ። ድፎ ዳቦ በሻይ። ለመንከር ያዳግታል። ቡጡን ሻዩ እያፈረሰው ብርጭቆ ውስጥ ይቀራል። በመጨረሻ ሻዩ ቀለሙን ቀይሮና ደፍርሶ እምቡሽ ቡሽ ጠላ ይመስላል። ያን ሰሞን አባቴም ከእኔ ጋር በድፎና በሻይ ብዛት ጢንቢራው ይዞራል። ሲበዛበት ለእናቴ ተረት ይነግራታል።

"እናልሽ ሰውየው..."

"እጅህ ነው የሚያወራው?"

"ግዴለሽ ሚስት አግብቶ ቁርሱ፣ ምሳው፣ እራቱ ድፎ ነው። ሰልችቶታል። ከእርሻ ሲመጣ ወደ ቤት ጭንቅላቱን አስገብቶ ዛሬ እራት ምንድነው? ሲል ሚስቱን ይጠይቃል።

'ድፎ' ሚስቱ ትመልሳለች

"ምን ድፎ ትይኛለሽ ይድፋህ በይኝ እንጂ አለ እሱ...እሃሃሃሃሃ" ብቻውን ይስቃል። የሚያጅበው ሲያጣ ሳቁ ትመከናለች።

"እጅህን አሳርፍ.. ሰውዬ!"

ይሁንና ነገ ቁርስ እንደሚለወጥ መተማመኛ ይኖረኛል። በስንት ጊዜዬ አባቴን አስታወስኩ? ኤሎሄ፣ ኤሎሄ፣ ለምን ተውከኝ ማለት አሰኘኝ።

* * *

ማታ ከጫት መቃም በኋላ ተያይዘን እንወጣለን። ጨረቃ አካባቢውን ከብር የተሰበጠ አስመስላዋለች። ጎፈሬውን ያሳመረው ግራር በዝርዝር ቅጠሎቹ መካከል ብርማው የጨረቃ ብርሃን ይስገሰግና የብር ማርዳ ይመስላል። የሞጆ ዳለቻ አፈር የብር ብዝብዝ መስሎ ይነጠፋል። ቱሪማንቱሪው እራሱን ችሎ ምድር ላይ የበቀለ ሳይሆን እድማስ ላይ የተለጠፈ ይመስላል። በዚያ መሃል ቆቁና ሚስቱ ከፊት



t.me/OLDBOOKSPDF

"እናትንና ሥርዓት ያዝ" አለችው ናፍቆት::

በሰውነቱ ሁሉ ተንሜነጨ::

ግዙፉ ሰው ረጅም ሹራብ ለብሷል:: ቤቱን ከጣሪያ ጀምሮ ስለሞላው የሹራብ መጋረጃ መስሏል:: ሞጆ ውስጥ ሹራብ የሚለብስ እሱ ብቻ ሳይሆን አይቀርም "ሥምና ቂጥ!" አለ::

"ከዚህ ጋር አውራ!"

ምዕራፍ ብቅ አለች:: አዘናግቼ ወጣሁ:: ራት ብላ ጠራችኝ:: ሄድኩ:: እኔን ያፈቀረች ሆኖ ተሰማኝ:: ትስቁልና ፊቷ ላይ ይታያል:: "ተከሲሱ፣ ቁርባኑ፣ ዕድቱ ቀርቶብሽ በቅጡ በኮነነሽ" በሚል ሐሳብ ውስጢ የተፈጠረውን ሐዘን ወገቡን አልኩት::

"ብዙ እንዳይጠጣ"

"እሺ"

"እንዳይጣላ"

"እሺ"

"ውጭ እንዳያድር"

"እሺ"

ፍቅር እናት አድርጓታል:: አክስቱን መሰለችኝ:: አክስቴ እየሰከርኩ ባስቸግራት እንደምዕራፍ የምታደርግ ይመስለኛል:: እሷ ግን እኔን ለእኔ ኀላፊነት ሰጥታ እራሴን በእራሴ ታስጠብቃለች::

ምዕራፍ የንዳዴን ኀላፊነት ለእኔ ስትሰጠኝ ወደ ቤቷ የምትሄድ መስሎኝ ነበር:: ግን ከገባሁም በኋላ በተደጋጋሚ አይቼአት ከማዘን ይልቅ ተናደድኩባት::

የሹራቡ መጋረጃ ቦታው ላይ የለም:: ንዳዴ ተነሥቶ ለሽንት ወደ ጓሮ ዞረ:: አካሄዱ እግሩን ከፍቶ አካባቢውን እየገለመጠ ነው:: ከጥቂት ፀጥታ በኋላ ሲኖሪና መጥታ:-

"ኑ ጉዳችሁን እዩ" አለችን



t.me/OLDBOOKSPDF

ተከተልናት:: ንዳዴ ሽንቱን ሽንቶ ግድግዳ እንደተደገፈ እንቅልፍ የወሰደው መስሎኝ ነበር:: ከናፍቆት ቀጥሎ ስገባ ግን ያየሁት ሌላ ነው:: ግዙፉ የሹራብ መጋረጃ ግድግዳ ተደግፎ በቀጡ ዘጭ ብሏል:: ንዳዴ ከበላዩ እግሩን እንፈራጥጦ በሁለመናው ይንቆራጠጣል:: ግዙፉ በፀጥታ ይናውዛል:: ፊቱ ደም በደም ሆኗል::

ሲኞሪና ውኃ በጠርሙስ አምጥታ ሰውየው ፊት ላይ መርጨት ጀመረች:: ንዳዴ ይቆረቆርለት ይመስል::

"ተይው ተይው" ይላል::

"ዝም በል" አለች ሲኞሪና፣ አፈጠጠችበት:: ዓይኑን መለስ አደረገ:: "አንተን ነው እንጂ መርጨት" በማለት በእፍኟ ሙሉ ውኃ ሞልታ ንዳዴ ፊት ላይ ረጨች:: ግንባሩን ሳያጥፍ በሁለመናው እየተነጫነጨ ዝም አላት::

"እጁ ላይ ሰው ይጠፋል ወይም እሱ.... ይዛችሁት ግቡ:: እኔ ሰውየውን በጓሮ አስወጣዋለሁ" አለች:: ንዳዴን ይዘን ገባን:: የብረት ምጣድ ተራው መዚቃ ተቀበለን::

የንዳዴ ስካር ንዴት ነው:: ምክንያቱ ግልጽ ያልሆነ በዓለም ላይ ሁሉ መበሳጨት:: አንዳንዴ እራሱን ይመታል:: በንዴት የመንፈጭፈጭ ሳቅ አለው:: መትከንከንና መብከንከን የተሞላበት ይሄን ሳቁን ሲለቅ የምትደፍረው ናፍቆት ብቻ ናት::

"ኮፊኑን ከፊተ" ትላለች::

"እገድላታለሁ፣ እገድላታለሁ" ይላል አይኑ እየሸሸት::

"እኔ አልገድልህም? እናትንና"

ሁለቱ ሲጣሉ ደስ የሚል ነገር ይሰማኛል:: ወደ ቤት እየሸኘነው ከሆነ ምዕራፍ ከኋላ ከኋላ መከተሏን ትታ እኔ ሥር ትሸጎጣለች::

ንዳዴ እሷንም ላለማየት ይጠነቀቃል:: ሲጣሉ በየመሃሉ ኮርማ ዘዬውን ይደጋግማል:-

"በለኝ በታንክ!"



t.me/OLDBOOKSPDF

ምን ማለት ይሆን?

ምናልባት በበሬኛ ፍቺ ይኖረው ይሆናል፡፡ ሚስቱ አሰሩ ገብታ ትፍለከለካለች፡፡

"በለኝ በታንክ" ቆቁ ይሄን አለምና ጣጣው ለኛ ትቶ ከእሷ ሌላ የማይፈልገውን ሚስቱን ይዞ ይቀድማል፡፡ ሰው ይሄው ነው፡፡ እንዴን ከፈለገ ለተቀረው ያን ያህል ነው፡፡ የሚጠቅም ከመሰለው ገንዘብ፣ የሚረካ ከመሰለው ሴት፣ የበላይ የሚሆን ከመሰለው ሥልጣን፣ ያለ ካመሰለው እግዚአብሔር... የትኛው ሕዋ ሥር ተሸጎጠ? እኛን ለመሸሽ ወይስ እራሱን? ፈጥሮ ከመጥፋት የፈጠሩትን ማጥፋት አይሻል ይሆን? ..... ጭንቅላቱ ይወጠራል፡፡

ንዳዴ በንዴት እራሱን እስኪስት ከሰከረ ተሸከመን አልጋው ላይ እስከንጥለው የእንጀራ እናቱ ትጠብቃለች፡፡ በእግሩ ከመጣ ደግሞ ገና በር እንደከፈተች ጀርባውን መድቃት ትጀምራለች፡፡

"ተውዋት ትጎስመኝ" ይላል ንዳዴ!! ከከርጉ ከፍ ብላ ትነክሰዋለች

"ተውዋት ትቦጭቀኝ፣ ተውዋት ትቦጥቡጠኝ፣ ተውዋት ትድፋኝ፣ ተውዋት ትሰርስረኝ፣ ተውዋት....."

በተስፋ መቁረጥ ስታለቅስ

"ተውዋት አንጀቴን ትብላኝ"


t.me/OLDBOOKSPDF

# 16

# ከሽሽት መልስ

እያንዳንዱ ቤት የየራሱ ባህል አለው፡፡ የሥርዓት ባህል፡፡ ይሄን ባህል የሚደነግገው የአማዳሪው ያልተጻፈ ሕግ ነው፡፡ ሕጉ የሚመነጨው ደግሞ አሳዳሪው ከሚወደውና ከሚጠላው ነገር ነው፡፡ የአከስቴ ቤት ባህል ፍቅር ነው፡፡

"ከሳህ" ትለኛለች የተኛሁበት መጥታ እራሴን እያሻሸች፡፡ አሁንም ለእሷ ትንሽ ልጅ ነኝ፡፡ እዚህስ እንደፈለገች፤ እህል በረንዳ ሰው መካከልም ጭኗ ላይ ልታስተኛኝ ትስበኛለች፡፡

"ጠቆርክ፣ ተጎሳቆልክ...."

የሰሞኑ ተንከራታችነት የፈጠረባት የሥጋት ስሜት እንደሆነ አውቄአለሁ፡፡ ከፍቅር ተነስታም ቢሆን መጥፎ ተግባሬን ማንሳት አትፈልግም፡፡ እኔን ለራሴ ጥቢቃ ትታኛለች፡፡ ሽቶዋ ውስጥ እየዋኘሁ ዝም እላታለሁ፡፡

"እኔ ሲከፋኝ ደስ ይልሃል? ታዲያ ለምን አትበላም? ለምን አትጠጣም?"

ሰንጥበ እንዳለኝ ሁሉ የሽቶ ባህሯ ውስጥ እየተነፈስኩ ትኝት ግንባሬን ስማ ትወጣለች፡፡ ለተወሰኑ ደቂቆች ፀዳሏ ከፍሌን ሞልቶት ይቆያል፡፡ ቶሎ የማይወጣው ሽቶዋ ነው፡፡

ያ የቱሪማንቱሪ ላይ ዘፋኝ ቢኖር ምን ብሎ ያንቋርር ነበር ይሆን?

ቅጣንባሩ የጠፋው የመምህርት መና ነው፡፡

"እንዴት ነው?" ትላለች

"ያው ነው" እላታለሁ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

በሚሰለመለያም ልስን መንፀር ታየኛለች:: መንፀር ይሰለመለማል? እንጃ! እንደቢ ቅጣንባሩ የጠፋ የፊዚክስ ቀመርና ንድፍ ላቦራቶር ከፍሎን ሞልቶታል:: ኒውተን እግዚአብሔርን ከተደበቀበት የሕዋ ሥርቻ ያገኘው ይሆን?

"አሁንም ሕልሙ ተደጋግሞ ይመጣል?"

በጭንቅላቴ አዎ አልኳትና መሠላቸት አሳየኋት "ላንቺ ስነግርሽ ተራ ትዕይንት ይመስላል:: እንዳች የሚያም ነገር አለው:: ሕይወትን የሚያስጠላ፣ ሞትን የሚያስመኝ::" እንደ ጦጢ ድሬዳዋን እንደተመኘ ያለበትን እንደጠላ... ግን አከስት::

ሙና ስትደነግጥ ድንጋጤዋ ቀጭን ነፍስ ሆኖ ትከሻዋ ላይ ግል ያደረገችውን ላይነን ቫሽ ግልብ አደረገው:: እንዴት? እንጃ! በአዲሱ ሽለምጥማጪ ከወዲያ ወዲህ ሽር... ሽር አለች:: አሳዘነችኝ:: በልብስ ምርጫዋ አማካሪ የሌላት ብቸኛ እንደሆነች ገብቶኛል:: እንደ እኔ አከስት ልብስ ገዝቶ አምጥቶ እንድትለብስ የሚያስገድዳት ያስፈልጋታል:: አሁን እዚህ ዘመን ላይ የሚኖር፣ የዚህ ትውልድ ተሳትፎ እንዲህ ያለ አይጥና ሽለመጥማጥ የመሰለ ሻማ ይገዛል? መነፅሯስ? ቀሚሷስ? የካህናት ልብስ ሠፊጋ ነው እምትሄደው?.

"ትቅማለህ፣ ታጨሳለህ፣ ትጠጣለህ፣ ትደባደባለህ....." ተንቋራጠጠች:: የአከስቴ ተቃራኒ መሆኗ ነው:: ይሄን ሁሉ የደረደረችው ምን ጉድሎብህ ትሞታለህ ልትለኝ ይሆን? ዝም ብዬ አየኋት::

"አብረህ የምትውላቸው እንዳቸውም አንተን አይመስሉም"

"እንዴት?"

"ሁሉም ተሰፋ ቢስ ዱርዬዎች ናቸው::"

ምን ግርር ግትር አደረጋት? መነፅሯ በንዴት አፈጠጠብኝ:: "ዱርዬ" ስትል ውስጤ ንፁህ፣ ንፁህ፣ ንፁህ አለ::

"አንድ ነኝ"

"አይደላችሁም! አይደለህም! እነሱ ዱርዬነትን የመጨረሻ ተስፋቸው ያደረጉ ናቸው::"



t.me/OLDBOOKSPDF

የሴት ፍርሃቴ መጣብኝ:: አሁን ልምታህ ብትለኝ ምን አደርጋታለሁ? ተንበርከክ ብትለኝስ? ወደልምምጥ ገባሁ::

"እስኪ እኔ የማስበውን አድምጪ" የድምጼ መለሳለስ ወደቀልቧ ትተታት

"ምን ልታስብ ትችላለህ በቃ በድክመታቸው ጥንካሬህን እረትተውት እነሱን ለመሆን እየጣርክ ነው::" በሽለመጥመጧ ተንሜነጨች::

"በመጀመሪያ ደረጃ አልቅምም፣ አላጨስም፣ አልጠጣም:: እነዚህን የማላደርገው ግን ዱርዬ ላለመሆን አይደለም:: ከዚያ በላይ ያለ ነገር ውስጤ ሆኖ ስለሚከላከለኝ ነው::"

ዝም ብላ መማላሊት በመሰለ መነፅሯ ታየኛለች::

"እነዚህ ዱርዬ ያልኻቸው ጓደኞቼ የእኔን ሊላኛ ዕጣፈንታ የሚኖሩ ልጆች ይመስሉኛል"

መነፅሯ "አልገባኝም፣ እንዴት?" አለኝ

"እየተፈላሰፍኩ አይደለም:: እንዳልሽው ከእኔ ፍላጎት ጋር የሚገጥም ፍላጎት የላቸውም:: ግን የነገሮች ጥቂት መስተካከል አሁን እንደምታውቂኝ አደረገኝ እንጂ እስኪ አሰቢው....

"እናቴ ደካማ በመሆኗ እንጂ የአባቴን መጥፎት ብትቋቋም ኖሮ የምታሳድገኝ ጦጤ በተባለው ጓደኛዬ እናት ስልት ነበር:: ትባትላለች፣ ትባትላለች.... በመጨረሻ እእ ስጠፋበት በር መዝጋት እቅቷት ጅብ ይበላታል::"

"እንዴ እንዴ?"

"ቆይ፣ እጣፈንታዬ ባቡር ሲመጣ ተንጠላጥዬ ሻርፕ ከመንጠቅ የተሻለ አይሆንም ነበር:: ጓደኞቼ እንዲያገኙላት አድርጌ ከተነጠቀው እንዲረጠቧት......." አለቀስኩ እንጂ!

"እስቲ እኔ ያልኩት....." አለች አቋረጥኳት

"አባቴ ደካማ ባይሆንና እናቴ እስከትሞት ጠብቆ ሌላ ቢያገባ ብለሽ አሰቢው:: እንጀራ እናት ማለት አይደል? ሰዚያች እንጀራ እናቴ ጥሎኝ ቢሄድስ?


t.me/OLDBOOKSPDF

ንዳዴን ሆንኩ ማለት አይደል? እሱ የሚያደርገውን ከማድረግ ምን ይከለክለኝ ነበር....."

"ይቅርታ፣ በጣም ይቅርታ....."

"ዱርዬነት ዕጣፈንታ ነው:: ሁሉም አቢታቸው መብላት ሲያቅታቸው ነው ወሟ ያለውን የውርደት ምግብ የሚሾት:: አለበለዚያ እንደእኔና እንዳንቺ ዕዩፍነት ከውስጣቸው ተሟጥጦ አያልቅም ነበር"

"ይቅርታ አልኩህ አይደል?" ሲብስባት መጥታ እንገቷ ውስጥ ፊቷን ከተተችው:: አንገት ነበራት? እንጃ! የአከስቴ ተቃራኒ አለም፣ የውኃ ጠረን:: ከተፈጥሮ ያልተፋታ ሽታ፤ የመነፅሯ እጀታ ከጆሮዬ ከፍ ያለ ቦታ እርፎ ትገዛዛ ተሰማኝ::

ካልተቆሰቆሰ የማይነድ፣ ካልተገላለጠ መዳፊት የማይታወቅ የአሳት ባሕርይ ያለው ትውስታ መኖሩን ዛሬ አውቅሁ:: እነ ጦጢን የምረዳው እንደዚህ ነበር? ከእነንዳዶ ጋር ያጣበቀኝ ይሄ ኖሯል? እንጃ! መረጋጋቴን ካረጋገጠች በኋላ አንድ ጥያቄ እንደ ዘበት ጣል አደረገችልኝ::

"አባትህ ጠፍተዋል?"

*            *            *

ዳለቻው ምድር ቀና ብለው እንዳዩት ሰማይ ዓይን የሚያደናቅፍ ነገር አልበቀለበትም:: ለሥዕል የተዘጋጀ አቡጀዲድ ይመስላል:: እሱን ስመለከት እግዚአብሔር ሥራውን አጠናቆ ስለመጥፋቱ ተጠራጠርኩ:: እቋርጦ በመሰልቸት ነው የጠፋው::

በር ብቻ ያለው ቤት ደጃፍ ላይ ተቀምጬ ይሄን ሳስብ ጋሽ ጥበቡ መተኮሻ ቆርቆሮአቸውን ይዘው ከዚያ በር ወጡ:: በአጠገቤ አልፈው ያንን ጭው ያለ ሰማይ መሰል ምድር ተያያዙት:: ከቆርቆሮአቸው ላይ የሚትንጋለለው ጭስ የሄዱበትን ለመጠቆም እየተጎረደ ምድር ላይ ይተከላል:: የጭስ ዱካ እያየሁ እሳቸውን መከተል እጀምራለሁ:: ጫፍ የሌለው መዳረሻ፣ ምልክት የለለው ጉዞ... ልቤ ይመታል፣ ይደቃል፣ ይጨፍራል..... ሲያመኝ እነቃለሁ::


t.me/OLDBOOKSPDF

"ወዴት ነው?"

"ወደ አዲስ አበባ"

"ምነው?"

"አክስቴ ጋ"

የእኔ ተቃራኒ:: አክስት አዲስ አበባ፣ እናት ሞጆ፣ አባት ጠፍቶ እናቷ...."

"አትሂጂ" አልኳት

"ከቤት ሄጃለሁ ብዬ ወጥቻለሁ"

"ጥሩ አጋጣሚ፤ ከኛ ጋር ታመሺና ከናፍቆት ጋር ታድሪያለሽ" አልኳት:: እግዚአብሔር ለሌለው ዓለም መድኅኒቱን የምናውቀው ጥቂቶች ነን:: እሸን፣ ምስጥ እና እኔ:: ቁራው "ቂ...ቅ" የሚለው በፍሊጋ ዕድሜውን ጨርሶ ነው:: እኛም ዕድሜያችንን ሳንጨርስ እንደምስጥ ኩይሳ እንገንባ::

"እ?"

"እሺ"

እሺ ያለችው እንደምስጥ ኩይሳ የመገንባታችንን ጉዳይ መሰለኝ:: እዚያ ኩይሳ ውስጥ ምን እናደርጋለን? መቼም ሳንጋባ፣ ተከሊል ሳናደርግ፣ ሳንቆርብ የሚሉት ጣጣ እዚያ የለም::

እንደ ቤቴ ቆጥሬው እንደሁ እንጃ ወደ ኒኮላ ወንዝ ይዣት ሄድኩ:: ምናልባት ኩይሳ ውስጥ ለመኖር ስለሚመች ይሆናል::

ቁሪማንቱሪ ስር ቁጭ አልን:: ግራ ገብቷታል:: ይለመዳል:: እግዚአብሔር ካበጃጀው ቦታ ይልቅ፣ ይሄኛው ያለዕዳ መኖርን ያስተምራል:: እዚህ ምን አብቅሎ ለየትኛው ውለታው እግዚአብሔር ይፈለጋል? ለዚህ ቦታ ከእግዚአብሔር ይልቅ ኒኮላ ባለውለታ አይደለምን?

እጇን ትከሻዋ ላይ ጣል አደረኩት:: ከዚህ በፊት አቅፌያት ዓለምን አልዞርኩም ዛሬ ምን እኮ ምን ተገኘ ይሄ ቦታ የእሸኖች፣ የእኔና የምሥጦች ራስ ገዝ አስተዳደር ነው:: አንዳንድ ሰርጎ ገብ ቁራዎች ቢኖሩም::



t.me/OLDBOOKSPDF

ያለምንም መንደርደሪያ ባቀፍኩበት እጄ ፊቷን ወደ እኔ መልሼ ከንፈሯ ላይ ሳምኳት:: ያልጠበቀችው ስለሆነ አይኗ እንደተገለጠ ቀርቷል:: ከንፈሯ ከንፈሬ ላይ አይንቀሳቀስም:: ምኗ ነው ያልተቀበለኝ? ምኗ ነው ያላስተናገደኝ ግን ዝም ብላኛለች:: እጆቿ ደረቴ ላይ ቢሆኑም አልገፋችኝም ከንፈር ሳይሆን የበትር ላይ ጉጥ የምስም መሰለኝ:: እኔ እራሴ ተውኳት::

"እንሂድ" አለችኝ::

"ወዴት?"

"እኔ አንጃ፣ ብቻ ከዚህ እንሂድ" ለእኔ ሳታፍርልኝ አትቀርም:: እሷ ምን አድርጋ ታፍራለች ታዲያ?

"ለምን ወደ አዲስ አበባ አትሄጂም?"

"እሺ" ብላ ግር እያላት ተነሳች::

"ቢቃ ሂጂ" አልኳት:: ደግሞ ፈጣሪው ጥሎት ለሄደ እጓለምውታን ዓለም ነው ሸር ጉዱ? መምህርት ሙናምኃ ብሄድ ይሄን ከማድረግ አልመለስም ነበር::

ሄደች የይጋርዱ ቁጥ ችግኙ እዚህ ተተክሏል:: ሲያፈራ ሌላ ይጋርዱ:: የይጋርዱ ምዕራፍ፣ የምዕራፍ ይጋርዱ.... ላብድ ነው? ወይስ አብጄ ጨርሻለሁ?

"እግዚአብሔር ይቺን ዓለም የተዋት ለሰው ልጅ እና ለዕብደቱ ነው::"

የዚህ ድፍረቴ ምላሽ የሚመስል ነገር ከጀርዬ ከፍ ያለ ቦታ ላይ፣ ምዕራፍ አበባ የሰካችበት ቦታ ላይ ከባድ ነገር አረፈብኝ:: ዓለም አጣጣረች:: ሞቷ ቀረበ:: በደብዛዛው ከፊቴ ተንፈራጦ የቆመ እግር ይታየኛል::

"ከጥርስ መንጋጋ፣ ካገር በሌጋ ከያዘ አይለቅም" አለኝ ያ - እግር:: እግር እንዴያ ይላል? አንጃ! ብቻ ደስ ብሎኛል:: ይኺ ዱላ አከስቴ ላይ ቢያርፍ ቀድሜ የምሞተው እኔ ነበርኩ:: አሁን የእራሴን ሞት እሞታለሁ - በቃ::



t.me/OLDBOOKSPDF

# 17

# ሌላው ንዳዶ

ሰማዩ-ሰማያት እንዲህ ቅርብ ነው? ከጀርባዬ እስከ እናቴ ፍልጥ የገባ መሰለኝል:: ከሞት ወደ ህይወት ተመልሶ የእከስቴን ሁኔታ ከማይ በዚያው መቅረቱን መረጥኩ:: ነፍሴን ይቆረቁራት ይሆን? ደግሞስ አከስቴ የእህቷ እጣ ፈንታ እንቆ ያዛት ማለት አይደል? ልትብሰከሰክ? ልትዋኸርቅ? እውነትና ውሸት ሊምታታባት? ሊዘባበቱባት? ልትሞት?......

ሞትን ታገልኩት:: ዓይን መግለጥ አዳጋች የሆነበት ራስ ምታት ፈለጠኝ:: ፍልጤ ገትሮ አስቀረኝ:: የት ነኝ?

"ቱሪስት፣ ቱሪስት...."

የተኛሁት ብዙ የድንጋይ ጉልቶች ላይ ነው:: ኮርማ ትዝ አለኝ:: እስከሬኔን አጋድመው የሚት ሸኝት ሲያደርጉልኝ ነበር? ቀለል አለኝ:: እንደምንም ዓይኔን ገለጥኩ:: ሰማይ በስንዝር ልኬት ቀርቧል:: በአሊጋው የሸቦ ሽንሽን ፍራሹ ብዙ ጡት መስሏል:: እንዳንዱ አጎጠጎጤ ነው::

"ቱሪስት ነቃህ?"

የገረመኝ ነገር በዚህ ሁኔታ ምን ያህል እንደቆየሁ አላወቅኩም እንጂ ስነቃ እስከምመታበት ድረስ ያለው ሁኔታ ወዲያው ታውሶኛል::

"ደርሶ መልሱ እንዴት ነው?" አለ ንዳዴ:: ፈገግ ለማለት ሞከርኩ:: ፍልጤ እንደተቆጣ ጡንቻ ውጥር ብሎ ፀጥ አለኝኝ::

"እናትንና በዚህ ይቀለዳል?" አለች ናፍቆት:: መኖሯ አስደሰተኝ:: የከብቶች ግርግም እንደተኛሁ የተሰማኝ ኮርማንና ሚስቱን ስመለከት ነው:: ቡግራም ላም የሚል ሃሳብ መጥቶብኝ በህመም ውስጥ እየዋኘሁ የሳቅ አየር ሳብኩ::


t.me/OLDBOOKSPDF

"እናትንና ይሰቃል እንዴ?" ብላ ደረቴ ላይ በኀንጪ ተኛች:: እያለቀሰች እንደሆን በእንቅጥቃጤዋ ገባኝ:: ከሁለቱ ኩቦዎች በተጨማሪ ቆቁ፣ ሚስቱ፣ ምዕራፍ አሉ:: የምዕራፍን አበባ ከቦታው አጣሁት:: ከወትሮው እረዝማለች። ከፍ ያለ ጫማ ማድረጓን አስታወስኩ። ሽቶዋስ? ድሮ የሆነ ቦታ አለ:: ድሮ- ድሮ ሸተተኝ::

"ቡቃ! ድኗል:: እንቃም" አለ ድሮ

እንደምንም እጄን አንስቼ ናፍቆት ጭንቅላት ላይ አሳረፍኩት:: ናፍቆት እንዲህ የሆነች አከስቴ?

"ለአከስቴ ነገራችኋት?" አልኩ እንደ ምንም

"ድምፅህ እኮ ካንተ ጋር አልሄደም:: እዚህ እስከናደርስህ ለአከስቴ አትንገሩ እያልክ ነበር"

"በለኝ በቃንክ!"

ንዳዴ ዛሬ ምን ሆኗል?

እንዴት እንደተገኘሁ ተረኩልኝ:: ለካ ምዕራፍ ወዲያው መለስ ብላ ኖሯል:: በረት ገልባጭ መፎከር ጀምሮ ነበር:: ምዕራፍ ጮኸች:: በረት ገልባጭ ወደ ኒኮላ ወንዝ ሸመጠጠ::

ምዕራፍ ለምን ተመልሳ መጣች? ምናልባት የሳምኳትን ለንዳዴ እንዳልነግርባት..... ያቺም መሳም ሆና? ጉጥ ከንፈር!

"እንደ ጣሊያን በፋከራ ቃጅበህ ነፍስህ ወጥታ ነበር" አለ ንዳዴ "የአድዋ ጦርነት ሲነገር በሰላቶ ላይ ስቀህ ነበር እንዴ?"

ናፍቆት ደረቴ ላይ እንዳለች ስትስቅ ታወቀኝ:: መሳቋ እንዳይታወቅ ውጣ ተነሳች::

"እናትንና ተወ!" ፊቷ ቀልቷል:: ዓይኖቿ ግልብጥብጥ ብለዋል:: አፍንጫዋን ይዛ ተናፈጠች::

"ጠቆር አድርጊው" አላት ንዳዴ

"ምኑን?"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ማኪያቶውን፤ የሻይ ማሽን መሰልሽኮ" ሁሉም ሳቁ

"በለኝ በታንክ!"

እኔም የጥቁር እንግዳዬን የፍልጤን ግሳዬ ችዬ ሳቅሁ:: ናፍቆት በጣም ተናደደች:: ከዚህ ዕለት ጀምሮ ሌላውን ንዳዬ አወቅኩት:: ሲቅም የሚጋገረው፣ ሲጠጣ የሚገነፍለው ብቻ ሳይሆን ከመቃም በፊት የሚሟወተው ሦስተኛው ንዳዬ....

ከምዕራፍ ጋር እንኳን ይቃለዳል:: ያደረገችውን ረጅም ሻማ አይቶ "ነገን ለማየት ነው?" አላት:: የኮርማ ግርግም ከመቃም በፊት እና ከመቃም በኋላ መለኪ ሁለት ነው::

ሜት ሲገዛ ድፎን ሲልኩት "ዝም አልከ?" አለኝ ንዳዬ

"ምን?"

"የቁም ተሰካር አስቅመና"

ናፍቆትን ወደ ኪሴ አመለከትኳት:: አወጣች:: በዓይኔ ሁሉንም ሰጪያቸው አይነት ጠቀስኳት። በጭንቅላቷ የጎረምሳ አምቢታ አሳይታ የተወሰነ ገንዘብ ወደ ኪሴ መለሰች::

"እኛም ከሞት ጋር ለዓይነ ሥጋ እስኪያበቃን ብር እንሰስታለን" አለ::

"ማን ሰሰተ?" ኮርማ ቀደም ቀደም ያለው የደበቀው ብር አለ ማለት ነው:: ሁሉም ሳቁ:: ቤቱን ሜት እስኪወስደው ድረስ ተሳቀ:: ከዚያ በኋላ እኔም አልፈለኩትም:: ወደ ቤት እንዲያደርሱኝ ጠየኩ::

* * *

ሶሚ እትንገሬ የተባለችውን ለአከሰቴ ነገረች:: እራሴን እንዳመመኝ ተነግሯት ነበር:: አከሰቴ ብርክ ይዟት ወደ ክፍሌ ገባች:: አልጋዬ ሥር ፍስስ አለች:: እየዳኸች መጥታ በሁለት እጇ አልጋዬን ተመርኩዛ አየችኝ:: መጠንከር ተሳነኝ:: ልነሳ ሞከሬ ፍልጤ ተገትሮ መለሰኝ::

ሶሚ መጥታ ልታነሳት ስትል "ተይኝ ልላበሰው" አለቻት:: መላበስ ምን ይሆን?



t.me/OLDBOOKSPDF

ተላበሰችኝ፡፡ "ጦስህ ለእኔ፣ ጦስህ ለእኔ......" ግንባሯን ከግንባሬ አጋጨች፡፡ መላ ሰውነቴን በሰውነቷ ዳሰሰች፡፡

"ጦስህ ለእኔ፣ ጦስህ ለእኔ......እኔን ድፋት፣ እኔን፣ እኔን........."

እንባዬ በዓይኔ ግራና ቀኝ መጋጠሚያ ወረደ፡፡ መነሳት አቃተኝ፡፡ ይኼን ፈርቼ መሞት ተመኝቼ አልነበር? ታዲያ?

ደጋግማ ተላበሰችኝ፡፡ ጦሴን ወደ እሷ፣ ህመሜም ወደ እሷ፣ ሞቴን ወደ እሷ...... እንዴት? የዋልኩበት ውላለች? የተሳሳትኩትን ተሳስታለች? የቱን በሽታ ከዩት እንዳመጣሁት በምን አውቃ?

"አይ አንተ አምላክ እኔ ቆሜ እሱን ልቀብር ማለት? ቀልድ ነው! ይልቅ እኔን! እኔን! ጦሱን ለእኔ! ጥንቡሳሱን ለእኔ.........አይ አንተ አምላክ አታደርገውማ......" አሁንም ተላበሰችኝ፡፡

መላበስ ምንድን ነው? በኋላ አወቅኩት፡፡ በሰው ዳሩ መግባት፣ ሞቱን መሞት፣ በሽታውን መውረስ፣ ራስን ለሰው አሳልፎ የመስጠት ርክክብ ነው፡፡ የትኛው ሞት ይኼን የአክስቴን ፍቅር አልፎ እኔ ጋ ሊደርስ?

ሦስት ቀን አልጋዬ ሥር ውላ አደረች፡፡ ሽቶዋ እየከሰመ፣ ልብሷ እየጠየመ፡፡

በአራተኛው ቀን የአክስቴን መውጣት በምን እንዳረጋገጡ ሳላውቅ እነ ንዳዴ መጡ፡፡ ናፍቆት፣ ምስራጭ ፣ ኮርማ፣ ቆቁና ሚስቶቻቸው፡፡

"እነ ናፍቆት ቤት ነው እንዴ የከረምከው?" አለ ንዳዴ ምን ለማለት እንደፈለገ አልገባኝ አለ፡፡

"እንዴት?"

"አ-ይ ከሳህ ብዬ ነው"

"በለኝ በቃንክ"

"እናትንና....."

ሳቁ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ድር ድር ሽተተኝ፡፡ መጣ፡፡ ብዙም ሳይቆይ፡-

"ቤቃ ተሽሎታል እንቃም!" አለ፡፡ የዓይኑ አረንጓዴነት ደብዝዞ ታየኝ፡፡ ምናልባት ሚስት መቃሚያ ሰዓት ስላለፈ ማስጠንቀቂያ ይሆናል፡፡

t.me/OLDBOOKSPDF

ላይ ፈጣሪ ይኼን ሁሉ ፈጥሮ ጥሎ መሄድ? ነው ወይስ እሱ ያልፈጠረውን በሐሰሳ ፍቅር አገኘነው? እኛ ገላ ከገላ ጋር ከማገናኘት ውጭ ምን ተአምር ፈጠርንና? ኒውተን ህዋ ላይ የወጣው ይኼ ጠፍቶት ነው?

"እናትንና..... እናትንና.......እናትንና......"

እኔ ያቃተኝ እሷ እንዴት ትቻለው? ምስጢረ ተፈጥሮ ባለ በሌለ ኃይሉ እኛ ላይ ወደቀ::

"ትወደኛለህ? ትወደኛለህ? ትወደኛለህ?"

"በጣም! በጣም!........"

ከላይዋ ላይ ገፍትራኝ እግሮቿን ነፃ ካደረገች በኋላ የውስጥ ሱሪዋን አወለቀች::

ጥቂት የቴከኒከ መቋረጥ አጋጥሞኝ ነበር:: ቀጠልኩት...... መልሳ እንበረችበት ስሜት ውስጥ ስትገባ......

"ቱሪስት ትወደኛለህ? ቱሪስት ትወደኛለህ?" አለች አፌን አፏ ላይ ደቅኗ:-

"በጣም!" አልኳት:: ምኗ ተቀበለኝ? ምኗ አስተናገደኝ?........... ኡፍፍፍፍ...........

"ታዲያ ለምን? ለምን?.........."

አታገባኝም ልትል መሰለኝ::

"እ?" አልኳት

"ምዕራፍን ሳምካት?"

ፈጣን የቴከኒከ መቋረጥ.......

ናፍቆት ለመቀበል እንደተዘጋጀች ሆና እንባዋ በዓይኖቿ መጋጠሚያ መውረድ ጀመረ:: ያ ሁሉ የደስታ ምንጭ የህመም ሳቢያ ሆነ::

"ሙ..ማን አወራልሽ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

"እራብ:: ለእኔም ለንዳዴም ነገረችን፣ ሁለታችንንም ይቅርታ ጠየቀችን::" ዛሬ መጥታ አለመጠየቋ ሌላ ምልክት ሆነኝ:: ዝም! ዝም! ዝም ያምማል? ምንም አለማለት ከበረት ገልባጭ ዱላ ይከብዳል?.......... ሌላ ፍልጥ::

"እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ጥሎት የሄደው ለህሊናው ትቶት አይደለም:: ለስሜቱ እንጂ::"



t.me/OLDBOOKSPDF

# 18

## ሥራይ

ብዙ የናፍቆት እንባዎች የቡጢ ያህል ከብደው ውስጤን ወገሩት፡፡ ልቤ ሐጢያተኛ ነውና ተወግሮ ይሙት ስል ፈረደረኩበት፡፡ ሱሪዋን እንኳ ሳትታጠቀው ከቤት ስትወጣ ውጪውን አለም አልፈራችም፡፡ ያን ቀን ማታ በህልሜ የሱሪዋን ጥርጊያ እንዳባቷ ሞተር ብስክሌት ጎማ ተወሳስቦ በሞጆ መንደሮች ሁሉ አየሁት፡፡ የእሷ ሳይሆን የእኔ ገመና ሆኖ በአሸዋ ከርታስ ላይ ተገፈ፡፡

ለወና ዓለም ሐጢያት ምኑ ነው? ገመናስ ፍቺ አለው? በሁለተኛው ቀን ከቤቴ ወጣሁ፡፡ የፀሐይ አብሪና አጥፊዋ ማነው? የጨለማስ አዛዡ ከወዴት ነው? ለኩይሳዎች ዋስትናቸው ምንድን ነው? አሸን ከከንፍ ጋር ቀጠሮ የሚይዘው ማንን ተማምኖ ነው? ነገን እንደጌኛ ጭኖ የሚያመጣው የጊዜ ሲራራ ከወዴት አለ? ይህች ዓለም ባለቤቷ ያቀለላት እሞሌ አይደለችምን? ታዲያ ስለምን እኛ ባለ ዕዳዎች እንቀበላታለን?..........

የናፍቆት እንባ ዶፍ ሆኖ ልቤ ላይ ዘነበ፡፡ በሱሪዋ ጥርጊያ ላይ ወደ ትምህርት ቤት አመራሁ፡፡ ትምህርት ከተጀመረ ቆይቷል፡፡ ምዕራፍ ብቻ የከፍሉን ግድግዳ በአንድ እግሯ ረግጣ ተደግፋዋለች፡፡

"ጉጥ ከንፈር! መሳሜ የበትር ዓይን መሳም እንደነበር ማን በነገራት?" ተመለስኩ፡፡ ዘበኛው ለ ሰዓት ስገባም ስወጣም ዝም ብሎ አየኝ፡፡ እንደ ናፍቆት ሱሪ ሁሉ የአክሰቴ እጅ ወደ የትም መሄጃዬን ያመቻቻል፡፡ የማንንም ልብ ያለዝብልኛል፡፡

"የየሺ ወርቅ ልጅ አይደለህ?"


t.me/OLDBOOKSPDF

ብስክሊት ነው ድውድውታውን የናኘው። መጡ። ገርመዎ አድርገውኝ አለፉ። የእሳቸውም እንድ እግራቸው እብጦ ሱሪያቸውን እስከ ጉልበታቸው ተርትረውታል። የሙናን ሁለት ዓይነት ጫማ አድርገዋል። የሙና አይጥና ሸለምጥማጥ።

ሊያመኝ ነው? ወይም አምሞኝ ጨርሷል? እነ ናፍቆት የሄዱበት አራት አቅጣጫ በየተራ ፊቴ ይደቀናል። እኔ ሳልዞር እሱ እየዞረ ይመጣል። አዲስ አበባ፣ ናዝሬት፣ አዋሳ፣ ምንጃር........

"ሰባኪው!.... እንዴ መከብብ......"ከአራቱ አቅጣጫዎች አንዱ የሙናን ድምፅ ወሰደ። በረት ገልባጭ ሲመታኝ ከው ብሎ የቀረው ደሜ ከጆሮ ግንዴ በላይ አድርጎ ወደ ቅንድቤ በመውጣት ነስር ሆኖ ወደ አፍንጫዬ ወረደ። ቅልል አለኝ። የተንሳፈፍኩ መሰለኝ።

ናፍቆት! ናፍቆት! ናፍቆት!



t.me/OLDBOOKSPDF

# 19

## ወደ ሲና ተራራ

"የት ነኝ?" አካባቢዬን አየሁ:: ስልምልም ብርሃን ይሰፍፋል:: እኔ ክፍል ውስጥ እንዳልሆንኩ አወቅኩ:: ጀርባዬ ሥር ጉልቶቹን ብፈልግ ስላጣሁ ግርግም እንዳልተኛሁ ገባኝ:: እጄን ስሰድ ከፍራሹ ቀጥሎ መሬት አገኘሁ:: አልጋ ላይ አይደለሁም በረት ገልባጭ ወደ ቡልጋ ወስዶ አግቶኝ ይሆን?

"ሰባኪው!" በር ተከፍቶ በብርሃን ጎርፍ እየተላጋች መጣች:: ተዳፋት ስላለው ይሆናል መዝጊያው በራሱ ጊዜ ቀስ እያለ ተዘጋ:: የብርሃን ደራሹ ግድብ ተበጀለት:: ሙና ድምጿን ልካ ቀርታለች:: ድምጿን ይዛ አጠገቤ የቆመችው ሌላ ሴት ናት:: አጭር ራንግለር ሱሪ ከረጅም ካናቴራ ጋር ያደረገች ሴት::

"የት ነኝ?" ስል ጠየቅኳት::

"እኔ ቤት" አለች እንግዳዋ ሴት

ቅዠት ውስጥ ነኝ:: አንዲት በውል ያላወቅኋት ሴት በሙና ድምፅ ታናግረኛለች::

"አንቺ ማነሽ?"

"ሙና፤ መምህርህ"

ፊቷ ላይ እንደመቃብር የተዘጋ መነፅር የሌላት ሙና አላውቅም፣ በልስን መነፅር ፈንታ ህይወት ባለው ዓይን የምታባብል መምህር አላውቅም፣ ከጉርድ ራንግለር ሱሪዋ ሥር ሁለት እይጦች ፈለኩ:: የሉም:: በእነርሱ ፈንታ የናፍቆትን የሚያማምሩ እግሮች አገኘሁ:: ምናቢ እውነቱን እየተገረረ እንደሆነ ገባኝ:: ላብድ ነው ወይስ አብጄ ጨርሻለሁ?

t.me/OLDBOOKSPDF

እግሯን ወደ ጎን ሽርመም አድርጋ አግርጌዬ ቁጭ አለች:: ላምን አልቻልኩም:: ሽበቱ ፀጉሯን ፈለኩ:: በእራፊ ጨርቅ ከግንባሯ ጀምሮ ወደ ኋላ ሽብ ተደርጓል:: እንደ እከስቴ ለማስረጃ ያህል እንኳን የፀጉር ዘለላ አልተወችም::

"እከስቴ ሰማች?"

"እንዳትሰማ እያልከ ብዙ ለፈለፍከ" ድምጿ የቢችኛዋ ሙና እንጂ የዛችኛዋ አልነበረም:: እውነታ ምንድን ነው? እንዴት ይቺን ሙና ብዬ ለመቀበል ዳዳሁ? የእውነትና የሐሰት የማስመሰልና የመሆን ድንበሩ የት ነው?

እግሬን እያሻሸች ልታወራኝ ሞከረች::

"አሁን እንዴት ነህ?"

"ደህና ነኝ፤ ግን ሙናን አትመስይም"

"ሙና እንዴት አይነት ናት?"

"የሚሰማኝን ልንገርሽ? ሁሌ የማስበውን?"

"እም"

"ጥቁር ጉም የማይለየው፣ የተራቆተና ህይወት የሌለው ትልቅ ተራራ እንደዛ ናት ሙና"

"የምትገርም ልጅ!" ህይወት ባለው ዓይኗ አየችኝ:: ሙቀት የሚለቅ:: በዛ ደባደቦ መነፅር እንዲህ ስንቴ አይታኝ ነበር ይሆን? ተቀባይ ጋ ያልደረሰ ውድ ስጦታ

"መወደድ ለመቀነስ ነው እንደዛ በሰው ቅርፅ የቆመ መቃብር መስለሺ..." ምን ነካኝ?

"የምትገርም ልጅ!"

"ምንድን ነው?" እግሬን ጨበጥ ጨበጥ እያደረገች ነርቬን ለማነቃቃት ትሞክራለች::

"የምደበቃቸው ሰዎች ስላሉ ነው"

t.me/OLDBOOKSPDF

"ለምን?" ላለመናገር ተቅለሰለሰች:: እኔ ቃላት፣ እሷ ቃናሽ የሆንን መሰለኝ:: "ለምን? መንገር ከሌለብሽ ተይው"

"አደጋ ያለበት ምስጢር ስለሆነ ነው::"

"አደጋ? ተይው......"

"ሳላምንህ ቀርቼ አይደለም፤ አንተ የምትገርም ልጅ ነህ"

"ተይው...." አኮረፍኩ?

"እየውልህ በፖለቲካ ቁርሾ ለመበቀል ይሁን ለሌላ ብቻ የሚፈልጉኝ ሰዎች እንዳሉ ይሰማኛል:: በፊት ወጣት እያለሁ የመንግስት ተቃዋሚ ነበርኩ::"

ወጣት ሳለሁ? አሁንስ? ፊቷን አየሁት:: መስመር የለሽ ልሙጥ ነው:: አይኖቿ ህይወት የሚረጩ ትኩሶች ናቸው::

"አሁን የምፈልገው በዘመኔ የነበረውን የወጣቶች መንፈስ እዚህ ትውልድ ላይ ማምጣት ብቻ ነው:: ሃላፊነት ይሰማኛል ይገባሃል?"

እራሴን ወዘወዝኩላት ያቋረጠችውን እግሬን ማሸት ቀጠለች::

"የፖለቲካ ብቻ አይደለም:: በሳይንስ፣ በስነ-ፅሑፍ፣ በኪነጥበብ...... በሁሉም:: ብቻ ጠንካራ ትውልድ! እኛ ልናመጣ ስናልም ከነበረው በላይ አገሪቱን የሚጠቅማት የእኛ መኖር ነበር:: አጣችን:: የልጅ ድሃ አደረግናት:: ከምንም በላይ የሚታየውን የሰው ኃይል ነፈግናት::"

ዓይኔን ጨፍኜ አዳመጥኳት። እራሷ ናት፤ ሙና ናት....

"የአንተ ዓይነት ብዙ ልጆች አሉኝ:: የወለድኳቸው ሳይሆኑ መስመር ያስያዝኳቸው:: የተለያየ ቦታ እየዞርኩ ይሄን ሳደርግ ነው የቆየሁት:: አንድ ቀን ሺ አፍርታችሁ እንደማያችሁ ተስፋ አለኝ::"

አይኖቿ እንባ አቅርረው ሳይሆን አይቀርም:: ያለውን ድንግዝግዝ ብርሃን አጠራቅመው መርጨት ጀመሩ::

"ስለ እግዚአብሔር ምን እንደምታስብ ንገረኝ" አለችኝ:: ድምጿ ውስጥ ሲምምጥ አለ:: የአክስቴን የመሰለ ከማፍቀር ብቻ የሚመነጭ::

"ንገሪኝ"


t.me/OLDBOOKSPDF

"እግዚአብሔር ኒኮላ ነው::"

"ኒኮላ ማነው?"

"የወፈወፎው ባቡር የነበረው ጣሊያናዊ"

"እ......ሽ?"

"ዓለም እንደ ኒኮላ እህል መፍጫ ባቡር ዝገትና ትቢያ ውጧት ቀርታለች:: ፈጣሪዋንና ጠጋኟን ብትቃበዝም ኒኮላ እንዱ መንገድ ጥግ በገብ ተዳክሞ እንደተደገፈ ቀርቷል:: አወዳደቁ ሁሉ ይታየኛል:: አንድ እግሩን እጥፎ ለላውን ዘርግቷል:: እኛ ሰዎች ያለ አፈጣጠራችን እህል መፍጫ ባቡር ውስጥ በየቀዳዳው ተሰግስገናል:: ኩይሳ ማበጀት ያቃተን ምስጦች ሆነናል:: የኒኮላ መገኘትና የባቡሩ መነሳት ዝገትንና ዳዋን ተገን ላደረግን ለእኛ ለምስጦቹ ትልቅ ጥፋት ነው::"

ምን አልኩ? እንጃ! አእምሮየ ሴት ተቀን ከሚለፈልፋቸው አንዱን ነገርኳት::

"ጥሩ" አለችኝ:: "እግዚአብሔርህ አንተ ፈልገህ ካላገኘኸው አይገኝም፤ አንተ ፈልገህ ካላጣኸው አይታጣም::"

ዝም ብዬ አየኋት:: ህይወት የበዛለት ዓይኗ ከበበኝ:: እዚያ ውስጥ እንደ አከስቴ ሽቶ ዋንሁ::

"ትምህርት ቤት ሲዘጋ ትፈልገዋለህ፤ አብረን እንፈልገዋለን:: ወይ እናገኘዋለን፣ ወይ እናጣዋለን:: ይሄ ለውጥ አያመጣም::"

አለመገኘቱና አለመታጣቱ ነው ጉዱ አልኩ:: እግሬን ለቅቃ እንደ አከስቴ መላበስ ሰቅስቃ አንገቴን አቀፈች:: ውሃ-ውሃ ሸተተችኝ:: ሙና ናት::

በሚቀጥለው ሳምንት እግዚአብሔር ወደሚገኝበት ወደ ሲና ተራራ እንሄዳለን:: ሙና ሙሴዬ ናት:: እኔ እግዚአብሔሬ እስኪገኝ የምታስከትለኝ ህዝቧ ነኝ::



t.me/OLDBOOKSPDF

# 20

## ህማማት

አለምርዬ እያርፍም፤ ሲሰራ ያድርና ሲነጋ ግሎ አገኘዋለሁ:: ሠላማዊ እንቅልፍ ከተነፈግኩ ቆየሁ:: አንድ አዲስ ቅዠት ደግሞ ደጋግሞ ይጎበኘኝ ይዟል:: ረጅም አውቶብስ ነው:: ሰዎች ተጠቅጥቀዋል:: ወደ ኋላ የምነዳ ይመስለኛል:: ያለፍኩት መንገድ ብቻ ከፊት ለፊቴ እየበረረ ይሸሸኛል:: ብዙ ኩርባዎች ሳይታዩኝ እንዴት ታጠፍኳቸው? ይሄን ሁሉ ሰው ይገዥ ገደል ልገባ? ጋሽ ጥበቡ ከቆሙት መካከል ሆነው ይገረምሙኛል:: በአንድ እጃቸው የአውቶብሱን አግዳሚ ይዘዋል:: በሌላ እጃቸው ፍም ያለው ቀለም ቆርቆሮ :: የጦጤ እናት እልጋቸው ላይ እንደነበሩ ሆነው አጠገቤ ተቀምጠዋል:: እዚህ አውቶብስ ውስጥ እናቴ እንዳትኖር እጨነቃለሁ:: ነገር ግን ፍሬን ለመያዝ ሳይሆን አስተካክዬ የማላየውን ኩርባ ለማለፍ እጨነቃለሁ::

"አትጨነቅ አውቶብሱ ነፍስ ያውቃል::" ጋሽ ጥበቡ ይህን ያሉኝ ይመስለኛል::

"እንደ ፈረስ? ታዲያ ፈረስም በጋላቢው ስህተት ገደል ይገባል'ኮ" እላለሁ:: እጨነቃለሁ::

በዚህ መካከል ጭንቅላቴ እንደ እንስራ በኩርኩም ይንኳኳል:: ከቅዠት ውስጥ ተመንጭቼ ስወጣ መንኳኳቱ ቀጥሏል:: የሚንኳኳው ግን ጭንቅላቴ ሳይሆን ደጃፌ ነው:: ለሰስ ያለው ማንኳኳት አንዳች ነገር አስታወሰኝ::

ናፍቆት! ናፍቆት! ናፍቆት!

ወደ በሩ ተጠግቼ መከፈት ፈራሁ:: ቅዠቴ ነፍስ ዘርቶ የመጣ መሰለኝ::


t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዲያ ከሆነ ደግ" በፍጥነት አወላልቃ አውስጥ ገባች:: እኔ ከብርድ ልብሱ በላይ ተንጋልዬ ከንዴን እንተራስኳት::

"በሌሊት ተነስቼ አውቶብስ ተራ ላሉት ደግሞ እሰጣለሁ:: የሄደበትን ሳያውቁ አይቀሩ ይልኩብኃል:: መስጠት ጀምሬለትን ሲሰማ ይመጣል::"

ወይ ጉድ! ይሄን እያየ ዝም የሚል አምላክ እንዴት ያለ ነው? እውነትም የለም:: ሸሽቷል፣ ፈጥሮ ጠፍቷል:: መተኪያ ሳያበጅ ለውጥንቅጥነት ዳርጎን ኮብልሏል::

እንቅልፍ ወሰደኝ:: ስነቃ መብራቱ ጠፍቷል:: ምዕራፍ አጠገቤ የለችም:: ወደ አውቶብስ ተራ ሄዳለች ማለት ነው:: ዘገነነኝ:: ተከትሎም በኮርማ ላይ ብስጭት ያዘኝ:: ንዴት እየጋለበኝ ወደ ኮልባ ሠፈር ሄድኩ::

የበረሃ ውርጭ የኮልባ ሰፈርን አኮማትሯታል:: አሸዋው እርጥበት ጠግቦ ሲረግጡት ድምፅ አያወጣም:: ጫማ ላይ ይፈረፈራል:: የኮርማ ግርግም ከውስጥ እንደተሸጎረች ነው:: አንኳኳሁ:: ደገምኩ::

በሩ ተከፈተ:: ያለ ንግግር ቴስታና ቦክስ ላከታትል ስዘጋጅ ኮርማ ሳይሆን ቆቁ ብቅ አለ::

"ቱሪስት ምነው?" አለኝ አይኑን እያሻሸ

"ኮርማን ፈልጌ" አልኩ

"በደህና?" ብልግብልጥ ፊቱ ገና አልነቃም::

"በደህና ነው::" ቁና ቁና ተነፈስኩ::

"ኮርማኮ ከታሰረ ዛሬ አራት ቀኑ" ደነዘዝኩ::

"ምዕራፍ አልመጣችም?"

"እዚህ አልመጣችም፣ ግባ" ብሩን ለቀቀልኝ::

"አልገባም" አልኩት "አልገባም እሄዳለሁ"

"ይገርማል፣ የኮርማ ነገር ይገርማል:: ደስታውን ከእኛ ጋር ያሳልፋል:: ደስታው የሚያመጣውን መከራ ግን ዘውትር ብቻውን ይወጣል:: እስኪ አንተ እርዳው:: አከስትህን ከለመንካት ታስፈታዋለች::"



t.me/OLDBOOKSPDF

መልስ ሳልሰጠው ፊቴን መለስኩ:: ምዕራፍ ለምን ዋሸች? ነው ወይስ እንደ እናቴ ህሊናዋን ሳተች:: እውነቷ በምኞቷ ተገስስ ይሆን?

ወደ አውቶብስ ተራ በግስጋሴ ሄድኩ:: የለችም:: እራሴን አረጋግቼ ወደ ቤት ተመለስኩ:: ሎሚ ያቀረበችልኝ ቁርስ ለላከፌ ደብተሬን ያዝኩና ወጣሁ:: የመማር ፍላጎት የለኝም:: ቀጥታ ወደ ፊዚክስ ቤተ ሙከራ ሄድኩ::

ሙና የድሮዋን ሆና ጠረጴዛው ላይ ተቀምጣለች:: አንድ እግሯ ተንጠልጥሎ አይጧ ይታያል:: እኔን ስታይ እንደ መሽቆጥቆጥ ብላ መጣች:: ያቺን ሙና ይቺ ናት ብሎ ማመን ይከብዳል:: ከንፈሯቸውና ድምፃቸው ብቻ ነው የጋራ:: ማታ የሆነውን ነገርኳት::

ይሄ ነው የምትለው ነገር አልነበራትም:: ዝም ብላ እንደናፈቀ ሁሉ ታየኛለች:: ያ ሙቀት የሚለቅ ህይወት ያለው ዓይኗ ይሄኔ........ .

"ዝም አልሽ"

"ምን ልበል?" ታናሺ ሆነች?

"የሆነ ነገር በይ እንጂ"

"የእግዚአብሔርህ ነገር ከፍ ወዳለ ደረጃ ተሸጋግሯል ማለት ነው::"

"ዋሸሁ? ቃዠሁ? አንቺ ጋ መምጣቴ ውሸት ነው? ቅዠት ነው? እግሬን ማሻሸትሽ ህልም ነበር? ማቀፍሽስ?......"

"ረጋ በል:: እሱ ሁሉ እውነት ነው::"

"እና?........."

"ይሄኛው ግን ውሸት ነው"

"በምን አወቅሽ?"

"ያልካትን ልጅ ቀስ በልና በግራ መስኮት በኩል እያት:: ቀስ በል፣ እንዳልካት አይደለችም::"

እንደተባልኩት ቀስ ብዬ ሳይሆን በድርቅና የተጠቆምኩትን መስኮት አየሁ:: ምዕራፍ ስትንጧኩክ ያዝኳት:: እራሷን አልጣለችም:: እንቅልፍ አጥታ እንዳላደረች ያስታውቃል:: እግሯን አይቼ ለማረጋገጥ በፍጥነት ቤተ ሙከራውን ትቼ ወጣሁ::


t.me/OLDBOOKSPDF

“ጠዶሽ? ወዴት?” የመና ድምፅ ተከለኝ፡፡ ወደ ዳሮ፤ ምስራቁ ምንም እንዳልተፈጠረ ግድግዳውን በአንድ እግሯ አረግጣ በጀርባዋ ተደግፋለች፡፡ እግሮቿ የሁለት ሳይሆን የአንድ ሰው ናቸው፡፡ አላመንኩም፡፡ ተጠግቼ፡-

“ሊሊት እዚጋ መጥተሽ ነበር?” አልኳት፡፡

“ምን ላድርግ?”

ቢቃኝ፡፡ ፊቷን መልሼ ከእሷ ለመራቅ ሰጠጋፍ “እንዴት በቀህ መጥተውልህ......” በሚል ሸንቆጠኝ፡፡ ማበዴ ነው? ወይስ አብጄ ጨርሻለሁ?

መና መጥታ በእይጠቿ አጠገቤ እየተራመደች፡፡ “ተዘጋጅ፡ ዛሬ ፊቃድ ወሰጄ ነገ እንሄዳለን፡፡” አለችኝ፡፡

“እንቺስ ቅገርቴ ብትሆኚ?” አልኳት

“ልጅ አትሁን”

“የት ነው የምንሄደው? እግዚአብሔሬን ፍለጋ? ወደ ሲና በረሃ ነው? ወይስ ወደ ሰማየ ሰማያት? እሱ ጠፍቷል፡፡ እሱን በመፈለግ እራስ መጥፋት እንጂ ሌላ ነገር አይገኝም፡፡”

“እራስ መጥፋትም መዳን ነው”



t.me/OLDBOOKSPDF

# 21

## አዲስ ዘፀአት

ወደ እግዚአብሔር እምባ የሚወስድ ሊሞንቺና ውስጥ ገባን፡፡ "አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ!" ይላል ረዳቱ፡፡ ሙና መንፅሯን አላደረገችም፡፡ አይኖቿ የህይወት ባህር ውስጥ ይዋኛሉ፡፡ ስስ የአንገት ልብስ ነጥላ ከራሷ ጀምሮ ተከናንባለች፡፡ በደባደቦ ቀሚሷ ፈንታ የጨርቅ ሱሪ አጥልቃለች፡፡ የእጅ ቦርሳዋን ጭኗ ላይ አስቀምጣለች፡፡ መነጋገር እንዳልፈለገች ያስታውቃል፡፡ በመስኮቱ ወደ ውጭ ትመለከታለች፡፡ በእሷ ላይ አሸማሬ አያለሁ፡፡

አዲስ አበባ በብርድ ልምጭ ተቀበለችን፡፡ መወለድ ለአዲስ አበባ ቋንቋ ብቻ ሆነ፡፡ ወሌዳ ተነጠቀች፡፡ ልጇን አጣች፡፡ በዩጎኛነት አሳድጋ ቆለኛ ሆኖ መጣ፡፡ እቅፏ የግርፊያ ያህል ሸነቆጠው፡፡

ለገሃር ወርደን በእግራችን ወደላይ ስንወጣ ሁሉ ሙና ዝም እንዳለች ነበር፡፡ አንድ ትልቅ ህንፃ ጋ ስንደርስ ሙና ጠብቀኝ ብላ ገባች፡፡ እላዩ ላይ ፅሑፍ ፈለግኩ፡፡ የለም፡፡ ትንሽ ከፍ ብዬ በጎን በኩል ስመለከት "የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር" የሚል ፅሑፍ አገኘሁ፡፡ እግዚአብሔር ቴአትር ቤት ምን ያደርጋል? ሳንሰለጥን እንተውንለት የለ? ያለ ቴአትር ረቂቅ እንስቅና እናለቅስ የለም?..... የምንቅላቱ አንድ ጎን እንደ ጦጢ እናት እግር ለብቻው ያበጠ መሰለኝ፡፡

ሙና ከህንፃው ወጥታ እየፈለገችኝ ነበር፡፡ ታየኋት፡፡ እጇን ከመዳፈ በላይ ለቀም አድርጋ ይዛኝ ገባች፡፡ ህንፃው በረጃጅም መጋረጃዎች የታጠሩ ሰፋፊ በረንዳዎች አሉት፡፡ ጨለምለም ባለ ኮሪደር በኩል አልፈን ሥራ አስኪያጅ ቢሮ ተብሎ የተፃፈበት ክፍል ገባን፡፡

"ኒኮሌል ሥዕሉ ላይ እንዳለ ሆኖ ሲጣንን እንደተረገጠ፣ ከእግዚአብሔር መቀመጫ በሉተቶኝ የቆመበት የቢሮ አደረጃጀት ጠብቄ ነበር፡፡ የሁሉቱም ከንፍ



t.me/OLDBOOKSPDF

"የት ነው ያለነው?" አልኳት የእኔን ሙሴ መንገድ ስታ አርባ ዓመት ሙሉ ኳኳታ፣ ብርቅርቅታ፣ከውከውታ ውስጥ ስንዞር እንዳንኖር ሰግቼ::

"ፒያሳ" አለችኝ::

"የት ነው የምንሄደው?"

"እናንተ ሰፈር"

"ግንፍሌ?"

"አዎ"

ሙና የእኔን እግዚአብሔር ከቆጥ አወርድ ብላ የራሷን እግዚአብሔር የማለች መስሎ ተሰማኝ:: ለምን? አልጠየቅኋትም:: ዝም ብለን ሾላ መገናኛ የሚል ታክሲ ውስጥ ገባን:: ከአባቴ ጋር ሲኒማ ልንገባ የምንመጣው እዚህ ነበር:: እረንቻታ የሚገዛልኝ እዚህ ነበር:: ትክክለኛው ቦታ ግን ጠፍቶብኛል:: እንደ ሙና ሁሉ ፒያሳም ሁለት መልክ ሳይኖረው አይቀርም፣ የሚያታልልበት:: አራት ኪሎ ሀውልት ጋ ስንደርስ የት እንዳለን ገባኝ:: ግንፍሌ ድልድይ ጠራኝ:: የድልድዩ ሥር ቢራቢሮዎች ክንፎቻቸውን ወደ ሰማይ ቀስረው ያንቀላፉ ይሆናል:: ወይም ቀን እጥሮባቸው ሲነጫጩ ጎረቤቶቻቸውና የስጋ ዘመቻቸው የሆኑትን አባ ጨጓሬዎች ተርተውባቸው ይሆናል::

"እናቱ የምተችበትም ገበያ የሄደችበትም እኩል ያለቅሳሉ" ብለው

ሠፈሬ ጠራኝ:: የአየር ሁኔታው ገፈተረኝ:: ግንፍሌ የሚሸነቁጠውን ብርድ ከማን ተዋሰች:: እንደ ግንፍሌ እናቶች ሁሉ ሠፈሮችም እትዬ አንትና እስኪ አለናጋዎትን፣ ልጁ ሊያሳብደኝ ነው:: ሊያሳብደኝ ነው እየተባባሉ የአየር ሁኔታ ይዋዋሱ ይሆን?

ሙና በፀጥታ ትከተለኛለች:: የእኔን ልጅነት ፍለጋ ይሆን እዚህ ያመጣችኝ? እኔን ሲጫወት ወይም በመወዘቻ ውሃ ይዞ ከጋንጩር ጋር ሲያወሩ ብናገኘውስ? ወይም አባቴ ዘንቢል ይዞ ከእናቴ ኋላ ኋላ እየተከተለ ሲያገለግላት ብናገኘውስ? ጋሙዳ "ወጋሁ" ቢለኝስ? እማማ ይጋርዱ ቂጦ "የቢላዋና የወንድ ትንሽ የለውም የሰባ ይወዳሉ" ቢሉኝስ?......



t.me/OLDBOOKSPDF

ታች ሠፈር ደረስን:: ጣሪያቸው የሚያብረቀርቅ ጥቂት አዳዲስ ቤቶች ታክለዋል:: በፊት ሰፊ ይመስለኝ የነበረው ሜዳ አነሰብኝ:: የውሃ ጉድጓዱ ግምብ የጥንት ተረት ስዕል መስሎ ተገትሯል:: ስራ ካቆመ በመቆየቱ ጉድጓዱ በቆርቆሮ ታሽጓል::

ላይ ሠፈር የተለወጠ የለም። የእኛና የእነ ጋንጩር ቤቶች ስለ ጥንት የሚያወሩ አዛውንቶች መስለው የእስተርጅና ዘመን ግልጋሎት ይሰጣሉ:: የእነ ጋንጩር ቤት ዛሬም በደረቅ ቅጠል ሽምጥ እንደታጠረ ነው:: ዘወር እስከንልና እስካረጋግጥ አባቴ አንድ እግሩን ዘርግቶ ደረቅ አጥር ተደግፎ የማገኘው መሰለኝ::

"ይህ የእኛ ቤት ነበር" አልኳት

ዝም ብላ በትካዜ አየችው::

"በሩ ላይ ያለችው ጠፍጣፋ ድንጋይ ትታይሻለች? እሷ ላይ ሆኜ ነበር አግሬን የምታጠበው::"

"እስቲ ቁጭ በል:: ድንጋዩ ላይ........እንደ እሱ...... አግርህን ስትታጠብ ምን ይሰማህ ነበር?" ስትል ጠየቀችኝ::

"ፍርሃት"

"የምን ፍርሃት?"

"የሴጣን፣ ቅጠሉ እንዲህ ሲንኮሻኮሽ......"

"የመጨረሻ ቀን እዚህ ነበርክ? አባትህ ሲጠፋ?"

"አዎ" ልቤ መታ

"እሱ ከየት መጥቶ በየት ሄደ?"

"ከቤት ወጥቶ በሜዳ አቋርጦ ሄደ"

"እንዴት? እስኪ ተከተለው...."

"እንደዚህ ዞርም አላለም:: በዚህ በኩል፣..... ጫማውን እየጎተተ፣ አካሉን እየጎተተ .... እንዲህ በዚህ ...."

"የሚሄድ በሚመስልህ በኩል ተከተለው" ከኋላ ድምጿ አጅቦኛል:: ጥርት ብሎ የሚታይ ነገር የለም:: በፊት የሜዳውን ጎድባ ሁሉ አውቀው ነበር:: ዛሬ



t.me/OLDBOOKSPDF

ጥቂት እንደተጓዝኩ ሰዎች ተሰብስበው አየሁ፡፡ ጠጋ አልኩ፡፡ የሚያዩት እኔ የሄድኩበትን አረህ አቆልቁለው ነው፡፡ ወደሚመለከቱት ተመለከትኩ፡፡ ሌሎች ጥቂት ሰዎች ከማጡ ውስጥ ሰው ለማውጣት ይጥራሉ፡፡ ተጎርጹ የቀረ "እኔ" ይሆን? አፋፉ ላይ ወሬ ለማየት የተሰባሰቡት እኔን ሲያዩ በመገረም መንገድ ለቀቁልኝ፡፡ አልተጠራጠርኩም እሷ ናት፡፡ ከህመም ጋር ወረድኩ፡፡ ሙና የእኔን ግማሽ ተጉዛ በመድከም በአረንቋ ተይዛለች፡፡ እኔን ስታይ ከጭቃ ፊቷ መሃል ጥርሶቿ ብቅ አሉ፡፡

"የእኔን አምላክ ፍለጋ ስለምን እርሷ ዳከረች?" ስል አሰብኩ፡፡ አንድ አዛውንት "ፈልጉልኝ ያልሽን እሱን ነው?" ሲሉ ጠየቋት፡፡ የጭቃ ኳስ የመሰለ ጭንቅላቷን በአዎንታ ነቀነቀች፡፡ ሁለታችንንም ይዘው አቅራቢያው ወደሚገኝ መንደር ወሰዱን፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF

# 22

## ሌላው ዘፀአት

"ማንኛውም ሰው ቢያንስ በህይወቱ አንዴ ሀገሩ እና ባህሉ እጅ ላይ ይወድቃል" አለች መና ግዴ ማዶውን እያየች::

"እንዴት?" የብዕር ጭረት የሚመስሉ ቀጫጭን ቡጭሪያዎችን ፊቷ ላይ እያለሁ:: ሊጠልቅ የሚስለመለመው ጀምበር ቁስሏን ጌጥ አስመስሎታል::

"ሃደ ወርቂቱ እኛን ተቀብላ እንድታስተናግደን ያስገደዳት ምን ይመስልሃል?" ህይወት የሚቸር ዓይኗ ዳሰሰችኝ::

የነጠር አባ ወራ እና እማ ወራ መስለን አንዲት ጎጆ በር ላይ ቁጭ ብለናል:: የአባ ወራውን ብልኮ አጣፍቻለሁ:: እሷ የእማወራዋን የአንገት ልብስ ደርባለች::

"የግለሰብን ውለታ ለመንጠቅ ይመስላል" አልኳት::

"የትኛውም ግለሰብ የባህልና የሀገር ግንዛቤ ስሪት አይመስልህም?"

በዝምታ ጣዕረ ሞት ወደ ተናነቃት ጀምበር አተኮርኩ:: ከሀገርና ከባህል ግንዛቤ ባሻገር የህይማኖትና የስጋ ዝምድና ተፅዕኖስ? አከስቴ ትዝ አለችኝ:: አዲስ አበባ ደርሼ በሁለት ቀን ውስጥ እንደምመለስ አሳምኛት ነበር የመጣሁት:: ሌላ ሁለት ቀን ሳልጨምር አልቀርም:: እንዴት ትሆን ይሆን? ለመጀመሪያ ጊዜ ካሰሁበት ሁኔታና ቦታ ውጪ አሰቢ ስጨነቅ ይኼ የመጀመሪያዬ አይደለም? ለካ ሞጂ ሆኜ ስለ ንፁህ አሰብ ነበር:: ንፁህ ምን ሁኔታና ደረጃ ላይ ትገኝ ይሆን?

"እናንተ ዱርየዎች"

"እናያችሁንና!"

ናፍቆትና ንፁህ ሳቢና ተሳቢ ሆነው እኔ ህይወት ውስጥ ይቀጥላሉ ማለት ነው?


t.me/OLDBOOKSPDF

"እንዴት ነው ሁኔታህ?" ሙና ጠየቀችኝ

"ደህና ነኝ" ድምጿ እንደ ዋሽንት ለማስደሰት ሆን ተብሎ የተፈጠረ ይመስላል::

"ጥያቄዎችህ ተመለሱ?"

"ጥያቄዎች ብቻ ሳይሆን ሽክምና እዳየም በከፊል ተቃሏል"

"በከፊል?"

"አ"

"የሰው ልጅ አሁን ባለው አቅም የሚቻለው እስከ ጨረቃ መምጠት ብቻ ነው። ከዚህ በኋላ አምላክ ሊኖርም ላይኖርም ይችላል:: በከፊል ያልከው እዚህ ውስጥ መጢቃለል ይገባው ይመስለኛል"

ዝም ብዬ ወደ ማድመጡ አዘነበልኩ:: የቤቱ እመቤት ሃደ ወርቂቱ ትገባለች ትወጣለች::

"የእኔን ልምድ ልንገርህ" ወደ ትዝታ ልትገባ እንዳይሆን የፊቷ ፀዳል ይናገራል:: እንዴት? እንጃ!

"በፖለቲካ ሩጫ መካከል የማስተናግደው ፍቅር ይዞኝ ነበር:: ለነገሩ በወቅቱ ፍቅር እንደያዘኝ አላውቅም ነበር:: ብቻ የሚናገረው፣ የሚያደርገው፣ የሚሆነው ሁሉ ለእኔ አርአያነት ያለው፣ በእርሱ ፊት ሁሌም እራሴ እንስ የሚታየኝ ወጣት ነበር:: ከባድ የድርጅት ተልዕኮዎችን አቅልሎ በማየት ያከናውናል:: ከባድ አስተሳሰቦች አቅልሎ ያብራራል:: ከባድ ኃላፊነቶችን ሳይጨነቅባቸው በቀላል መንገድ ይወጣቸዋል:: ስታወራው፣ ስታየው... የሚጨነቅበትና የሚከብደው ነገር ሳይኖር የሚኖር ወጣት እንደሆነ ትረዳለህ። ስለድርጅት ስጠይቀው "ተፈጥሮዬ ውስጥ አለ" ይላል::

"ስለ ኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች ወገንተኝነት ስጠይቀው 'ተፈጥሮዬ ውስጥ አለ:: እናት ልጇን ማፍቀሯን ከየት ታመጣዋለች? ለልጇ መሞት እንዳለባት ማን ሊነግራት ይገባል? ሁሉም ተፈጥሮ ውስጥ አለ:: አንቺም ተፈጥሮሽ ውስጥ መፈለግ ነው ያለብሽ።' ይለኛል:: እኔስ እሱን እንዳፈቅር ማን ነገረኝ? ተፈጥሮዬ ውስጥ አለ?"



t.me/OLDBOOKSPDF

ከእንግዲህ ከንፈሯና ከዚያ ይወጡ የነበሩ ቃላቶቿ የመልኬ አንዱ ገፅታ ሆነው ግንባሬ ላይ እንደሚኖሩ ገባኝ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF

# ድህረ ታሪክ

እኔ ይሄን መፅሐፍ መግታት የፈለኩት አሁን ያቆምኩበት ቦታ ላይ ነበር:: ይሁንና ታሪኩን በጨዋታ ሰምተው የነበሩ አንዳንድ ወዳጆቼ የዚህን መፅሐፍ ረቂቅ ሲያነቡ ብዙ የቀሩ ነገሮች እንዳሉ ይጠቁሙኝ ጀመር:: እነዚህ በወዳጆቼ ቀሩ የተባሉ ነገሮች የአተራረክ ዝንፈት የሚያስከትሉ፣ የትረካው ዘርፍ ሆነው ለመዘምዘም የሚያዳግቱና የተቋጨን ታሪክ የሚተረትሩ ቢሆኑብኝ በድህረ ታሪክ ተጠቃለው እንዲቀርቡ ለመወሰን ተገደድኩ::

ትረካውን ካቆምኩ በኋላ ግንፍሌ የቆየሁት ሦስት ቀን ያህል ብቻ ነበር:: በዚች አነስተኛ ቀን ጋንጩርን አግኝቼዋለሁ:: ትምህርቱን አቋርጦ የአብዮታዊ ፖሊስ አባል ሆኗል:: "ብሔራዊ ውትድርና እንዳይወስዱኝ ነበር:: ግን መዝመት የቀረልኝ አይመስለኝም" አለኝ::

"እንዴት?" አልኩት

"የአብዮታዊ ፖሊስ አባላትም ወደ ሰሜን እንዲዘምቱ ተወስኗል ይባላል" አለኝ::

የሐዘን ድባብ ያጠላበት ጨዋታችንን ለመሸሽ "አሁንም ድንጋይ ትወረውራለህ?" ስል ጠየቅኩት::

"የት ይቀራል" አለኝ::

"አትለኝም?"

"አንዳንድ ቀማኞች ሲሮጡ የምደርስባቸው ካልመሰለኝ አንድ ሦስቱ ፈንከቻቸው ያመልጣሉ::"

ሁለታችንም ከልብ ሳቅን::

እህቱ ማናሉ እኔ ከግንፍሌ እንደወጣሁ ሰሞን ጠፍታለች:: እስካሁን የት እንዳለች እንደማይታወቅ ጋንጩር አጫወተኝ:: ጋሙዳ አባቱ ጦር ሜዳ ስለሞቱ


t.me/OLDBOOKSPDF

ወደ አብዮታዊት ኩባ ተወሰዷል:: ይሄን ስሰማ የጋሙዳ "ወጋሁ!" ጨዋታ አለም አቀፍ ይዘት እንደሚኖራት አሰቤ ሳቅሁ:: ይሄኔ ኩባዎቹን "ወጋሁ!" ጨዋታ አስለምዷቸው ይሆናል::

አሰፋ ጢሪሪ፣ ቤንጢ፣ ሙቄና ቀጮ ደህንነታቸውን ብሰማም አላገኘኋቸውም:: በመጨረሻ ስፈራ ስቸር ስለ ንፁህ እነሳሁበት:: አባቷ ሞተው እናቷ መጥፋታቸውን ነገረኝ:: "ከፍተኛ ሐ!!ን ውስጥ ያለች መሰለኝ" አለኝ::[2]

የማግኘት ጉጉት ተቀሰቀሰብኝ::

"የጠዋት ተማሪ ስለሆነች ከሰዓት በኋላ ብንሄድ እናገኛታለን:: ከበረንዳው ላይ አትጠፋም:: በተለይ አመሻሽ ላይ" አለኝ::

እንዲህ ያለ ታሪክ እየተከታተለኝ መሆኑ አስገረመኝ:: አንድ አግሯ አብጦ ይሆን? ስል አሰብኩ::

ንፁህ! ናፍቆት! ንፁህ! ናፍቆት!

በተፈራራቂነት የህይወቴ መለያ ሆነው ሊቀሩ ይሆን? ንፁህን ለማየት ጓጓሁ::

አመሻሽ ላይ ወደ ንፁህ ቤት እንድንሄድ ጋንጪር መጣ:: መንገድ ላይ እማማ ይጋርዱ ቂጦን አየሁ:: በፈገግታ ጠርተው አገላብጠው ሳሙኝ:: ከኋላቸው ባላቸው አይጠፉም:: በከፉ አይናቸው አዩኝ:: ይጋርዱ ቂጦ ቀስ ብለው:-

"ባሌ" አሉኝ:: አርጅተዋል:: ፊታቸው ዘብዝቧል:: የልጅነት ገጠመኜ ትዝ ብሎኝ አፈርኩ:: "ምን ሆንክ ፊትህን? ደሞ አደከ"

ሌላ ሰው ማግኘት ስላልፈለኩ በአሳባሪ ወደ ቀበና ወንዝ አመራን:: ግንፍሌ ወንዝ እኔን ስታይ ጭራዋን የቆላች መሰለኝ - እንደ ወዳጅ ውሻ::

ብርዱን አልቻልኩትም:: ጥርሴ ይንገጫገጫል:: ያኔ ቢሆን ኖሮ ወደ ንፁህ ቤት መንገድ ስጀምር ልቤ ከፉኛ ይደልቅና እግሬ ይተሳሰር ነበር:: ዛሬ ልቤ የት

---

[2] የንፁህ ሽሬራ ታሪክ "ከርቢት" መጽሐፍ ውስጥ "ኩርቢቷ" በሚል ርዕስ ቀርቧል::



t.me/OLDBOOKSPDF

ንፁህ በግዴለሽነት አይታ "አጎቴ ሲያስተምር የሄደበት ገቢያ ውስጥ ያየውን ነው እዚህ መጥቶ የሳለው" አለች፡፡ እሷ እንዲታይላት የፈለገችው የእኛ የልጅነት ምስል ስለሆነ ወደዚያው ተሸጋገረች፡፡

ሥዕሉን ደግሜ አየሁት፡፡ አባቴ ፀጉሩንና ጺሙን አግኝቷል፡፡ ሴቷ ግን ማናት ስለመሆኗ አልተጠራጠርኩም፡፡ የፀጉሯና የፊቷ አለመግጠም ሁኔታ ምስሉም ላይ ይታያል፡፡ ውስጡ ቁርተው የነበሩ ጥቂት ጥያቄዎች፣ ጥቂት ሀሳቦችና ጥቂት ሸክሞች ተሟጠው ሲነጥፉ ታወቀኝ፡፡

ይኼን ነው ወዳጆቼ ልፊ እንዳካትተው የጎተጎቱኝ፡፡ እነሱንም እናንተንም አመሰግናለሁ፡፡


t.me/OLDBOOKSPDF



[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

t.me/OLDBOOKSPDF

ብር 45.60